አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የሂውማኒትስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጀርናሊዝምና የኮሚውንኬሽን
ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በቅማንት ማህበረሰብ

በ
ማኅሌት ሁነኛው

2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በቅማንት ማህበረሰብ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂውማኒትስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝምና የኮሚውንኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ኤም ኤ ዲግሪ ሚሚያ

የቀረበ

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

በ

ማኅሌት ሁነኛው

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂውማኒትስ ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝምና የኮሚውንኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍል

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በቅማንት ማህበረሰብ

በ

ማኅሌት ሁነኛው

የፊተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ዘርሁን ኸስሩም

የውስጥ ፈታኝ

የውጭ ፈታኝ ተስፋለገ ፈቀሰ

2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አ.አ.ዩ. ቤተ መጻሕፍት
ILS LIBRARY
ADDIS ABABA UNIVERSITY

ምስጋና

ለጥናቴ የሚያስፈልጉኝን ግብዓቶች በቅንነትና በፍላጎት ለሰጡኝ ለቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ለመቶ አለቃ ጥጋቡ ዘገየ ፣ ለአቶ ኢዮብ ድንቁ ፣ ለአቶ አየልኝ ተሰማ እና ለአቶ ፍርዱ ነቃ ፤

ጥናቱን እንዴት ማካሄድ እንዳለብኝ በማመላከት ፣ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው ድረስ በማረምና ገንቢ ሃሳቦችን በመስጠት የማይረሳ ድጋፍ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው ፤

መረጃዎችን ለመሰብሰብ ስጓዝ ከጎኔ በመሆን ላገዙኝና ላበረታታኝ ወንድሜ አቢይ ሁነኛው ፤

ገንቢ ሃሳቦችን በመስጠት ፣ ረቂቁን በማረም እና የአርትኦት ስራ በማከናወን ለረዱኝ ጓደኞቼ በሙሉ ፤

የነጻ ትምህርት ዕድልና ጥናቱን እንዳካሂድ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤

ለቅማንት ማህበረሰብ ወንበር ሙሉነህ መርሻ እና ለልጃቸው ቂስ አማረ ሙሉነህ ፤

ጠቃሚ መረጃዎችንና ሃሳቦችን በማፍለቅ ፣ የገንዘብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ፣ ላበረታታኝና ጊዜውን ሁሉ ሰጥቶ በትዕግስቱ ላቀናኝ ውድ ባለቤቴ ዘካሪያስ ሃይለ ፣ እንዲሁም ለተወዳጇ ልጄ ለአሚን ዘካሪያስ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።።

አጠቃሎ

ይህ ጥናት ‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በቅማንት ማህበረሰብ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ Contextual Methodological Approach ሲሆን ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በምልከታ ፣ በቃለመጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በጥናቱ ውስጥ በቅደም ተከተል ለመተንተን እንዲያስችል ገላጭ የትንተና ስልትና በጥናቱ ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎችን አውዳዊ ትርጓሜ ለመግለጽ የይዘት ትንተና ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የቅማንት ማህበረሰብ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምባቸው የፍትህ ተቋማት የአካባቢ ሽንጎ ፣ አፈሊቅ እና ወንበር እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ እነዚህ የፍትህ አካላት ደግሞ ማንኛውንም ዓይነት ግጭት ለመፍታት ‹‹ሽወን›› የተባለውን ስርዓት ይጠቀማሉ፡፡ በአብዛኛው በማህበረሰቡ ውስጥ ግጭት የሚከሰትባቸው ምክንያቶች ከኢኮኖሚ ፣ ከእሴት ፣ ከሞራልና ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ማህበረሰቡ የግድያ ግጭት ዓይነቶችን በግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት አካላት ማንነት በመነሳት (በቤተሰብ ሠራተ ፣ ከዘመድ መጣበል ፣ በጎሳ ውስጥ ፣ በጎሳዎች መጣበል) የሚለፈለው ባህ እንደ ግድያው ሁኔታ ፣ እንደ ተጋፊዎቹ ማንነት የተለያየ ሲሆን አፈጻጸሙም ሀሬዝ ፣ ድንገተ ሞትሊ ፣ ሂሽነንካ እና ዘመድኛ በተባሉ ደንቦች እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ የባልና ሚስት ጸብ በቅርባቸው ያለ ሰው ችግሩን ካልፈታ በሦስቱም የፍትህ ተቋማት እርቅ እንደሚፈጸም ከአውዳዊ ክዋኔው መረዳት ተችሏል፡፡ ጠለፋ በሁለት ዓይነት መልኩ እንደሚካሄድ እና እንደጠለፋው ዓይነት የእርቁም ሥርዓት እደሚለያይ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በማንኛውም የግጭት አፈታት ሥርዓት ላይ እርግማን ፣ ምርቃትና ምሳሌያዊ ንግግሮች የእርቁ ሥርዓት አንድ አካል መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡ በጥናቱ ግኝት እንደታየው ማህበረሰቡ ማንኛውም ዓይነት ግጭት መከሰት አይገባውም ከተከሰተም በፍጥነት መፍትሄ ማግኘት አለበት የሚል አመለካከት አለው፡፡ ጥናቱ ባህላዊው የግጭት መፍቻ ተቋመ. ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነልቦናዊ ፋይዳዎች እንዳሉት አመልክቷል፡፡ በባህላዊው ስርዓት እና በተቋማቱ የበለጠ ለመጠቀምና ማህበራዊ ፋይዳቸውን እንደያዙ እንዲቆዩ ለማድረግ ለሀገር ሽማግሌዎች እውቅና መስጠት ፣ በሞራልና በቁሳቁስ ማገዝ ፣ ባህላዊውን እውቀት ለማስቀጠል ሁሉም የሚመለከተው አካል የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ እና መሰል ሃሳቦችን ማመቻቸት እንደሚገባ በይሁንታ ጥናቱ አካቷል፡፡

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና.....i

አጠቃሎ.....ii

1 መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ 2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 4

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች 4

1.3.1 ዋና ዓላማ 4

1.3.2.ዝርዝርዓላማዎች 4

1.4 የምርምር ጥያቄዎች 5

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ 5

1.6 የጥናቱ ወሰን 5

1.7 የመረጃዎች አሠባሠብ ዘዴ 6

1.8 የመስክ ክንውን 8

1.9 በጥናቱ ላይ ያጋጠመ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 12

2 ክለሳ ድርሳናት 14

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት 14

2.1.1 ክዋኔ 14

2.1.2 የክዋኔ አለባውያን 15

2.1.2.1 አውድ 15

2.1.2.1.1 ባህላዊ አውድ 17

2.1.2.1.2 ማህበራዊ አውድ.....19
2.2 የግጭት ብያኔ.....21
2.2.1 የግጭት ዓይነቶች.....22
2.2.2 የግጭት መንስኤዎች.....23
2.2.3 የግጭት አፈታት ዘዴ.....25
2.2.3.1 ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴ.....27
2.2.3.2 ሃይማኖታዊ የግጭት አፈታት ዘዴ.....27
2.2.3.3 ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ.....28
2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት.....29
3 ማህበረ ባህላዊ ዳራ.....42
3.1 የቅማንት ህዝብ አሰፋፈርና የሚኖርበት አካባቢ.....42
3.2 የቅማንት ማህበረሰብ ቋንቋ.....43
3.3 የቅማንት ማህበረሰብ ሃይማኖት.....44
3.4 የቅማንት ማህበረሰብ አስተዳደራዊ ሁኔታ.....48
3.5 የቅማንት ማህበረሰብ የጋብቻ ስርዓት.....49
4 ግጭት ፣ የግጭት መፍቻ ተቋማትና ሥርዓቶች.....53
4.1 የግጭት እሳቤ በቅማንት ማህበረሰብ.....53
4.2 በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች መንስኤ.....54
4.2.1 ከኢኮኖሚ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች.....54
4.2.2 ከእሴት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች.....54
4.2.3 ከሞራል ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች.....55
4.2.4 ከሃይማኖት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች.....55
4.3 ባህላዊ የፍትህ ተቋማት.....57

4.3.1 የአካባቢ ሽንጎ 57
4.3.2 አፈ.ሊቅ 58
4.3.3 ወንበር 60
4.4 መደበኛው ፍርድ ቤት እና ባህላዊው የፍትህ ተቋም ያላቸው ትስስር 62
4.5 የፍትህ ተቋማቱ ግጭትን የሚያስወግዱበት ስርዓት 64
4.6 በባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ የቀረቡ አቢይ ግጭቶችና ውሳኔዎቻቸው 65
4.6.1 የነፍስ ግድያ 65
4.6.1.1 የደም ካሳ አፈ.ጻጸም 68
4.6.1.1.1 ሀሬዝ 69
4.6.1.1.2 ድንገተ ሞትሊ 69
4.6.1.1.3 ሂሽነንካ 69
4.6.1.1.4 ዘመድሻ 70
4.6.2 ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች 70
4.7.2.1 የቤተሰብ ፀብ 71
4.7.2.1.1 በቅማንት ማህበረሰብ የባልና ሚስት ባህላዊ የግጭት
አፈታት ስርዓት አውዳዊ ክዋኔ 72
4.7.3 ጠለፋ 78
4.8 በግጭት አፈታት ወቅት ሂደቱን የሚያግዙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች 84
4.9 ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ፋይዳዎች 92
5 ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳቦች 98
5.1 ማጠቃለያ 98
5.2 የይሁንታ ሃሳቦች 100
ዋቢ መጻህፍት
አባሪዎች

1 መግቢያ

የቅማንት ማህበረሰብ በርካታ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች አሉት። የአንድ ህዝብ ባህልና ወግ መገለጫ የሆኑ ተቋማትን (የእምነት ስፍራዎችን ፣ ታሪካዊ የመቃብር ቦታዎችን ፣ ባህላዊ የፍትህ አካላትን ፣ አስተዳደራዊ ስርዓቶችን ...) ማጥናት ደግሞ የህዝቡን ማንነት ለማወቅና በተለይም ፎክሎራዊ የሆኑ ጉዳዮችን ለማጤን ወሳኝ ናቸው። የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና ዓላማም በቅማንት ማኅበረሰብ ውስጥ የማኅበረሰቡ አባላት እርስ በእርስም ሆነ ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈጠሩ ግጭቶች የሚፈቱበትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ማሳየት ሲሆን የተለያዩ ዝርዝር ዓላማዎችንም አካቷል። የፍትህ አካላቱ በማህበረሰቡ ውስጥ የተከሰተ ግጭት ተባብሶ የከፋ ጉዳት ከማድረሱ በፊት እንደ ግጭቱ ዓይነት ፣ ባህርይና ደረጃ ህግና ደንብ በማውጣት ሊያደርስ የሚችለውን ቀውስ ለመከላከል ጥረት ያደርጋሉ።

ጥናቱ በአራት ክፍሎች ተደራጅቶ የቀረበ ሲሆን አደረጃጀቱም እንደሚከተለው ነው። የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ ሲሆን በስሩም የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ፣ የጥናቱ ዓላማዎች (አቢይ እና ንዑሳን ዓላማዎች)፣ የጥናቱ ውጤት የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የመስክ ክንውን እና ያጋጠመ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦቻቸውን ይዟል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ክለሳ ድርሳናት የያዘ ሲሆን በውስጡም የንድፈ ሃሳብ መሰረትንና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትን አካቷል። በንድፈ ሃሳብ መሰረት ውስጥ ስለ አውዳዊ ክዋኔና ስለ ግጭት ብያኔ ፣ ዓይነት ፣ የአፈታት ዘዴ ... በመጠኑ ተቃኝተዋል።

በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ስር ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያላቸው ዘጠኝ ያህል ጥናታዊ ጽሁፎች ተቃኝተዋል። ሦስተኛው ክፍል ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይ ነው። ስለሆነም የማህበረሰቡን አሰፋፈር ፣ ቋንቋ ፣ ሃይማኖት ፣ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ፣ ...ትውውቅ ይዟል። አራተኛውና የመጨረሻው ክፍል የቅማንት ማህበረሰብን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

ያሳያል። በውስጡም ማህበረሰቡ ስለ ግጭት ያለው እሳቤ ፣ የባህላዊ የፍትህ ተቋማቱን ዓይነት ፣ ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ የሚጠቀሙበትን ስርዓት ፣ በፍትህ ተቋማቱ ቀርበው ውሳኔ የተሰጠባቸውን የግጭት ዓይነቶች ፣ የባልና ሚስት ባህላዊ የግጭት አፈታት አውዳዊ ክዋኔ ፣ በእርቅ ሥርዓቱ ሂደት የሚታዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ፣ ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ ያላቸውን ፋይዳ ፣ የማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች እንዲሁም ዋቢ ጽሁፎችን አካቷል።

1.1. የጥናቱ ዳራ

[illegible] ከሰው ግጭት [illegible] ይገልጻል። Fisher (1982 ፣ 567) የተባሉ ምሁር ግጭት አንዱ ከሌላው ጋር የጠላትነት ስሜት ባላቸውና አንዱ ሌላውን ለማሸነፍ በሚፈልጉ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል የተለያየ ፍላጎትና ዓላማ ሲኖር የሚከሰት መሆኑን ይገልጻሉ። ከዚህ ብያኔ በመነሳት ግጭት ማህበራዊ የሆነና ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል በዓላማና በፍላጎት አለመገናኘት ምክንያት በሚፈጠር አለመግባባት የሚከሰት ድርጊት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

Tirsit Girshaw (2004፤4) Siomo Dekha (2000)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ‹‹Conflict is a natural phenomenon in human history. Conflict is relationship between two or more parties who have or think they have incompatible goals›› ከዚህ ሃሳብ ግጭት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያለ የነበረና ወደፊትም የሚኖር የተፈጥሮ ክስተት መሆኑን ፣ እንዲሁም ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች ልዩነት መካከል የሚፈጠር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በተያያዘ መልኩ እንደ Fisher and Ibrahim (2000) ገለጻ ግጭት አንድ ወገን የሌላውን ወገን ጥቅም ፣ ግብ ፣ አተያይ ፣ ፍላጎት ፣ ባህርይ መሰረት አድርጎ የሚከሰት ክስተት እንደሆነ ያብራራሉ። ይህ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል ክስተት የሰው ልጅ ማኅበረሰባዊ ፍጡር በመሆኑ ሂደቱ የነበረ ያለና የሚኖር ሲሆን በግለሰብ ፣ በቡድን ፣ በሀገር ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊፈጠር ይችላል።

ግጭት እንደየዓይነቱና ባህርይው የተለያዩ የመቆጣጠሪያ እና የማርገቢያ እንዲሁም እልባት የመስጫ መንገዶች አሉት፡፡ አንድ ማህበረሰብ በውስጡ የሚከሰቱትን ግጭቶች የሚያስወግድባቸው የራሱ የሆኑ ሥርዓቶች ፣ ህግና ደንቦች እንዲሁም ሂደቶች ይኖሩታል፡፡ እነዚህንም ግጭቶች እንደየዓይነታቸው በመለየት ለየግጭቶቹ ይበጃሉ የሚላቸውን መፍትሔዎች ለመስጠት ግጭቶችን የሚያስወግድባቸው ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ይኖሩታል፡፡ በመሆኑም ማኅበረሰቡ ከራሱ የፈለቁ የግጭት አስወጋጅ አካላት በሚሰጡት ብያኔ ይተዳደራል፡፡

ከዚህ በፊት የነበሩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየደረጃቸው እነዚህን በየማህበረሰቡ የሚፈፀሙ ትውፊታዊ ልማዶች (ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች) ወደ አካዳሚ እውቀት በማምጣት ጥናትና ምርምር በማካሄድ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት አቅርበዋል፡፡ ከነዚህም መካከል በእኔ ዳሰሳ የተደረሰባቸው ጥናቶች ቁጥር ከ1999 እስከ 2001 በመጀመሪያ ዲግሪ 3 ያህል ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን ከ1997- 2004 ዓ.ም ድረስ በሁለተኛ ዲግሪ 32 ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ የመንግስቱ ፍስሀ (1999) ከትምህርት ክፍሉ ውጪ ለህብረ ባህልና ልማነ ብዙ ክፍለ ትምህርት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው፡፡ በመጽሐፍ መልክ ታትመው የወጡና በተለያዩ ዓለምአቀፍና አገር ዓቀፍ ጉባኤዎች ላይ የቀረቡ በተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ላይ የተሰሩ 25 ጥናታዊ ጽሑፎችም ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች በተለያዩ ማኅበረሰቦች ዙሪያ የተጠኑ ሲሆኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ሂደቱን የሚያትቱ ፣ ማኅበራዊ ጠቀሜታውን የሚገልጹ ፣ ማኅበረሰቡ ይህን ባህላዊ ሥርዓት ተጠቅሞ የሚገነባውን ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት የሚያወድሱ ፣ ሂደቱን የሚመሩት አካላት ለዚህ ሥርዓት የሚጠቀሙትን ስልት የሚያስተዋውቁ ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡

የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት እንዳሏቸው ከላይ ተጠቁሟል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በተጠኚው የቅማንት ማኅበረሰብ

ውስጥ ያሉ ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶችንና ምክንያታቸውን ፣ ግጭቶቹን የሚፈቱትን ተቋማት ማንነትና የአፈታት ሂደታቸውን ፣ ወ.ዘ.ተ ማሳየት ነው።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱኝ ምክንያቶች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው በቅማንት ማኅበረሰብ ውስጥ ፎክሎርን ያማከለ የግጭት አፈታት ሥርዓትና ክዋኔ ተጠንቶ አለማግኘቱ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ባህላዊ የፍትህ ተቋሙ የተዋቀረበትን መሠረት እና ማኅበረሰቡ ስለ ባህላዊ የፍትህ ተቋሙ ያለውን አመለካከት ፣ ፍልስፍና ፣ ...ወዘተ የማወቅ ጉጉት ስላደረበኝ ነው።

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በቅማንት ማኅበረሰብ ውስጥ የማኅበረሰቡ አባላት እርስ በእርስም ሆነ ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈጠሩ ግጭቶች ዓይነትና የሚፈቱበትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ማሳየት ነው።

1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ አበይት የግጭት ዓይነቶችን እና መንስኤዎቻቸውን መለየት ፣
- ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱን አመሰራረት ፣ አወቃቀር እና የአሰራር ሂደት እንዲሁም የግጭት አፈታት ክዋኔዎችን መግለጽ ፣
- ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ ግጭትን በመከላከል ፣ በማብረድና በመፍታት ረገድ ያላቸውን ሚና ማሳየት ናቸው።

1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ጥናቱ የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል፡፡

1. የባህላዊ ተቋሞቹ ጥንተ አመጣጥ እና ማህበረሰቡ ለባህላዊ ተቋሞቹ ያለው እምነትና ታዛዥነት እንዲሁም ተቋሞቹ በነበሩበት እንዲቀጥሉ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድን ነው?
2. አስታራቂ ሽማግሌዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ምን ዓይነት ስልቶችን ይጠቀማሉ?
3. ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋሞቹ ለወረዳው ህዝብና ለመንግስት የህግ አስፈፃሚ አካላት ያላቸው ተጨባጭ ፋይዳ ምንድንነው?
4. የግጭት አፈታቱን ለመምራትና ውሳኔ ለመስጠት የሚፈቀድላቸው በየትኛው እርከን (የማኅበረሰብ ደረጃ) ያሉ ሽማግሌዎች ናቸው?

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ከተመሰረተበት ርዕስ አንጻር የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል፡፡

- የቅማንትን ማኅበረሰብ ማንነትና ማኅበራዊ ህይወት በጥቂቱም ቢሆን ያስተዋውቃል፡፡
- የአካባቢውን ትውፊታዊ ልማድ ወደ አካዳሚ እውቀት ያመጣል፡፡
- መደበኛ የፍትህ አካላት ከተሞክሮ እውቀት የሚቀስመውበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡
- በመንግስትና በየደረጃው በሚገኙ የመንግሥት መዋቅሮች በኩል ሰላምና መረጋጋትን ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት በባህላዊ ዕውቀትና ልምድ እንዲታገዝ የጥናቱ ውጤት ሊያገለግል ይችላል፡፡

1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚካሄደው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን በሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ በጭልጋ ወረዳ በኢይከል ከተማ በመሆኑ ሌሎች አጎራባች ከተሞችን አያካትትም፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በጭልጋ ወረዳ ከሚገኙት ከተሞች አይከል ብቻ የተመረጠበት ምክንያት

በብዛት የቅማንት ማኅበረሰብ የሚኖርበት በመሆኑ እና በዋነኛነት ወይም ማዕከል[1] በመሆን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ክዋኔ የሚካሄድበት ከተማ በመሆኑ ነው።

1.6 የመረጃዎች አሠባሠብ ዘዴ

የተቀረጹትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ ፣ የተነሱትን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ ተስማሚ የሆነውን ንድፈ ሃሳብ እና ስነ-ዘዴ መምረጥ ተገቢ በመሆኑ ለዚህ ጥናት contextual Methodological approach (ክዋኔ ተኮር) እና ሶስት የማይነጣጠሉ እንዲሁም ይህ ዘዴ የሚጠራቸው (የሚፈልጋቸው) የስነ-ዘዴ አይነቶችን ተጠቅሚያለሁ።

አውዳዊ አቀራረብ የተለያዩ ምሁራን እንደሚገልጹት በአውድ ውስጥ ማህበራዊ መዋቅርን ፣ አካባቢያዊ ታሪክን ፣ መቼትን ፣ ባህልን ፣ እምነትን ፣ ስርዓትን ፣ ወግና ልማድን ፣ ሃይማኖትን ፣ ወዘተ መፈተሽ የሚያስችል እንደሆነ ነው። (Ben-Amos, Bauman, Bessinger) Bessinger የአውዳዊ ጠቀሚታን ሲገልጹ ‹‹analysing text within context effectively illustrates the necessity of relating oral traditional texts to the ceremonies or circumstances in which they functioning in order to appreciate the significance›› Bessinger (1988:36) አንድ የፎክሎር ተመራማሪ ለምርምሩ አጋዥ የሆኑ መረጃዎችን ከመስክ ፣ ከመዛግብትና ከታተመ ስራዎች ሊያገኝ እንደሚችል Dorson (1972 ፣ 465) ይገልጻሉ። እነዚህን የመረጃ ምንጮች ጥቅል በሆነ መንገድ ቀዳማይ እና ካልዓይ ብሎ በሁለት መክፈል ይቻላል። በመሆኑም ለዚህ ጥናት ተገቢ የሆኑ መረጃዎች በሙሉ በዚህ መልክ የተገኙ ናቸው። ቀዳማይ ምንጮች የፎክሎር ቅንጣቶች የተከወኑባቸው ባህላዊና ማህበራዊ አውዶችን ፣ በአውዱ የተሳተፉ አቀባዮችን ፣ ለፎክሎር ቅንጣቶቹ መከወን መንስኤ የሆኑ አጋጣሚዎችን የሚመለከቱ ናቸው ፈቃደ (1999 ፣ 17)።

[1] ወንበሩ (የቅማንት ማህበረሰብ የፖለቲካና የሃይማኖት መሪ) የሚገኙት እዚሁ ከተማ (ተበር ሚካኤል) ነው። በመሆኑም ማንኛውንም ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በታማኒነት እና በተሳታፊነት የሚመሩ በመሆናቸው ይህንን ከተማ ልመርጥ ችያለሁ።)

በዚህ ጥናት መረጃዎችን ከቀዳማይ ምንጮች ለመሰብሰብ ምልከታ ፣ ቃለመጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ጥቅም ላይ ውለዋል። በመስክ ስራ ምልከታና ቃለ መጠይቅን በቅንጅት መጠቀም ሰፊ መረጃ ለመሰብሰብ ፣ የመረጃ ክፍተትን ለመመላት ፣ አመለካከቶችን ፣ ስሜቶችንና ፍልስፍናዎችን ለመገንዘብ ያግዛል። ፈቃደ (1999 ፣ 90) በዚህ ጥናት እነዚህን ዘዴዎች ተጠቅሞ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተደረገው ሂደትም በባለ ሙያዎች ምክር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በመረጃ ማደራጀት ፣ ገለጻ እና ትንተና ወቅት መረጃዎችን በክዋኔ ወቅት እንደ ነበሩ በሙሉነት ለማግኘት አስችሏል።

ምልከታ አጥኚው ጥናት ሊያካሂድበት በመረጠው ማህበረሰብ መካከል (ክዋኔ ላይ) ተገኝቶ የጥናቱ ትኩረት በሆነው የፎክሎር ዓይነት ላይ የሚያደርገው ጥልቅ አስተውሎት ነው። ምልከታ የሚያደርግበት ክዋኔ መቼቱ (ጊዜ እና ቦታው) ተፈጥሯዊ ወይም አርቲፊሻል ሊሆን ይችላል። ተፈጥሯዊ መቼት ማለት ክዋኔው የሚፈጸምበት ትክክለኛ ቦታና ጊዜ ከመሆኑም በላይ የፎክሎሩ ዓይነት በትክክል የሚከሰትበትና የሚከወንበት አጋጣሚ ነው። አርቲፊሻል መቼት ደግሞ ትክክለኛው መቼትና ክዋኔ በማይኖርበት ወይም አጥኚው በድጋሚ ለመመልከት በሚፈልግበት ጊዜ በማስመሰል የሚፈጥረው መቼት እንደሆነ Goldstein (1964 ፣ 80-81) ይገልጻሉ።

ቃለ መጠይቅ አጥኚው ጥናት በሚያደርግበት የፎክሎር ዘር ላይ ጥልቅ እውቀት ወይም ልምድ አላቸው ብሎ የመረጣቸውን እና የሚያምንባቸውን ሰዎች የተደራጀ ወይም ያልተደራጀ ጥያቄ በማቅረብ በቃል መረጃ የሚያገኝበት ዘዴ ነው። የሚያገኛቸውን መረጃዎች በማስታወሻ እና በድምጽ መቅረጫ ይይዛል። በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ጊዜ የሚያጋጥመውን የመረጃ ክፍተት ለመሸፈን እና የበለጠ ለማረጋገጥ ቁልፍ የመረጃ አቃባዮችን በመሰብሰብ የቡድን ውይይት በማድረግ ክፍተቱ ይሞላል። ይህ ጥናት ሦስቱንም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ አውሏል።

ይህ ጥናት ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ አድርጎ የወሰደው ጥናቱ በተካሄደበት ማኅበረሰብ ውስጥ በአካል በመገኘት ሥርዓቱን በመመልከት ፣ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት በማድረግ የተሰበሰበውን መረጃ ነው። ካልዓይ የመረጃ ምንጮቹ ደግሞ በጥናቱ በማቅረቢያና በመተንተኛ ዘዴነት የሚያገለግሉ ንድፈ ሃሳቦችና ጽንሰ ሃሳቦችን የያዙ መጽሐፍት ፣ ለመጀመሪያ እና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናታዊ ፅሑፎች ፣ መጣጥፎች እና ድረ ገፅ ላይ የሚገኙ መረጃዎች ናቸው። እንዲሁም የሚሰበሰቡትን መረጃዎች በጥናቱ ውስጥ በቅደም ተከተል ለመተንተን እንዲያስችል ገላጭ የምርምር ትንተና ስልትን ተጠቅሚያለሁ። በተጨማሪም በጥናቱ ወቅት የሚሰበሰቡ መረጃዎችን አውዳዊ ትርጓሜ ለመግለፅ ደግሞ የይዘት ትንተና የምርምር ማቅረቢያ ስልትን ተጠቅሚያለሁ። ይህ ስልት በገለፃ የቀረቡ መረጃዎች የቀረቡበትን አውዳዊ ትርጓሜ ለመለየት የሚጠቅም ስልት ነው።

ከመስክ ቆይታ በኋላ የተቀረጹ መረጃዎችን ወደ ወረቀት የመገልበጥ እና የማደራጀት ስራ ተሰርቷል። የተያዙ ማስታወሻዎችም በይዘታቸው እንዲሰፍሩ ተደርጓል። መረጃዎች ወደ ወረቀት በሚሰፍሩበት ጊዜ የመረጃ አቀባዮች ዳራ ፣ የክዋኔውን መቼት እና አውድ በማስገባት ከመግለጫ ጋር ለማደራጀት ተሞክሯል። ከዚህም በመነሳት መረጃዎችን በመቼታቸው እና አውዳቸው በመከፋፈል ገለጻና ትንተና ተደርጎባቸዋል።

1.7 የመስክ ክንውን

ወደ መስክ በመሄድ መረጃ ለመሰብሰብ ከመነሳቴ በፊት ከማህበረሰቡና ከአካባቢው ለመተዋወቅ ስለቅማንት የተፃፉ የተለያዩ የጥናት ዘገባዎችን ፣ የታሪክ መፃህፍትን ፣ መፅሄቶችንና የመሳሰሉትን አንብቤያለሁ።

የመስክ ተግባሬን የጀመርኩት የካቲት 15 2005 ዓ.ም ወደ ጎንደር በአውቶብስ በመጓዝ ነው። በዚያው ዕለት ከአመሻሹ 12፡45 ሰዓት ጎንደር ከተማ ደረስኩ። በምን ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንደምሠራና መረጃውን ከየት አካባቢ ልሰበስብ እንደምችል ለወንድሜ ቀደም ብዬ አሳውቸው ስለ ነበር ፣ ወንድሜ ‹‹የቅማንት ማህበረሰብ

ተወላጅ የሆነ በአይከል ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የሚሰራ ኢዮብ ድንቁ የሚባል የቅርብ ሰው አለኝ›› በማለት ስልክ ደውሎ በማግስቱ እንገናኝ ዘንድ ቀጠሮ አስያዘልኝ፡፡

በማግስቱ ቅዳሜ የካቲት 16/2005 ዓ.ም ወንድሜ ቀጠሮ ያስያዘልኝ ሰው የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ከሆኑ ሁለት የስራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን መጥቶ ተገናኘን፡፡ ከነርሱም ጋር የተለያዩ ቁም ነገሮችን ተወያየን፡፡
ሰኞ የካቲት 18 2005 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡30 ሰዓት ከወንድሜ ጋር ወደ ሞዶጋ (አይከል ከተማ) ተጓዝን፡፡ ከዚያም ጉዟችንን ከአይከል ከተማ ወጣ ብላ ወደምትገኘው የወንበር ሙሉነህ መርሻ መንደር ተበር ሚካኤል አደረግን፡፡ እዚያ እንደደረስንም ቤታቸውን ጠይቀን ወደ አጥር ግቢያቸው እንደተቃረብን የውሻ ድምጽ ስለሰማን ድምጻችንን ዘለግ አድርገን ተጣራን፡፡ ከዚያም ወንበር ሙሉነህ መርሻን ፈልገን የመጣን መሆናችንን ነገርናቸው፡፡ እነሱም ወንበሩ ፀበል ለመፀበል ልጃቸውን ቂስ አማረን ይዘው ወደ አንዘመርኩም ፀበል የሄዱ መሆናቸውንና ለ20 ቀናት ሊቆዩ እንደሚችሉ ነገሩንና ወደ አይከል ከተማ ተመለስን፡፡

በዚሁ ዕለት ከረፋዱ 5፡00 ሰዓት ሲሆን የሞዶጋ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ ክልሉ ያስጠናቸውን አንዳንድ ጥናቶች ተመለከትኩ፡፡ የሞዶጋ ወረዳን ካርታም ወሰድኩ፡፡ ከዚያም ከወንድሜ ጋር ወደ ጎንደር ተመለስን፡፡ ከማክሰኞ የካቲት 19 - ሀሙስ የካቲት 21/2005 ዓ.ም ድረስ በጎንደር ከተማ ውስጥ ያሉ የማህበረሰቡ ተወላጆችን በማፈላለግ አንዳንድ አጋዥ መረጃዎችን ስሰበስብ ቆየሁ፡፡ ከሰኞ እስከ አርብ ድረስ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በፊርጅ በፊርጅ ሰደርኳቸው፡፡ ከዚያም ጥያቄ የሆኑብኝን በማስታወሻ አሠፈርኩ፡፡

መረጃ አቀባዬ ኢዮብ የማህበረሰቡ ተወላጅ የሆኑ እና ታሪክ አዋቂ ሰው አሉ ብሎ ጥቆማ ስላደረገልኝ ቅዳሜ የካቲት 23 በድጋሚ ወደ አይከል ከተማ ከወንድሜ ጋር ተጓዝኩ፡፡ በዚሁ ዕለት ከረፋዱ 4፡00 ሲሆን መረጃ አቀባዬ ከላከልን ሰው (መልዕክተኛ) ጋር ወደ አቶ አየልኝ ተሰማ ቤት አመራን፡፡ ቤታቸው እንደ ደረስን መልዕክተኛው አቶ አየልኝን ፈልገን እንደሄድን ገልጸ

እና እንዲያስተናግዱን በትህትና ተናግሮ ‹‹ብዙ ስራ አለኝ›› በማለት ተሰናብቶን ወጣ፡፡ ከቤታቸው አጠገብ ካለ ነፋሻማ ቦታ ላይ ከከብት ቆዳ (ጠፍር) የተዘጋጁ ወንበሮች ወጡልንና ተቀመጥን፡፡ ከዚያም ሁለት ሴት ልጆቻቸው አቶ አየልኝ ተሰማ ራቅ ወዳለ ስፍራ እንሂዱና በትዕግስት እንድንጠባበቅ ገለጹልን፡፡ በዚህ ዕለት አቶ አየልኝን ከረፋዱ 5፡00-10፡00 የጠበቅናቸው ቢሆንም ቅሉ በተንቀሳቃሽ ስልካቸውም ማግኘት ስላልቻልን ፤ ይመጣሉ የሚለው ተስፋችን በመመናመኑ እርሳቸውን በሚመቻቸው ቀን ደውለው እንዲጠሩን የስልክ ቁጥራችንን ትተን ልጆቹን ተሰናብተናቸው ወደ ጎንደር ተመለስን፡፡

ሰኞ የካቲት 25/2005 ዓ.ም አቶ ነጋ ጌጤ እና አምባሳደር ዘመነ ካሴን የተባሉ የማህበረሰቡ ተወላጆችና ነዋሪነታቸው ጎንደር ከተማ የሆነ ግለሰቦችን ለማግኘት የሞከርኩ ቢሆንም በእለቱ አልተሳካልኝም ነበር፡፡ በማግስቱ አቶ ነጋ ጌጤን ለማነጋገር ጐንደር ፒያሳ የሚባል ሠፈር ውስጥ ወደ ሚገኘው የግል ፋርማሲያቸው አቀናሁ፡፡ ቦታው ስደርስ ፋርማሲያቸውን ክፍት ሆኖ ባለ ማግኜቴ በአካባቢው ወደሚገኝ አንድ ካፌ አመራሁና ቁጭ ብዬ መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡ አቶ ነጋ ጌጤ ከ40 ደቂቃ ቆይታ በኋላ መጡ፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ራሴን አስተዋውቄ የመጣሁበትን ዓላማ ነግሪያቸው የምፈልጋቸውን መረጃዎች በጥያቄ መልክ አዘጋጅቼ እንድመጣ ነግረውኝ በዚህ ተስማምተን ተለያየን፡፡

በዚሁ ዕለት አቶ ነጋ ጌጤን ልጠይቃቸው የሚገቡኝን ጥያቄዎች አዘጋጀሁ፡፡ በማግስቱ ረቡዕ የካቲት 27/2005 ዓ.ም ጠዋት 3፡00 ሰዓት አቶ ነጋ ጌጤን አገኘኋቸው፡፡ አቶ ነጋ ጌጤ በማህበረሰቡ ዙሪያ መጽሃፍ የጻፉ ሰው ናቸው፡፡ ከእርሳቸው ጋር ከ3፡00-6፡30 ሰዓት ድረስ ብዙ ቁምነገሮችን ተጨዋወትን፡፡ ከዚያም ስለ ሰጡኝ መረጃ ሁሉ ከልብ አመሰግናቸው ተለያየን፡፡

ከሀሙስ የካቲት 28/2005 ዓ.ም እስከ ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ድረስ በአይክል ከተማ ውስጥ በአገር ሽማግሌዎች የሚዳኝ የባልና ሚስት ባህላዊ

የግጭት አፈታት ስርዓቱ ክዋኔን አይቼ አስፈላጊ መረጃዎችን ከሰበሰብኩ በኋላ እሁድ መጋቢት 1/2005 ዓ.ም ወደ ጎንደር ከተማ ተመለስኩ።

ሰኞ መጋቢት 2/2005 ዓ.ም አቶ አየልኝ ተሰማ ወደ አይከል ብሄድ እንደማገኛቸው ደውለው ስለገለጹልኝ ከረፋዱ 3፡30 ሲሆን ወደ አይከል አመራሁ። ቤታቸው አይከል ከተማ ስለነበር ብቻየን ለመሄድም ሆነ አቅጣጫ ለማወቅ አልተቸገርኩም ነበር። እንደደረስኩም ሰላምታ ተለዋውጠን በባለፈው ጊዜ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ችግር እንደዘገዩ ገልጸው ይቅርታ ጠየቁኝ። እኔም ምንም ማለት እንዳልሆነ ገልጬላቸው ወደ ቤት ይዘውኝ ዘለቁ። ከዚያም በጥያቄ መልክ አዘጋጅቼ የወሰድኳቸውን የመወያያ ሃሳቦች በማቅረብ ከተወያየን በኋላ በቤት ውስጥ ሲፈላ የነበረው ቡና ስለደረሰ እርሱን ጠጥቼ እንድሄድ ጋበዙኝ እና ቁጭ አልኩ። ወዲያው አቶ አየልኝ ሚስታቸውን ወ/ሮ በላይነሽን በመጥራት ምሳ እንዲቀርብ አዘዙ።

ወ/ሮ በላይነሽ በአባት መሶብ[2] የተደራረበ ብዙ እንጀራዎችን ይዘው መጡ። እንደገናም ተመልሰው በመሄድ በወጭት[3] ስጋ ወጥ እና በግራራ እርጎ ይዘው መጡ። ከዚያም በመሶቡ ዙሪያ እንድንቀመጥ እየጠቆሙ አመላከቱን። እኔ ለወጉም ቢሆን ተግደርድሬ እሺ አልኩ። የቤቱን ጥግ ይዘው የተሰሩት መደቦች ላይ ተኮልኩለን ተቀመጥን። በመጀመሪያ አቶ አየልኝ ፣ ከርሳቸው በስተቀኝ ደግሞ ባለቤታቸው ወ/ሮ በላይነሽ ፣ ፊትለፊታቸው የልጃቸው ባል አቶ እውነቱ ፣ ከርሱ በስተግራ ባለቤቱ እና ለነአቶ አየልኝ የበኸር (የመጀመሪያ) ልጅ የሆነችው እነየ ፣ ከእነየ ጎን የአቶ አየልኝ የወንድም ልጅ አዳነ እና ከእርሱ ጎን ደግሞ እኔ ሆነን ተቀመጥን። ከዚያም የቤቱ አባወራ አቶ አየልኝ በጸሎት ባርከው ቡራኬ ከሰጡን በኋላ መመገብ ጀመርን። ወዲያው ወ/ሮ በላይነሽ የቤቱን የመጨረሻ ልጅ ‹‹የማታ›› ብለው ተጣርተው የሚጠጣ እንድታመጣ አዘዟት። ልጅቷ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አንድ ትልቅ ዋንጫ እና ብዙ የኢኬል ኩባያዎች ፣ በጆግ ጠላ ይዛ ተመለሰች።

---

[2] እግሩ በጣም ረዥም መሶብ ሆኖ የበዓል ቀን እና እንግዳ ሲመጣ ቤተሰቡ ተሰባስቦ የሚበላበት የመሶብ ዓይነት ነው። ይህ መሶብ በከተማ አካባቢ እንደ ቤት ማስዋቢያ ይጠቀሙበታል።
[3] የድስት ዓይነት ሆኖ ዝርግ የሆነ በማህበረሰቡ አካባቢ በስፋት የሚጠቀሙበት ነው።

ጠላውን ከአባቷ በመጀመር እንደ አቀማመጣችን ለርሳቸው በዋንጫ ለሌሎቻችን ደግሞ በኒኬል ኩባያ ቀድታልን ቡና ከዳሚ ስለነበረች ወደ ቡናዋ ተመለሰች። ከቀረበው ምግብ ከእንጀራውም ፣ ከወጡም ፣ ከጠላውም እየተጨመረ እስኪጨንቀኝ ከበላን በኋላ ማዕዱ ከፍ አለ። የቀረበውንም ቡና በተቀመጥንበት ጠጥተን እኔ እንደመሸብኝ ገልጨላቸው ለመሄድ ተነሳሁ። አቶ አየልኝ የቤቱን ሰው ከመቀመጫቸው እንዲነሱ አዘው ‹‹ጸሎት አድርግን መርቀን እንሸኛት›› አሏቸው። ከመቅጽበት የማላቀው እና ደስ የሚል ስሜት ወረረኝ። ከልብ የሆነ ፈገግታ ፈገግ አልኩ። ከዚያም ከሦስት ደቂቃ ላልበለጠ ጊዜ ጸሎት ተደረገ። ሁሉም የቤተሰቡ አባላት እንደ ዕድሜያቸው እና ማህበራዊ ደረጃቸው እየተነሱ መመረቅ ጀመሩ። ‹‹ፈጣሪ ያሰብሽውን ያሳካልሽ ፤ ውጤትሽን ያሳምረው ፤ በሰላም ግቢ ፤ መንገዱን ቀኝ ያርግልሽ ፤ ልጅሽን ያሳድግልሽ ፤ ፈጣሪ ይጠብቅሽ ፤ ፈጣሪ ይባርክሽ ›› አሉኝ። ከዚህ በኋላ ተሰናብቻቸው ከቤት ወጣሁ። በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ምርቃት ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና ተፈላጊ ጉዳይ ነው። በተለይም በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ወቅት ትልቅ ሚና የሚጫወት ፣ የበዳይንና የተበዳይን እንጀት የሚያራራ ዋና መሳሪያ ነው።

አቶ አየልኝ እና የወንድማቸው ልጅ አዳነ ‹‹አሳፍረንሽ እንምጣ›› ብለውኝ አብረን የጎንደር መኪና ወደማገኝበት ወደ መናኸሪያ ሄድን። በዛ እያለን የጎንደር መኪና ቶሎ ባለመምጣቱ ጥላ የሆነ ስፍራ ፊልማን ቁጭ አልን። ትንሽ ጊዜ እንደቆየን ወደ ጎንደር የሚሄድ መኪና በመምጣቱ በወጉ እንኳን ሳንሰነባበት እየተሯሯጥን ወደ መኪናው ከሄድን በኋላ እኔን እንደ ምንም አሳፍረው በመኪናው መስኮት ‹‹ቻው›› ብለውኝ ሄዱ። ከአመሻሽ 11:45 ሲሆን ወደ ጎንደር ከተማ ደረስኩ። ለሁለት ቀናት ያህል የቀሩኝ ጉዳዮች ካሉ በማለት መረጃዎቼን ሁሉ ፈተሽኩ። ከዚያም መጋቢት 5/2005 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

1.8 በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

የመጀመሪያው ችግር መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሄድኩ ጊዜ መረጃ አቀባዮችን አለማግኘት ነበር። ለዚህም የወሰድኩት የመፍትሄ እርምጃ ጎንደር ከተማ ውስጥ

የሚኖሩ የማህበረሰቡ ተወላጆችን መተዋወቅ ነበር። ከዚያም እነርሱ ለተለያዩ (ጭልጋም ሆነ ትክል ድንጋይ ለሚኖሩ) የማህበረሰቡ ተወላጆች የመጣህበትን ዓላማ ገልፀው ደብዳቤ ስለፃፉልኝ ሰዎችን እንደ ልብ ማግኘት ችያለሁ።

ሌላው ችግር በጀት ነው። ዩኒቨርሲቲው ጥናታዊ ስራውን ጀምሮ ለመጨረስ የበጀተው ገንዘብ አነስተኛ በመሆኑ ገንዘቡ መረጃ ሰብስቦ ለመምጣት እንኳን የማይበቃ ነበር። ነገር ግን ከቤተሰቦቼና ከባለቤቴ በተደረገልኝ ድጋፍ ጥናቱ ከዳር ደርሷል። በመስክ በተገኘሁበት ወቅት በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚከሰቱ ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶች መካከል የግድያ ግጭት አፈታት ስርዓት አለማግኘቴ አንዱ ዋና ችግር ነው። ይህንን ችግር ለማቃለል ከዚህ በፊት ውሳኔ የተሰጠባቸውን በቃለመጠይቅ ሰብስቢያለሁ።

2 ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ የንድፈ ሃሳብ መሰረትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ይቀርባሉ። በንድፈ ሃሳብ መሰረት ለዚህ ጥናት ተስማሚ ሆኖ ስለተመረጠው አውዳዊ አቀራረብና ስለግጭት ይነገራል። በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ዝምድና ስላላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ዳሰሳ ይደረጋል።

2.1 ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

2.1.1 ክዋኔ

ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሃሳብ በዋነኛነት በመስክ ጥናትና ምርምር ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ስለተጠኚው ማህበረሰብ ወይም ቡድን ዝርዝር መረጃ ከነባራዊ ሁኔታቸው (ክዋኔያቸው) ለመሰብሰብና ለመገንዘብ ይረዳል። አብዛኛዎቹ የፊክሎር ዘርፎች እንደ ዓይነታቸውና ባህርያቸው ይለያዩ እንጂ ክዋኔ ግን የጋራ ባህርያቸው ነው። እንደ ባህሉ ፣ ዘመኑ እና እንደሚጠናው ጉዳይ መለያየቱ ፎክሎር ተለዋዋጭ መሆኑን ያሳያል እንጂ ያለ ክዋኔ ፎክሎርን ማጥናት አይታሰብም። በፎክሎር አንድ ስርዓት ሲከናወን የመከወኛ ምክንያት ፣ ክዋኝ ፣ አውድ ፣ ታዳሚ ፣ የሚደረስበት መንገድ ፣ የክዋኔ መሪዎች ፣ የክዋኔ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልጉ (Finnegan 1970 ፣ 2 ፣ 1977 28 ፣ Bauman 1977 ፣ 13 ፣ Vansina 1985 ፣ 94 ፣ Sims እና Stephens 2005 ፣ 128) ይገልጻሉ።

ክዋኔ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በውስጡ በርካታ ነገሮችን የያዘ ሲሆን ዋናው ዓላማው ኪነ ጥበባዊ ፋይዳ መፍጠር (ማስገኘት) ነው። በመሆኑም የፎክሎር ክዋኔ ኪነ ጥባባዊነቱ የሚታወቀው በክዋኔው ሁኔታ ፣ በክዋኙ ፣ በኪነ ጥበቡ ቅርጽ ፣ በተሳታፊዎቹ እና በመቸቱ ነው። (Bauman 1977 ፣ 4) ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ዋናው ጉዳይ ነው። ያለክዋኔ የትኛውንም የፎክሎር ጥናት በማካሄድ የፎክሎር ሃብቱን መሰረታዊ ይዘት ማግኘትና መረዳት ያስቸግራል። የክዋኔ አለባዊያን አንዱ ከሌላው ጋር የጠበቀ ትስስር እና ዝምድና በመፍጠር

በክዋኞቹ እና በተሳታፊዎቹ መካከል የጋራ ግንኙነት እና ተግባር እንዲያከናውኑ ያደርጋሉ።።

Sims እና Stephens (2005) እንደሚገልጹት፡- ክዋኔ በተግባር የሚገለጽ ስራ ሲሆን ተሳታፊዎችን ማሳተፍ ግድ ይላል።። ይህም እንደየልምዳቸውና እንዳላቸው ክህሎት መሳተፍ እንዲችሉ እድል ይፈጥራል።። ክዋኔ በአግባቡ እንዲከወን ከተፈለገ ክዋኔው የሚከናወንበት መቼት (ጊዜና ቦታ) ፣ ተሳታፊዎች እና ክዋኞች መገኘት አለባቸው።።

ክዋኔ እንደየባህሉ ዓይነትና ይዘት የተለያየ አቀራረብ ይኖረዋል።። በመሆኑም ክዋኔ የሚቀርብበትና የሚተረጎምበት ሁኔታ የተለያየ ይሁን እንጂ ዋናው ጉዳይ ፎክሎር ያለ ክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውናም ሊኖረው እንደማይችል የመስኩ ምሁራን ይጠቁማሉ (Finnegan 1977)።። በክዋኔ ተኮር አቀራረብ አንድን ክዋኔ ለማጥናት/ለመረዳት የተለያዩ ነጥቦች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል።። ከእነዚህም ውስጥ ክዋኙ ፣ አድማጩ/ ተደራሲው ፣ ለክዋኔ የሚቀርበው ጉዳይ ፣ መቼቱ ፣ መልዕክቱ ፣ የአቀራረብ ቅደም ተከተሉ ፣ ደንቡ እና የአድማጩ ምላሽ ዋነኞቹ ናቸው።።

2.1.2 የክዋኔ አለባውያን

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ማንኛውንም ፎክሎራዊ ጉዳይ ለማጥናት ሲታሰብ ክዋኔ የማይቀር ነገር ነው።። ክዋኔ የሚከወነው ወይም የሚገለጸው ደግሞ በአውድ በመሆኑ ፣ አውድ ክዋኔ የሚፈጸምበትን ሁኔት አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይ ነው።። ስለሆነም ለዚህ ጥናት የተመረጠው አውዳዊ አቀራረብ በመሆኑ ከዚህ በታች ይቀርባል።።

2.1.2.1 አውድ

አውዳዊ ንድፈ ሃሳብ ተከታታይ ጥናትና ምርምር የሚጠይቅ በመሆኑ በቤተ መጽሐፍት የተወሰነውን የጥናት አቅጣጫ የቀየረ ሰፊ የጥናት ዘርፍ ያለው ንድፈ ሃሳብ ነው።።ይህም ከረጅም ጊዜ በፊት በቤተ መጽሐፍት ብቻ ተገድበው ሲጠኑ የነበሩ የፎክሎር ጥናቶች የተጠኚዎችን የክዋኔ አውድ ከግምት ውስጥ

ሳያስገቡ የሚጠኑ ስለነበሩ የጥናቶቹ ግኝቶች በከፊል ውጤታማ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የተቀየሰ ወይም የተፈጠረ ንድፈ ሃሳብ ነው።

የክዋኔ አውድ የሚፈጠረው ወይም የሚኖረው ክዋኞች የሚከውኑባቸው ቦታዎች ፣ ማህበራዊ ሁኔታዎች ፣ እንዲሁም በተመልካቾችና በክዋኞች መካከል መስተጋብር ሲፈጠር ወይም ሲኖር እንደሆነ Sims እና Stephens (2005 ፡ 134) ይገልጻሉ።

አውድ በአንድ ሁነት ውስጥ የሚገኝና የሚታይ አጠቃላይ ድባብን የሚገልጽ ነው። በመሆኑም አውድ የክዋኔን ቦታ ፣ ጊዜ ፣ እና የተለያዩ እምነታዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ነው። ሆኖም የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሲሰጡት ይስተዋላል። Sims እና Stephens (2005 ፡ 137) አውድን ‹‹Context refers to anything and everything that surrounds a text and performance›› በማለት ይገልጹታል። Dundes በበኩላቸው አውድ ማለት አንድ ክዋኔ ሲካሔድ የሚታይበት ቦታ ነው በማለት ይገልጹታል። Ben-Amos (1971 ፡ 5) ደግሞ ባህላዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል። ጠቅለል ተደርጎ ግን አውድ አንድ የፎክሎር ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት ያለውን አጠቃላይ የክዋኔ ድባብ የሚያመላክት ነው። ክዋኔውን ፣ የሚከወንበትን መቼት (ጊዜና ቦታ) ፣ የክዋኔውን ሁኔታ ፣ የመከወኛ ቁሳቁሶችን ፣ የክዋኔውን ድርጊቶች ፣ የታዳሚንና የክዋኙን መስተጋብር ይይዛል። Ben Amos (1971 ፡ 5) ፣ Bauman (1977 ፡ 37) ፣ Bascom (1986 ፡ 36)።

የመስኩ ምሁራን አንድ የፎክሎር ክዋኔ ቢያንስ ሁለት አውዶች ይኖሩታል ይላሉ። እነዚህም ባህላዊ እና ማህበራዊ አውድ ናቸው። ባህላዊ አውድ የአንድ ቡድን ብቻ የሆነ የግንኙነት/ የመግባቢያ ደንብ ሲሆን ማህበራዊ አውድ ደግሞ ከአንድ ቡድን አልፎ ብዙዎችን ሊያሳትፍ የሚችል አውድ በመሆኑ ይህን አውድ ለመረዳት የማህበረሰቡን ኢኮኖሚያዊ መሰረት ፣ ፖለቲካዊ መዋቅሮች እና ማህበራዊ ባህርያትን መረዳት ይገባል ይላሉ። እንደ ክዋኔ ተኮር

አቀራረብ የትኛውንም ፎክሎራዊ ጉዳይ መረዳትና መተርጎም የሚቻለው በዚያው በማህበረሰቡ ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ውስጥ ሆኖ መሆን እንዳለበት ይመክራሉ። ከመስክ ስራ የተገኘውን መረጃም በእነዚህ ሁለት የአውድ ዓይነቶች መድቦ መተንተን ተገቢ መሆኑን ምሁራኑ ይመክራሉ Bauman (1983 : 363-7) ፣ Ben Amos (1992 : 209)።

2.1.2.1.1 ባህላዊ አውድ

ይህ የአውድ ዓይነት ለፎክሎር ቅንጣቱ በየባህሉ የሚሰጠውን ትርጉም እና ትዕምርታዊ ግንኙነቶችን ይመለከታል። በውስጡም ትዕምርታዊ አውድ ፣ ተቋማዊ አውድና ተግባቦታዊ አውድ የተባሉ ሦስት ንዑሳን አውዶችን ያቅፋል። እያንዳንዱን በዝርዝር እንመልከታለን።

ትዕምርታዊ አውድ፡- ይህ አውድ የፎክሎርን ባህላዊ አውድ ለመረዳት ወሳኝ ነው። አንድ የፎክሎር ዓይነት ከይዘት ፣ ከትርጉም እና ከምንነት አንጻር ያለው አንድምታ ምን እንደሆነ ለማወቅ ይረዳል። የአንድን ፎክሎር ባህላዊ ትርጉም ለማወቅ በራሱ በባህሉ ውስጥ ባሉ የአተረጓጎም እይታዎች ላይ መመርኮዝ ያስፈልጋል። የባህሉ ባለቤቶች በፎክሎራቸው ውስጥ የህይወት መስመራቸው በምን መልኩ እንደተወከለ ፣ እንዴት እንደተላለፈ እና ምን ምን እምነቶች እና እሴቶች እንደተዛመዱበት ይመረምራል። በፎክሎር ዓይነቱ ውስጥ መንስኤ እና ውጤት ፣ ተነሳሽነት እና ምርጫ ፣ የአከዋወን ስልቶች ፣ ትዕምርታዊ እና ዘይቤያዊ አገላለጾች እንዴት እንደተገለጹበት ያጤናል። ለዚህም ልምዱ ያላቸው ፎክለረኞች ባህላዊ ትርጉምን ከባህሉ ባለቤቶች በቀጥታ ይወስዳሉ። Bauman (1983 : 363)።

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጸመው ለፈጣሪያቸው ጸሎት ሲያደርሱ የሚያቀርቧቸው መስዋዕቶች ፣ በዓመታዊ ክብረ በዓላት ላይ የሚፈጽሟቸው ክዋኔዎች እያንዳንዳቸው ትዕምርታዊ ትርጉም አላቸው። በመሆኑም በዚህ ጥናት የእነዚህ ባህላዊ ትዕምርቶች ትርጉም ከባህሉ ባለቤቶች በቀጥታ የተወሰዱ ናቸው።

ተቋማዊ አውድ፡- ይህ አውድ አንድ የፎክሎር ቅንጣት በተለያዩ ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ያለውን አውድ ይመለከታል። ‹‹ተቋማት›› የሚለው ቃል ፖለቲካን ፣ ሃይማኖትን ፣ ኢኮኖሚን ፣ ቡድንን ፣ ጎረቤትን እና ለተለያዩ ጉዳዮች አንድ ላይ የሚሰበሰቡ ሰዎችን ይገልጻል። እነዚህን ተቋማት አንድ የፎክሎር ቅንጣት በምን እንዴት ያገኛቸዋል ፣ ባህላዊ መስተዳደሩን ፣ መዋቅሩን ፣ ህግና ደንቡን ፣ ለማወቅ ባህላዊ ተቋሙ ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። Bauman (1983 : 364)። የቅማንት ማህበረሰብ የሚከተለው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ወንጀልን በመቀነስ ፣ ስነ ምግባርን በማስተማር ፣ የእርስ በርስ ግንኙነትን በማጠናከር ፣ ዘላቂ ሰላምን በማስፈን ፣ ለፖለቲካዊ አሰራር ፣ ለሃይማኖታዊ አስተምህሮ እና ለማህበራዊ ግንኙነቶች የጋራ አገልግሎት ይሰጣል።

በአጠቃላይ ይህ አውድ ባህላዊና መንፈሳዊ ተቋማት የሚመሩበትን ህግና ደንብ ፣ የተቋሙን አመሰራረትና ከየት መጥነት ፣ ለሚመሩበት ህግና ደንብ ምን ዓይነት ትርጉም እንደሚሰጡ የሚመለከት ነው።

ተግባቦታዊ አውድ ፡- አንዱ የፎክሎር ቅንጣት ከሌላው ቅንጣት ጋር ያለውን ዝምድና ይመለከታል። ለምሳሌ በቅማንት ማህበረሰብ የሚፈጸመው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ከስነ ቃል ፣ ከቁሳዊ ባህል ፣ ከትውን ጥበባት እና ከመሳሰሉት ጋር በምን እንደሚጣመር በመመርመር የሚገኝ አውድ ነው። በባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱ ወቅት አስታራቂ ሽማግሌዎች ወይም ወንበሩ የሚናገሯቸው ከባህላዊ የግጭት አፈታቱ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች[4] ፣ በስርዓቱ ሂደት ወቅት የሚጠቀሟቸው መገልገያ ቁሳቁሶች ፣ እና የእርቅ ማጽኛ ብለው የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ስርዓቱ ከሌሎች የፎክሎር ዘውጎች ጋር የሚኖረውን ዝምድና የሚያመላክቱ ናቸው።

[4] ወንበሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን የሚጠቀመው ለግድያ የግጭት አፈታት ሲሆን ይኸውም ህሬዝ በሚባል ደንብ ለሚፈጸም የደም ካሳ የእርቅ ስርዓት ላይ ነው። እዮብ ድንቁ የካቲት 19/2005 ዓ.ም አይክል (ቃለ መጠይቅ)

2.1.2.1.2 ማህበራዊ አውድ

ይህ የክዋኔ አውድ በክዋኔ ወቅት የሚታየውን አጠቃላይ ድባብ የሚያመለክት ሲሆን በውስጡም የክዋኞቹና የተሳታፊዎቹ ማንነት ፣ ማህበራዊ ደረጃ ፣ ሃይማኖታዊ እውቀት ፣ የስራ ድርሻቸውን ይይዛል። በተጨማሪም በዘር ፣ በቋንቋ ፣ በጎሳ ፣ በጾታ ወ.ዘ.ተ. መለያየታቸው የሚፈጥረው አጠቃላይ ድባብ ማህበራዊ አውድ እንደሚባል Ben Amos (1971 : 8-9) ፣ Finnegan (1977 : 214) ፣ Bauman 1977 : 38) ፣ Vansian (1985 : 34) ይገልጻሉ። በአንድ ክበራ የሚሳተፉ ሰዎችን በዕድሜ ፣ በጾታ ፣ በሃይማኖታዊ እውቀት ፣ በማህበራዊ ደረጃ እና በመ.ያ መለያየታቸውን መገንዘብና መረዳት የማህበራዊ አውዱን አጠቃላይ ድባብ በቀላሉ ለማወቅ ያስችላል።

ማህበረሰቡ የተመሰረተበት የኢኮኖሚ መሰረት፡- አንድ ማህበረሰብ የሚተዳደርበትን የኢኮኖሚ መሰረት እንዴት እንደሚመርጥ ወይም ለምን እንደመረጠው የሚያይ ሲሆን የመተዳደሪያ ደንባቸውን እንዴት እንደሚደነግጉም ጭምር ይመለከታል። ለምሳሌ አንድ ማህበረሰብ የሚተዳደረው ከብት በማርባት ፣ በእርሻ ፣ አሳ በማጥመድ ፣ መንፈሳዊ አገልግሎት በመስጠት ወ. ዘ.ተ. ሊሆን ይችላል።

ግለሰባዊ አውድ ፡- ስለ ቡድን የተለያዩ ፎክሎሪስቶች የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንዳንዶቹ ቡድን (Folk) የሚባሉት ‹‹ገበሬዎች ናቸው›› ሲሉ በሌላ ወገን ያሉት ደግሞ ‹‹አንድን ነገር የጋራ አድርገው የሚጠቀሙ ማናቸውም ቡድኖች ናቸው›› በማለት ይገልጻሉ። ነገር ግን ፎክሎራዊ ንድፈ ሃሳቦች እየተስፋፉ በመምጣታቸው ቡድንን በጎሳ ፣ በዘር ፣ በስራ ፣ በዕድሜ ፣ በጾታ ፣ ሰይቶ ከመከፋፈልም በላይ በግለሰብ እና በቤተሰብ ደረጃ ቡድን ሊኖር እንደሚችል እየታመነ መጥቷል። ስለዚህም የፎክሎሩን አውድ ለመረዳት የፎክሎሩን ባለቤቶች ማንነት ማወቅ ግድ ይላል።

ፎክሎር በቡድን እንደሚከወነው ሁሉ በግለሰብም ይከወናል። ፎክሎራዊ ጉዳዩ በግለሰቡ ህይወት ውስጥ የሚይዘው ቦታ ፣ ለግለሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ ፣

ግለሰቡለፎክሎሩ የሚሰጠው ትርጉም ፣ እና ከሌሎች ግለሰቦች/ቡድኖች ጋር የተዋቀረበት ሁኔታ በዚህ አውድ ይጠናል። Bauman (1983 : 365) በቅማንት ብሂረሰብም የ‹‹ሀሸነው›› ስርዓት ከቡድናዊነት ባለፈ በግለሰብም ደረጃ በሰፈው ትርጉም ይሰጣል። ለምሳሌ፡- ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ ለብቻው ወንዝ ወርዶ የእራሱን ጸጉር እና የብልቱን ጸጉር ይላጫል። ከዚያም ለጓደኞቹ ይህን ማድረጉን ያሳውቃቸዋል። እነርሱም እየዘፈኑ እና እየሸለሉ ወደቤቱ ይወስዱታል።

ሁኔታዊ አውድ ፡- ይህ አውድ የፎክሎር ቅንጣቱን ወቅታዊ ትርጉም ለማወቅ የሚያግዝ እና በአሁኑ ጊዜ ፎክሎሪስቶች በስፋት የሚጠቀሙበት አውድ ነው። በዚህ አውድ ውስጥ የሚጠናው የፎክሎር ቅንጣት አከዋወኑና አወቃቀሩ ወቅታዊ/ሁኔታዊ ነው። ይህ አውድ የፎክሎሩን ተጨባጭ መቼት ፣ የተሳታፊዎችን ማንነትና ሚና ፣ ባህላዊ የክዋኔ ህጎችን ፣ የተግባቦትንና የአተረጓጎም ደንቦችን ፣ የተግባራትን ቅደም ተከተል እና የሁኔታውን ፍሰት ለመረዳት የሚያስችል በመሆኑ በጣም ተመራጭ ያደርገዋል።

በአንድ የፎክሎር ቅንጣት ውስጥ የተደራጀ ፣ ፍሰታዊ እና የተለመደ አከዋወን ወይም አውድ ሊኖር ይችላል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ ለውጥ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። እነዚህ ሁኔታዎች የሚከሰቱትም ለክዋኔ ከሚመረጠው ቅንጣት ፣ ለመከወን ከምንጠቀመው ስልት ፣ ከተፈጠረው አጋጣሚያዊ ጉዳይ እና ከሁኔታው ጊዜያዊ መዋቅር አንጻር ሊሆን ይችላል። በዚህም የተነሳ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ጥቅል ባህላዊ ትርጉም በተጨማሪ ሌላ የአተረጓጎም አቅጣጫን አዋኂው እንዲመራመር ያስችለዋል። Bauman (1983 : 365-6)

በአጠቃላይ አንድ የፎክሎር ባለሙያ አንድን የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ለማጥናት ሲነሳ ግምት ውስጥ የሚገቡና የማይቀሩ ነገሮች የክዋኙ የግል ተውኔታዊ አቀራረብ ፣ የተመጠነ ምታዊ እንቅስቃሴ ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ እና የፊት ገጽታ ፣ የአከዋወን ስልት ፣ የክዋኙና የታዳሚው መስተጋብር ፣ የክዋኔው

መቼት ፣ የአከዋወኑ ሁኔታ ፣ የክዋኔው አጠቃላይ ድባብ ፣ በሚገባ ማጤንና ማስተዋል ተገቢነት እንዳለው Bauman (1977 : 28) ፣ Finnegan (1977 : 214) ፣ Sims ና Stephens (2005 : 155) ፣ Mackdonald (1972 : 410) ይጠቁማለ።።

2.2 የግጭት ብያኔ

የሰው ልጅ ማህበር ፈጥሮ ሥርዓት አበጅቶ በዚህ ዓለም መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ግጭትም አብሮት ኖሯል። ዛሬም በሚያደርገው መስተጋብር በግጭት ሂደት ውስጥ እንዳለና ለወደፊትም እንደሚኖር ብዙዎች ይስማሙበታል። ‹‹Homosapiens has been learning about conflict through its development. That knowledge is spread across humanity, residing wherever humans live, work, and play.›› (Bartos and Wehr,2002 : 1)

Bartos and Wehr የተለያዩ ተመራማሪዎች እንደየሙያ መስካቸው የየራሳቸውን ብያኔዎች ሲሰጡ የቆዩ መሆናቸውን ይገልጻለ።። ‹‹Psycologists might define coneflict in terms of adversariesinner states, sociologist in terms of observable behavior aned son›› (Bartos and Wehr,2002 : 1)

እንዲህም በመሆኑ የዘርፉ ሊቃውንት ግጭት ማለት ይኼ ፣ ይኼ ነው ብለው ሁሉንም የሚያስማማ ወጥ የሆነ ብያኔ መስጠት እንደተቸገሩ እንገነዘባለን። ግጭት ገሃድና ስውር በሆነ መንገድ ጎጂና ጠቃሚ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ይሆናል። Bartos and Wehr Park aned Burges እና Max and snyder የተባለ ሰዎችን ጠቅሰው እንዲህ ይላለ።። ‹‹Conflict is a struggle for status.›› ‹‹Conflict is a struggle not only for status but also for scarcees and significant social change.›› (Bartos and Wehr,2002 : 10)

2.2.1 የግጭት ዓይነቶች

የዘርፉ ምሁራን የግጭት ዓይነቶችን ከግጭቱ ደረጃ ፣ ግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች ማንነት ፣ ግጭቱ ከሚያስከትለው ውጤት እና የግጭቱ ተሳታፊዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ማህበራዊ ደረጃ አንጻር ይከፋፍሏቸዋል።

እንደ Mpangala (2004 ፡ 1) አስተያየት ግጭትን በዓይነት ለመፈረጅ የተለያዩ መንገዶችን መከተል ይቻላል። ከውስብስብነት አንጻር የተወሳሰበ እና ያልተወሳሰበ ግጭቶች ፣ ከጊዜ አኳያ ደግሞ ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ ግጭቶች እና ለረጅም ጊዜ የሚዘልቁ ግጭቶች ፣ ሀብት የሚያስከትሉ እና ሀብት የማያስከትሉ ፣ የግጭቱን መጠን መሰረት አድርጎ ውስጣዊ ፣ ክልላዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሊባል ይችላል። ሌላው ደግሞ የግጭቱን አስፈላጊነት ወይም አላስፈላጊነት መሰረት ያደረገ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አፍሪካዊያን ለነጻነታቸው ሲሉ ከቅኝ ገዥዎች ጋር ያደርጉት የነበረው ፍልሚያ ‹‹ አስፈላጊ›› የሚባል ዓይነት መሆኑን ይገልጻል።

ግጭቱ ከተከሰተበት ደረጃ አንጻር ግለሰብ ከግለሰብ ፣ ቡድን ከቡድን ፣ ጎሳ ከጎሳ ፣ ማህበረሰብ ከማህረሰብ በማለት ይከፋፍሏቸዋል። Medhane (2004 ፡ 3) በግጭት ውስጥ ከሚሳተፉት ሰዎች ማንነት በመነሳት የብሄር ግጭት ፣ የቤተሰብ ግጭት ፣ እና የጎሳ ግጭት በማለት ይከፍሏቸዋል። Assefa Abebe (2001 ፡ 24) ግጭቱ ከሚያስከትለው ውጤት በመነሳት አዎንታዊ (ገንቢ) ግጭት (Constructive Conflict) እና አሉታዊ (አውዳሚ) ግጭት (Destructive Conflict) በማለት በሁለት ይከፍሏቸዋል። Augsburger (1992 ፡ 47) አዎንታዊ ግጭት የሚባለው የግጭቱ ተሳታፊዎች በጠቅላላ በግጭቱ አፈታት ሂደትና በሚገኘው መፍትሔ የሚረኩበትና በፍጻሜውም ሁለቱ አካላት ተጠቃሚ (ደስተኛ) የሚሆኑበት የግጭት ዓይነት መሆኑን ይገልጻሉ። አሉታዊ ግጭት ደግሞ በግጭቱ የተሳተፉት አካላት ግጭቱ በሚያስከትለው ውጤት በጣም የሚጎዱበት ወይም ተጠቃሚ የማይሆኑበት የግጭት ዓይነት መሆኑን ያስረዳሉ።

በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ሰዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ደረጃ አንጻር ጎናዊ ግጭት (Horizontal Conflict) እና ተዋረዳዊ ግጭት (Vertical Conflict) በማለት ይመድቧቸዋል። Deusdendit (2003 ፡ 2) ጎናዊ ግጭት የሚባለው በተመሳሳይ ማህበራዊ ደረጃ ላይ በሚገኙ በመካከላቸው የሃብት ፣ የስልጣን ፣ የዘር የበላይነት በሌለባቸው ግለሰቦችና ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው። ተዋረዳዊ ግጭት ደግሞ ማህበራዊ ደረጃቸው በተለያየ ሰዎችና ቡድኖች መካከል ወይም የበላይ እና የበታች ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው።

እንዲሁም Allowood (1993 ፡ 2-3) ደግሞ የግጭት ዓይነቶችን የተዳፈነ ግጭት (Latent conflict) ፣ ግልጽ ግጭት (Overt conflict) እና ድብቅ ግጭት (Covert conflict) በማለት ይከፍሏቸዋል። የተዳፈነ ግጭት በሁለት ወገኖች መካከል የሚያጋጥም ሲሆን ሁለቱም ወገኖች ግን ሁኔታው ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል ብለው አያስቡም። ግልጽ ግጭት ደግሞ ሁለቱም ወገኖች የሚጋጩበትን ጉዳይ አውቀው ወደ ግጭት ሲገቡ የሚፈጠር ግጭት ሲሆን ድብቅ ግጭት ደግሞ አንድ ወገን ስለ ጉዳዩ ምንም ፍንጭ ሳይኖረው በሌላ ወገን የሚፈጸምበትን ጥቃት መነሻ በማድረግ የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው።

2.2.2 የግጭት መንስኤዎች

Fisher (1982 ፡ 1) ለግጭት መንስኤ ናቸው ብለው የጠቀሷቸው ሦስት ነገሮችን ነው። እነርሱም የኢኮኖሚ ግጭት ፣ የስልጣን ግጭት እና የእሴት ግጭት ናቸው። የኢኮኖሚ ግጭት የሚባለው የማይገኙ ፣ ብርቅ እና ውድ እቃዎችን ለማግኘት ሲሉ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ወደ ግጭት የሚገቡበት ሁኔታ ነው። የስልጣን ግጭት የሚባለው ደግሞ አንዱ ቡድን በሌላው ቡድን ላይ የስልጣን የበላይነትን ለማሳየት ሲጥር ሲሆን የእሴት ግጭት የሚባለው በአመለካከት ፣ በአኗኗር ብልሃት (ስልት) ፣ እንደዕምነት በሚወስዷቸው ምርጫዎች ፣ መርሆዎች እና ተግባሮች አለመጣጣም ሲኖር ወደ ግጭት የሚገቡበት ሁኔታ ነው። ለግጭት መቀስቀስ መንስኤ ወይም ቀስቃሽ የሚሆኑ

በርካታ ምክንያቶች አሉ። እነዚህን ምክንያቶች በርካታ ምሁራን በጥናታዊ ጽሁፋቸው ገልጸዋቸዋል። የሁሉም ሃሳብ በአጠቃላይ ሲታይ ስነልቦናዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ገጽታዎች ያላቸው መሆኑን ማወቅ ይቻላል።

Kreidler የግጭት መንስኤዎችን በዋናነት በሦስት ይከፍሏቸዋል። እነርሱም፦

1. **የሃብት ክፍፍል**

ይህ ግጭት ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ አቅርቦት በሌለበት ወቅት (የመሬት ፣ የውኃ ፣ የገንዘብ ...) ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በሚያደርጉት ፍጥጫ የሚፈጠር የግጭት ዓይነት ነው። ሰዎች መሰረታዊ መብታቸው ፣ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው ሳይሟላ ሲቀር የጎደለውን ነገር ለማግኘት ሲሉ የሚፈጠር ግጭት ነው። የሰው ልጅ አካላዊ ፣ ስነ ልቦናዊና ማህበራዊ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ካልተሟሉና ትኩረት የማይሰጣቸው ከሆነ ግጭትን ሊቀሰቅሱና ወደ ብጥብጥ ሊያመሩ እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው።

2. **የፍላጎት አለመጣጣም**

አንድ ነገር የማድረግ ወይም የማግኘት (ስልጣን ፣ እድገት ፣ ለውጥ ...) ጽኑ ፍላጎት ኖሮ የተፈለገው ነገር በሌላ አካል ሲያዝና ትኩረት ሲነፈግ የፍላጎት መጣረስ በሚኖርበት ወቅት የሚፈጠር ግጭት ነው። በሌላ በኩል ፍትሃዊነት የሌለው የፖለቲካ መዋቅር ፣ ህጋዊ ሰውነትና የህዝብ አሜኔታ የሌለው አገዛዝ ፣ ደካማ አስተዳድር እና ስርዓት አልበኝነት የሰፈነበት ወይም መልካም አስተዳደር የሌለው አሰራርን መከተል ግጭትን ሊፈጥሩ ይችላሉ።

3. **የእሴቶች ግጭት**

የአንድ ማህበረሰብ እምነቶች ፣ ባህሎች ፣ እሴቶች ፣ አመለካከቶች በውስጥም ሆነ በባእድ አካላት ሲጣሱ የሚፈጠር ግጭት ነው። በብሄርተኝነት ፣ በዘረኝነት ፣ በጎሰኝነት ምክንያቶች አንደኛው ወገን ሌላውን ወገን ከማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ለሌችም ነገሮች ዙሪያ የመብት መንፈግና የማግለል ሁኔታ ሲከሰት የሚመጣ ግጭት ነው። ይህም በበቀል ፣ በጥላቻና በጠርነት ላይ ስለ ሚያተኩር በዓለማችን ላይ ለሚደርሱት የንብረትና የሰው ልጅ እልቂት

ምክንያት የሚሆን ነው። ይህ የግጭት ዓይነት ውስብስብ በመሆኑ በቀላሉ እልባት ለመስጠትም ሆነ ለመቆጣጠር የሚያስቸግር ነው። Kreidler (1984)

2.2.3 የግጭት አፈታት ዘዴ

ግጭት እንደየዓይነቱና ባህርይው የተለያዩ የመቆጣጠሪያ እና የማርገቢያ እንዲሁም እልባት የመስጫ መንገዶች አሉት። አንድ ማህበረሰብ በውስጡ የሚከሰቱትን ግጭቶች የሚያስወግድባቸው የራሱ የሆኑ ሥርዓቶች ፣ ህግና ደንቦች እንዲሁም ሂደቶች ይኖሩታል። እነዚህንም ግጭቶች እንደየዓይነታቸው በመለየት ለየግጭቶቹ ይበጃሉ የሚሏቸውን መፍትሔዎች ለመስጠት ግጭቶችን የሚያስወግዱባቸው ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ይኖሯቸዋል። በመሆኑም ማኅበረሰቡ ከራሱ የፈለቁ የግጭት አስወጋጅ አካላት በሚሰጡት ብያኔ ይተዳደራል።

የዘርፉ ምሁራን የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በተመለከተ ከዘዴዎቹ ዓይነት ፣ ዘዴዎቹ መሰረት ከሚያደርጉት ህግና ደንብ ፣ ከአስታራቂዎቹ ሚና ከታራቂዎቹ ሚና እና ከውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱ አንጻር የተለያዩ መንገዶች መኖራቸውን ይጠቁማሉ። Mitchell (2003 ፡ 75) በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ በግጭቱ የተሳተፉት ወገኖች ከሚወስዱት አቋም በመነሳት ሊቀርቡ የሚችሉት የመፍትሄ ሃሳቦች አምስት መሆናቸውን ይገልጻሉ። እነርሱም ጥሎ ማለፍ (Compeing) ፣ መቀበል (Accmodating) ፣ መተባበር (Collaborating) ፣ ማስወገድ (Avoiding) እና መደራደር (Compromising) ናቸው። ሌሎች የዘርፉ ምሁራን በግጭት አፈታቱ ላይ ከሚሳተፉ አካላት ማንነት እና ከሚያከናውኗቸው ተግባራት በመነሳት የግጭት አፈታት ዘዴዎችን ድርድር (Negotiation) ፣ ሽምግልና (Mediation) ፣ እርቅ (Arbitration) እና የህግ ድንጋጌ (Adjucation) በማለት ይከፋፍሏቸዋል። Jeong (2000 ፡ 168-177) ፣ Augusburger (1992 ፡ 192-194) ፣ Shaw (1997 ፡ 720)

ድርድር ፡- ድርድር የግጭቱ ተሳታፊ ከሆኑት ወገኖች ሌላ ተጨማሪ የሶስተኛ ወገን እገዛ ሳያስፈልግ ግጭቶች የሚፈቱበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው።

በድርድር የግጭት አፈታት ዘዴ አጠቃላይ ድባብ የጥላቻ ወይም የትብብር መንፈስ ሊሰፍንበት የሚችል ሲሆን ስምምነት ላይ መድረስ የሚቻለውም ሆነ የግጭቱ ተጣይነት የሚወሰነው በግጭቱ ተሳታፊ በነበሩት ወገኖች ፈቃደኝነት ነው። ሆኖም ግጭቱ ውስብስብ ከሆነና በተለይም በግጭቱ ተሳታፊዎች መካከል ስሜታዊነት አይሎ ጥሉ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰና መግባባት ከጠፋ ይህንን የግጭት አፈታት ዘዴ ተጠቅሞ ግጭትን መፍታት አዳጋች እንደሚሆን እንረዳለን። በዚህ ዘዴ የሚገኘው ውጤት እንደተደራዳሪዎች ፈቃደኝነት ሊለዋወጥ ይችላል።

ሽምግልና ፡- ሽምግልና የግጭቱ ተሳታፊ ከነበሩት ወገኖች በተጨማሪ ፈቃደኛና ሁሉንም ጠበኞች በእኩል ዐይን የሚመለከት ሦስተኛ ወገን (ሽማግሌ) በድርድሩ እና በግጭት አፈታት ሂደቱ ውስጥ በመገኘት የግጭቱ ተካፋይ ወገኖች ግጭታቸውን እንዲፈቱ እገዛ የሚያደርጉበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። ሆኖም ሽማግሌዎቹ የሚያቀርቡትን ሃሳብ ሁለቱም የግጭቱ ተካፋይ ወገኖች እንዲቀበሉ የማስገደድ ስልጣን የላቸውም። በሽምግልና የግጭት አፈታት ዘዴ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሁለቱ (በግጭት ውስጥ የተሳተፉ ወገኖች) ፈቃደኝነት የግድ ቢሆንም ፤ በመፍትሔ ፍለጋ ሂደቱ የሁለቱም የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ተሳትፎ የጎላ ስለሆነ አጠቃላይ ድባቡ የትብብር መንፈስ የሚታይበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ ብዙውን ጊዜ የሚገኘው ውጤት ሁለቱም ወገን ተጠቃሚ የሚሆኑበት ነው።

እርቅ ፡- እርቅ የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች የግጭታቸውን መነሻ ምክንያት እራሳቸው በጋራ ስምምነት ለመረጧቸው ወይም ተስማምተው መምረጥ ባልቻሉበት ጊዜ በፍትህ አካላት የሚወከሉና ሁለቱንም ወገኖች ያለ አድሎ ያገለግላሉ ተብለው ለሚታመንባቸው የቤተ ዘመድ የሽምግልና ዳኞች በማቅረብ የሚሰጠውን ውሳኔ እንዲቀበሉ የሚደረግበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። ሆኖም በእርቅ የግጭት አፈታት ዘዴ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ስለማይሆን ቅር የተሰኘ ወገን ወደ ፍርድ ቤት የመሄድ መብት አለው። የእርቅ የግጭት አፈታት ዘዴ አጠቃላይ ድባብ በጥላቻ መንፈስ የተሞላ ሲሆን በመፍትሄ ፍለጋ ሂደቱ የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ተሳትፎ የተገደበ ነው። በዚህ

ዘዴ የሚገኘው ውጤትም ብዙውን ጊዜ አንድን ወገን ተጠቃሚ ሌላውን ወገን ተጎጂ የሚያደርግ ነው።

የህግ ድንጋጌ ፡- የህግ ድንጋጌ የግጭቱ ተሳታፊ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ ወይም በሌላው ወገን አቤቱታ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል (ፍርድ ቤት) ቀርቦ ይኸው ህጋዊ አካል ውሳኔ በመስጠት ግጭቱ መፍትሔ እንዲያገኝ የሚደረግበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። የዚህ ዘዴ አጠቃላይ ድባብ የጠላትነት መንፈስ የሰፈነበት ሲሆን መፍትሔ በመፈለጉ ሂደት ላይም የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ቀጥተኛ ተሳትፎ የተገደበ ነው። በመሆኑም የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች በፍትህ አካላቱ የሚሰጠውን ማንኛውም ውሳኔ እንዲቀበሉ የሚገደዱበት የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። በህግ ድንጋጌ የሚገኘው ውጤትም አንዱ ወገን ተጠቃሚ ሌላው ወገን ተጎጂ የሚሆንበት ነው።

አንዳንድ የዘርፉ ምሁራን የግጭት መፍቻ ዘዴዎቹ መሰረት ከሚያደርጉት ጉዳይ በመነሳት የግጭት አፈታት ዘዴን ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ፣ ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴ እና ሃይማኖታዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በማለት ይከፋፍሉታል። ፡ Assefa (2001 ፡ 37-39)

2.2.3.1 ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴ

ከመንግስት መዋቅሮች ጋር ተያያዥነት ያለው ነው። ዘመናዊ የግጭት መፍቻ በህግ ባለሙያዎች የረቀቀ ፣ ከተለያዩ አገራት የተገኙ ልምዶች የተካተቱበት ፣ በጽሁፍ የሰፈረ እና በበላይ ምክር ቤቶች የጸደቀ ፣ ለተግባራዊነቱም በዳኝነት (በህግ ሙያ) የሰለጠነ የሰው ሃይል የሚመደብበት እና በአንድ አገር ውስጥ በአንድ ዓይነት ሁኔታ የሚያገለግል ለሁሉም ሰው (ማህበረሰብ) የሚሰራ ነው።

2.2.3.2 ሃይማኖታዊ የግጭት አፈታት ዘዴ

ሃይማኖታዊ የግጭት አፈታት ዘዴ የሚባለው መሰረቱን በታወቁ የዓለም ሃይማኖቶች ወይም በተለያዩ አገር በቀል እምነቶች ላይ ያደረገ የግጭት አፈታት ዘዴ ነው። በእስልምና ሃይማኖት የትዳርን ፣ የፍችን እና የውርስን ጉዳይ የሚመለከተው የሸሪያ ህግ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

2.2.3.3 ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ

ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ የአንድ ማህበረሰብ አባላት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰት ማንኛውም ዓይነት ግጭት ለመፍታትና የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ የሚገለገሉበት ዘዴ ነው። ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ የጽሁፍ መሰረት የሌለው ፣ በቃልና በመከወን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የማህበረሰቡ መንፈሳዊ ሃብት ነው።

በርካታ የዘርፉ ምሁራን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ ግጭትን ለመፍታት ከሚፈጀው ጊዜ ፣ ግጭቱን ለመፍታት ከሚጠይቀው ገንዘብ ፣ ለተቀናቃኞቹ አካላት ከሚሰጠው ነጻነት ፣ ካለው ግልጽነት ፣ ሦስተኛ ወገኖቹ ግጭትን ለመፍታትና ዘላቂ ሰላምን ለማምጣት ካላቸው ብቃት አንጻር ሲታይ ከዘመናዊ የግጭት መፍቻ ስልት የተሻለ እንደሆነ ይናገራሉ።

Beneman (2007 ፡ 137) ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስልት ከህገ መንግሥታዊ የግጭት መፍቻ ስልት የተሻለ አማራጭ ነው። ምክንያቱም ደግሞ በዝቅተኛ ወጪ እና በከፍተኛ ፍጥነት ውጤታማና ዘላቂ መፍትሔ ማስገኘቱ እንደሆነ ያስረዳሉ። Pendergast (2004 ፡ 405) የአጥቢያ ሽምጋዮች (Local Mediators) ከማህበረሰቡ ጋር አብረው የኖሩ በመሆናቸው ግጭቱን ለመፍታት የሚያስችል ከዘመናዊ ዳኞች የበለጠ እውቀት እንዳላቸውና ግጭቱንም ከመሰረቱ ማጥናት እንደሚችሉ ይገልጻሉ። Sills (1968 ፡ 241) ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስልት ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ በመጣ ተቋማዊ እምነት በተለምዶ የአፈጻጸም ስርዓት የሚከናወን በመሆኑ ውጤታማነቱና ተቀባይነቱ የላቀ መሆኑን ያብራራሉ ። Assefa (2001 ፡ 387) ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ ግጭቱን ለመፍታት የተጻራሪ አካላቱን ድርድር እና የሦስተኛ ወገንን ዳኝነት ሊያጠቃልል እንደሚችል ያስረዳሉ።

በተጨማሪም Webel እና Galtung (2000 ፡ 54) የተባሉ የመስኩ ምሁራን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስልት የሚከተሉት ፋይዳዎች እንዳሉት ያስረዳሉ ።

- በባላጋራዎች (በተጋጭዎች) መካከል ሙተማመን ያለው መግባባትን ያዳብራል።

- ተሸማጋዮች የየባላንጣዎቻቸውን ስሜት በውል እንዲረዱት ስለሚያደርግ ወደ ፊት በሚኖራቸው ግንኙነት ስሜታቸውን ጠብቀው ለመኖር ያስችላቸዋል፡፡
- የተደራዳሪ ወገኖች ሃሳብ ተቀባይነት ስለሚያገኝ በእኩልነት ተስተናግደናል የሚል ስሜት ያድርባቸዋል ፤ በራስ የመተማመንን መንፈስ ያበለጽጋል ፡፡
- ከተደራዳሪ ወገኖች ጀርባ ያሉ ወገኖቻቸው ጭንቀት እና የግጭት ስሜት ስለሚቀንስ ሀሴት ይሰማቸዋል ፡፡
- ከመደበኛው ፍርድ ቤት በተለየ መልኩ ውጤቱ ምክንያታዊ እና ፍትሃዊ ይሆናል ፡፡ ስለሆነም ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ከዘመናዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በተሻለ ሁኔታ ተመራጭ ያደርገዋል ፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የግጭት መፍቻ ዘዴ ለመጠቀም የግጭቶቹን ዓይነትና መንስኤ ማወቅ በጣም ጠቃሚ እንደሆነ Sechellenberg (1996 : 13) ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ እንደግጭቶቹ ዓይነት ፣ እንደ ተቀናቃኞቹ አቋም ፣ እንደመነሻ ምክንያታቸው እና እንደየ ግጭቶቹ ሁኔታ ተስማሚ የሆነውን ዘዴ መጠቀም ይገባል፡፡

2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህ ጥናት ‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት በቅማንት ማህበረሰብ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ ተዛማጅነት ያላቸውን ስራዎች ቃኝቻለሁ፡፡ የተዛማጅ ጥናቶችን ቅኝት ያካሄድኩት በሦስት አግባብ ነዉ፡፡ አንድም አጠቃላይ ኢትዮጵያ ዉስጥ በተለያዩ ብሄረሰቦች ላይ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓትን መሰረት አድርገዉ የተጠኑ ጥናቶች በምን መንገድ ተጠንተዋል የሚለውን ለማወቅ ፤ አንድም እኔ የምሰራበት ማህበረሰብ በአማራ ክልል የሚገኝ እንደመሆኑ በአማራ ክልል ተመሳሳይ የሆነ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ይከናወናል? ወይስ የተለያየ ነዉ? የሚለውን ለማወቅ ፤ አንዲሁም ጥናቱ በሚካሄድበት ማህበረሰብ ዙሪያ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን ይዘዉ የተሰሩ ጥናቶችን ተተኳሪ በማድረግ ነዉ፡፡

ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረቡ 4 ያህል ጥናቶችን እቃኛለሁ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ጥናቶቹ ከእኔ ዓላማ ጋር ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ እና ከእኔ በፊት በተደረጉ ጥናቶች ስላልተቃኙ ነው፡፡ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዙሪያ የተጠኑ ሁለት ጥናቶችንና በአማራ ክልል ከተጠኑ ውስጥ ሦስቱን ቃኝቻለሁ፡፡

ስለሺ አባተ ‹‹ የሸካኛ ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ›› በሚል ርዕስ በ2002 ዓ.ም ጥናት አቅርቧል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ብሄረሰቡ ግጭቶችን የሚፈታባቸውን ሾቦ እና ሾቶ ባህላዊ ተቋማት መግለጽ እና አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች የሚጫወቱትን ሚና ማሳየት ነው፡፡ ስለጥናቱ ምንነት ፣ ስለማህበረሰቡ ማህበረ-ባህላዊና አካባቢያዊ ዳራ ፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት አብራርቷል፡፡ ማህበረሰቡ ስለ ግጭት ያለው ዕሳቤ ፣ በብሄረሰቡ የሚታዩ መንስኤ ግጭቶች ፣ የብሄረሰቡ የመፍተሄ ማፈላለጊያ ተቋማት እና የተለያዩ የአውድ ክዋኔዎች እንዲሁም በቀረቡት አውዳዊ ክዋኔዎች ግጭት ውስጥ ገብተው በባህላዊ መንገድ የታረቁ ወገኖች ስላገኙት ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊና ስነልቦናዊ ፋይዳዎች ተንትኗል፡፡ የብሄረሰቡ ዕድሜ ጠገቦች በሽምግልና ወቅት ስለሚጠቀሙባቸው አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችና ክዋኔዎቻቸው ፣ እንዲሁም ግጭትን በመፍታት ረገድ ቃልቻ ፣ እርግማንና የብሄረሰቡ ሴቶች ስላላቸው ሚና ፣ ብሄረሰቡ በተለያዩ የእርቅ ስርዓቶች ላይ የሚናገሯቸውን ስነ ቃሎች በቃለመጠይቅ በመሰብሰብ ገለጻ አድርጓል፡፡መረጃዎችን ምልከታ እና ቃለመጠይቅ በማድረግ የሰበሰበ ሲሆን በገላጭ እና በይዘት ትንተና የማቅረቢያ ስልቶች ተንትኗል፡፡

የጥናቱ ግኝት ከነዚህ ሁለት ተቋማት ውጭ እንደ ከዋ ፣ ፊቾ ፣ ማራዮ ፣ ማሬጮ ፣ ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉ አማራጭ የግጭት መፍቻ ተቋማት መኖራቸውን ማሳወቁን ፣ ባህላዊው ተቋም ጊዜና ወጪን ቆጣቢ በመሆኑ ከዘመናዊው የፍትህ ተቋም የተሻለ እና ተመራጭ መሆኑን ፣ እንዲሁም ባህላዊ ተቋሙ ማህበረሰቡ

የሚደርስበትን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ችግሮች እንደሚያቃልል በጥናቱ ጥቆማ አድርጓል።

ሃፍታይ ገ/እግዚአብሄር ‹‹ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሄረሰብ ›› በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም ያቀረበው ጥናት ዋና ትኩረት በኩናማ ብሄረሰብ የሚከናወነውን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት እና የሚኖረውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳወቅ ፣ እንዲሁም አስታራቂ ሽማግሌዎቹ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመፍታት ምን ዓይነት ስልት እንደሚጠቀሙ እና ባህላዊ የግጭት አፈታት ሂደቱ ምን እንደሚመስል መተንተን እና መግለጽ ላይ ነው። ጥናቱ በዋናነት በግድያ የግጭት አፈታት ስርዓት ላይ ተወስኖ የቀረበ ነው። የግድያ ግጭትን የሚያስነሳው ምክንያት የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት ከኢኮኖሚ ጥቅም ጋር የተሳሰረ እንደነበር ፣ የክርስትናን ሃይማኖት ከተቀበሉ በኋላ ደግሞ ‹‹ በትዳር ላይ መወሰለት ›› ዋነኛው የግጭት መንስኤ እንደሆነ አመልክቷል። በተጨማሪም ቀላል የሚባሉ ግጭቶችን የሚፈቱት የሀገር ሽማግሌዎች ‹‹ ላጋኬ ›› እንደሚባሉ ፣ ከበድ ያሉ እና እንደ ግድያ ዓይነት ግጭቶችን የሚፈቱ የሀገር ሽማግሌዎች ደግሞ ‹‹ ሰንጋኔና ›› እንደሚባሉ ገልጿል።

የኩናማን ብሄረሰብ የግጭት ብያኔ ፣ ዋና ዋና የግጭት መነሻ ምክንያቶች እና ባህላዊ የእርቅ ስርዓታቸው ምን እንደሚመስል ጥናቱ አሳይቷል። የብሄረሰቡ አባላት በባህላቸው እና በእምነታቸው መሰረት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተረካከቡ ያመጡትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ከዘመናዊው ፍርድ ቤት በበለጠ እንደሚመርጡት እና እንደሚያምኑበትም በጥናቱ ታይቷል። በተጨማሪም በባህላዊ የእርቅ ስርዓት የታረቁ የብሄረሰቡ አባላትም ተሳስበው እና ተከባብረው እንዲኖሩ ተቋመ እንደሚያስገድዳቸው ጥናቱ ጠቁሟል።

ሃፍታይ ጥናቱን ባካሄደበት ማህበረሰብ ውስጥ ተፈጥሯዊ መቼት በማጣቱ በቅንብር ተፈጥሮ መቼት ለመጠቀም ደግሞ ብሄረሰቡ ‹‹ ሚርት እና ማርክስ ›› በሚሉ ሁለት ምክንያቶች ስለከለከሉት ፣ ምልከታ አለማካሄዱን እና መረጃ

የሰበሰበው በቃለመጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መሆኑን ጠቅሷል። አጥኚው ምልከታን ባለማካሄዱ የክዋኔዎቹን ትዕምርታዊ ትርጓሜ ለመተንተን ፣ ተቋማቱ የሚኖራቸውን ፈርጀ ብዙ ፋይዳዎች ለማወቅ እና ለአንባቢም ለመግለጽ አልቻለም። እንዲሁም አጥኚው ስራው ተአማኒነት እንዲኖረው በትክክል በቦታው ተገኝቶ ቃለመጠይቅ ማድረጉን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን (ፎቶ ግራፎችን) አላቀረበም። የጥናት ዘዴውን እና የማቅረቢያ ስልቱን አልገለጸም።

በ2003 ዓ.ም በ ለታሪክ ተሾመ ‹‹ የባሌ ኦሮሞ የግጭት አፈታት ›› በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ዋና ዓላማ የባሌ ኦሮሞዎች እርስ በእርስም ሆነ ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈጠሩ ግጭቶችን የሚፈቱበትን ባህላዊ ስርዓት ማሳየት ነው። ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በምልከታ በቃለመጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃዎችን ሰብስቧል። መረጃዎችን የማቅረቢያ ስልቱ ገላጭ እና የይዘት ትንተና ነው።

ለታሪክ በጥናቱ ውስጥ በአብዛኛው ግጭት የሚከሰትባቸው ምክንያቶች ከእርሻ እና ከከብት ማርባት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ፣ ማህበረሰቡ የግድያ ግጭት ዓይነቶችን በግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት አካላት ማንነት በመነሳት በቤተሰብ ውስጥ ፣ በዘመድ መካከል ፣ በጎሳ ውስጥ ፣ በጎሳዎች መካከል እና ኦሮሞ ካልሆኑ ህዝቦች ጋር የሚደረግ በማለት በአምስት እንደሚከፋፍሉ ገልጿል። ለግድያ ግጭት የሚከፈለው ጉማ (ካሣ) እንደ ግድያው ሁኔታ ፣ እንደ ተጋጪዎቹ ማንነት ፣ እንደ ሟች ፆታ የተለያየ እንደሆነና የሚከፈለው ጉማም እንደየዘመኑ ሁኔታና እንደ ማህበረሰቡ የገቢ ምንጭ በሞት ፣ በመሬት ፣ በከብት እና በገንዘብ እንደ ነበር በጥናቱ አሳይቷል። የሚከፈለው ጉማ በግድያው ሁኔታ ላይ በመመስረት ‹‹ አኮኮ ›› ፣ ‹‹ ሀምቢሳ ›› እና ‹‹ ረፈሳ ›› እንደ ሚባሉ ፣ ግጭትን ለመፍታት የሚያገለግሉት ተቋማትም የሃገር ጀርሳ ፣ ቢያ እና ራያ አምባ እንደሆኑ ገልጿል።

ማህበረሰቡ ለግድያ ግጭት ባለው አመለካከት የግድያ ግጭት መከሰት አይገባውም ከተከሰተም በፍጥነት መፍትሄ ማግኘት አለበት እንደሚልና ፣

ባህላዊው የግድያ ግጭት መፍቻ ተቋም ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነልቦናዊ ፋይዳዎች እንዳሉት አመልክቷል።

በአንዱዓለም አባተ በ2004 ዓ.ም ‹‹ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በመኤኒት ብሄረሰብ›› በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ዋና ዓላማ በመኤኒት ብሄረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ አቢይ ግጭቶችንና መንስኤዎቻቸውን መግለጽ እና የሚቀርቡትን የግጭት ዓይነቶችና ውሳኔያቸውን ማሳየት ነው። ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ምልከታ ፣ ቃለመጠይቅ እና የቡድን ውይይት በማድረግ መረጃዎችን የሰበሰበ ሲሆን የማቅረቢያ ስልቱም ገላጭ ነው።

አጥኚው በጥናታዊ ጽሁፉ በብሄረሰቡ ብዙ ጊዜ የሚነሱት ግጭቶች ሰው መግደል ፣ የሰው ሚስት መድፈር ፣ የድንበር መጋፋት ፣ የገንዘብ መካካድ ፣ የጎሳ ጸብ እና የብሄረሰብ ጸብ መሆናቸውን አሳይቷል። የጸቦቹ መነሻ ምክንያትም ስካር ፣ አንዱ ያጫትን ሴት ሌላው መንጠቅ ፣ ቀብር ላይ በሚደረግ ጭፈራ የሚነሳ ድንገተኛ ጸብ ፣ የቆየ ቂምን አስታውሶ አመቺ ቦታ ሲገኝ ጥቃት መፈጸም እና ስርቆት እንደሆኑ ጠቁሟል። እነዚህ ግጭቶች የሚፈቱባቸው ተቋማት ኮሞሩት (ባላባት) ፣ ፕራይ (ቃልቻ) እና የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚባሉ እና በእነዚህ ተቋማት ስር ሰው የመግደል እርቅ ስነ ስርዓት ሂደት (አሻ) ፣ ሴቶችን የመድፈር እርቅ ስነ ስርዓት ሂደት (ማጠብ) እና የድንበር እርቅ ስነ ስርዓት ሂደት እንደሚቀርብበት አሳይቷል።

በጥናቱ ግኝትም ባህላዊው የፍትህ ስርዓት ቂምና በቀልን አጥፍቶ ዘላቂ ሰላምና መተማመንን ማምጣት መቻሉን ፣ በአንጻሩ ደግሞ መደበኛው ፍርድ ቤት ይህን ማድረግ አለመቻሉን ፣ ባህላዊው የፍትህ ስርዓት ለህብረተሰቡ ማህበረሰባዊ ፣ ሞራላዊና ስነልቦናዊ ጥቅሞችን በመስጠት ከፍ ያለ ቦታ እንዳለው ፣ እንዲሁም የባህላዊውን እና የዘመናዊውን የፍትህ ተቋማት ጥንካሬ እና ድክመት አሳይቷል።

የአንዱዓለም ጥናት ፎክሎር ቢሆንም ለፎክሎራዊ ጉዳዮች ትኩረት አልሰጠም። ለምሳሌ ፦ የእርቅ ማጽኛ ስርዓቱ ላይ የሚፈጸሙ ክዋኔዎችን

ትዕምርት እና ፋይዳ መግለጽ ይገባው ነበር። እንዲሁም በእርቁ ክዋኔዎች ላይ የሚባሉ ሥነ ቃሎችንም ማካተት ነበረበት።

በአማራ ክልል ላይ ከተሰሩ አምስት ጥናቶች መካከል ሦስት ያህሉን ቃኝቻለሁ። ይህም የሆነበት ምክንያት ሁለቱን ጥናቶች (የዮሴፍ ጌትነትን እና የአበበ ዘውዴን) በቤተመጻህፍትም ሆነ በክፍለ ትምህርቱ ውስጥ ባለመገኘታቸው ነው። ከተቃኙት ሦስት ስራዎች መካከል የመጀመሪያው ጥናት በ1998 ዓ.ም በአየለ ፍቅሬ ‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ማህበረሰብ›› በሚል ርዕስ የተጠናው ጥናት ነው። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በባህር ዳር ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ነገዴዎች በመካከላቸው እና ከሌሎች ነዋሪዎች ጋር የሚፈጠረውን ግጭት እንዴት በባህላዊ መንገድ እንደሚፈቱ ማሳየት ፤ የግጭት መፍቻ ዜዴዎቻቸውን ማመላከት እና ፎክሎር በነገዴ ማህበረሰብ ውስጥ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ያለውን አስተዋጽኦ ማሳየት ነው። ይህ አጥኚ ምንም እንኳን መረጃዎችን ‹‹የማቅረቢያ ዘዴዬ ገላጭ ነው›› ቢልም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹን አልገለጸም ወይም የለውም ።

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን አላሳየም ። ባህላዊ የፍትህ ተቋማትን አልገለጸም ፤ የሚጠቀሙትን ስልት ፤ የሚሰጡትን ውሳኔዎች አልገለጸም። ተቋሙ ለማህበረሰቡ ያላውን ፋይዳ ፤ የደረሰበትን ድምዳሜ እና ጥናቱ ያስገኘውን ውጤት አልገለጸም። ከዓላማው ውስጥ አንዱ የሆነው ‹‹ ፎክሎር በነገዴ ማህበረሰብ ውስጥ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ያለውን አስተዋጽኦ ማሳየት›› የሚለው ዓላማ ታስቦበት የተቀረጸ አይመስልም። ምክንያቱም ፎክሎርን በማህበረሰቡ የፍትህ ተቋም ውስጥ ማሳየት ቀርቶ ቃሉን እንኳን አንድ ቦታ ላይ ሲጠቀም አለማየቱ ለዚህ እንደ ማስረጃ ይሆናል።

ሁለተኛው ደግሞ የዓለሙ ካሣዬ ‹‹ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ስርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ›› በሚል ርዕስ በ1999 ዓ.ም የተጠናው ነው። ጥናቱ በአማራ

ክልል ሰሜን ሸዋ አካባቢ የተካሄደ ነው። ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋና ዓላማ የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ህዝብን ጥንተ አመጣጥ ፣ አኗኗር ፣ እምነት ፣ ዓለማዊ አተያይ እና ግጭት የሚፈጠርበትን መንስኤና የሚፈታበትን ተቋም ፣ ስርዓት ፣ ዘዴ መመርመር እና መግለጽ ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎችን ‹‹ዕሞናዊ››እና አሳታፊ ምልከታ እና ቃለመጠይቅ በማድረግ ሰብስቧል። መረጃዎችን የማቅረቢያ ስልቶቹ ገላጭ እና ተንታኝ ናቸው።

በጥናቱ መሰረት ማህበረሰቡ ግጭት ውስጥ የሚገባባቸው ቋሚ እና ተለዋዋጭ ምክንያቶች አሉ። በቋሚ የግጭት ምክንያትነት የሚታዩት ውርስ ፣ የንብረት መጥፋት ፣ ፍቺ እና በጨዋታ መሀል የሚፈጠር አለመግባባት ሲሆኑ በተለዋዋጭ የግጭት ምክንያትነት የተጠቀሰው ደግሞ የክልሉ መንግስት አርሶ አደሮችን ‹‹ቢሮክራት ቅሪት ፣ ሃብታም ፣ መካከለኛ እና ደሃ›› በሚል ፈርጆ ያካሄደው የመሬት ሽግሽግ እና የይዞታ ቦታ መለዋወጥ ነው። ግጭቶቹም ሲፈጠሩ በተለያዩ ደረጃዎች በቤተሰብ ፣ በአካባቢ ሽማግሌዎች ፣ በሃይማኖት አባቶች እና በሀገር ሽማግሌዎች እንደሚፈቱ ፤ ከላይ በተጠቀሱት መንስኤዎች ምክንያት የሚፈጠሩትን ግጭቶች ማህበረሰቡ መለስተኛ እና ከባድ በማለት እንደሚፈርጃቸው ፤ እንደየደረጃቸውም የመፍትሄ ማስገኛ ተቋም የመጠቀም ልምድ እንዳላቸው ገልጿል።

የዓለሙ ጥናት ትኩረት የሆነው ደመኝነት (የደም ግጭት) ከእነዚህ መፍትሄ መስጫ ተቋማት መካከል የሀገር ሽማግሌዎችን እንደሚጠቀም እነዚህም ሽማግሌዎች ሲመረጡ ማህበራዊ ክበፊታ ፣ ሀቀኝነት እና የአስታራቂነት ጥበብ እንደሚያስፈልጉ ጠቁሟል። ግጭት ውስጥ ገብተው የታረቁ ሰዎች እርቅ የሚያጸኑት ጠመንጃ እየተራመዱ ፣ አፈር እየጨበጡ ፣ ሽንጥ ስጋ እየተቋረጡ ፣ እርጥብ ሳር እየነጩ ፣ መስቀል እየጨበጡ የመሃላ ቃል በመግባት መሆኑን አመልክቷል።

ይህ አዋጊ በጥናቱ ደጋግሞ እንደገለጸው የጥናቱ ትኩረት ደመኝነትና ደም መቃባትን ለማስቀረት የሚደረገውን ባህላዊ የደም እርቅ ስርዓት መግለጽ ሆኖ

እያለ ነገር ግን የጥናቱ ግኝት የሚገልጸው በመሬት ሽግሽጉ ሳቢያ አባቶች እና ልጆች ፣ ባሎች እና ሚስቶች ፣ እህቶች እና ወንድሞች ግጭት ውስጥ እንደሚገቡ ፤ ማህበረሰቡ እነዚህን ግጭቶች ለመፍታት ‹‹የአባት ዕድር ህግ›› ብሎ በሚጠራው ባህላዊ የፍትህ ተቋም እንደሚገለገል ነው፡፡

ይህ ግኝት አጥኚው ይዞት ከተነሳው ዓላማ አንጻር የሚጣረስ ወይም የዓላማውን ግብ ያልመታ ነው፡፡ (ምክንያቱም በጥናቱ በተጋጭዎቹ መካከል የስጋ ዝምድና በመኖሩ ደም የመቃባቱ ሁኔታ የለም ብሏልና) የግድያ ግጭት ስርዓቱንም ቢሆን በመግለጽ ላይ በማተኮሩ የተለያዩ የእርቅ ማጽኛ ዐውዶችን ትርጓሜ ፣ ትዕምርቶችን ፣ የተቋሙን ፋይዳ ፣ የመሳሰሉትን ትኩረት አልሰጠም፡፡ እንዲሁም የጥናታዊ ጽሁፉ ርዕስ ‹‹ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ስርዓት በላሎ-ማማ ምድር ወረዳ›› ሁኖ እያለ ይዞት የተነሳው ዋና ዓላማ ግን የላሎ-ማማ ምድር ወረዳ ህዝብን ጥንተ አመጣጥ ፣ አኗኗር ፣ እምነት እና ዓለማዊ አተያይን የሚያካትት ነው፡፡ በእርግጥ ይህንን መመልከቱ እንደ ስህተት ባይቆጠርም ፤ አቢይ ዓላማ ሊሆን ግን አይገባም፡፡

ሦስተኛው የብርሃኑ ቦጋለ ‹‹መሳል- ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በአንጸኪያ ገምዛ ወረዳ›› በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም የተጠናው ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋና ዓላማ የመሳልን መዋቅር ፣ የግጭት አፈታት ሂደት እና አጠቃላይ ገጽታ መግለጽ ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃዎች በምልከታ ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህን መረጃዎች በገላጭ እና በይዘት ትንተና የማቅረቢያ ስልቶች አቅርቧል፡፡

ከጥናቱ ለማወቅ እንደተቻለው ‹‹መሳል›› በባላጋራዎች (ጸበኞች) ምርጫ እና እምነት ላይ የተመሰረተ እርቅን የሚያስፈጽም ተቋም ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለግጭት በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል በዋናነት የቦታና የንብረት ውርስ ፣ ዕለታዊ ግጭት ፣ የብሄር ግጭት ፣ መስኖ እና ሴት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን እርቅ ከሚሰጥባቸው ግጭቶች ውስጥ አብዛኛውን የሚይዙት በድንገተኛ እና በዕለታዊ ጸብ የሚነሱ ግጭቶች እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህ ተቋም ስር ‹‹በሌ›› እና ‹‹ቤቱ ይፍታው›› የሚባሉ ሁለት ስልቶች እንዳሉ ፣ እነዚህም ስልቶች ድብቅ (ስውር) ለሆኑ የግጭት ዓይነቶች እንደሚያገለግሉ አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ተቋም ስር በግድያ ግጭት ላይ ሁለት ዓይነት ውሳኔዎች እንደሚተላለፉ (የቃል እና የጽሁፍ) ፣ የቃሉ ‹‹በሌ›› ሲባል የጽሁፉ ደግሞ ‹‹የእርቅ ሰነድ›› እንደሚባል አክሎ ገልጿል፡፡ በዚህ ተቋም እርቅ የሚፈጽሙ ተጋጭዎች እርቁን እንዳያፈርሱ ቀድመው የተደነገጉ ማህበራዊ እገዳዎች ያስገድዷቸዋል፡፡ በመጨረሻም ተቋሙ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ስነ-ልቦናዊ እና አስተዳደራዊ ፋይዳ እንዳለው እና የአረጋዊያንን ፣ የሴቶችን እና የህጻናትን መብት እንደሚያስጠብቅ ጠቁሟል፡፡

አጥኚው የግድያ ግጭት ስርዓቱ እንደ አስፈላጊነቱ ሁለት ጊዜ ሊካሄድ እንደሚችል ገልጿል፡፡ ነገር ግን ይህን ስርዓት ሁለት ጊዜ የሚያካሄድበትን ምክንያት ፣ ዓላማ እና ሂደት አላብራራም፡፡

እስካሁን የተቃኙትን ጥናቶች ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ ስንመለከት እንደ ጥናት ዓላማቸው የግጭትን ምንነት (ብያኔ) ፣ የግጭት መከሰቻ መንስኤዎችን ፣ የግጭት ዓይነቶችን እና የአፈታት ዘዴዎችን በስፋት ተመልክተዋል፡፡ ሁሉም አጥኚዎች በጥናታዊ ጽሁፋቸው ውስጥ የተጠቀሙትን ንድፈ ሃሳብ አልገለጹም፡፡ ነገር ግን ሙሉ ጥናቶቹ በጥንቃቄ ሲነበቡ ለጥናቱ የተጠቀሙት የንድፈ ሃሳብ መሰረቶች ይታወቃሉ፡፡ እንደ ርዕሳቸውና የጥናታቸው ዓላማ መቀራረብ አውዳዊ እና ተግባራዊ ንድፈ ሃሳቦችን ተጠቅመው ይገኛሉ፡፡

የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን በማጣመር ተጠቅመዋል፡፡ ነገር ግን የንድፈ ሃሳቦቹን ትኩረት በሚገባ ተከትለዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የአውዳዊ ትውር አቀንቃኞች የፎክሎር ቴክስት ከኮንቴክስት ተለይቶ መታየት እንደሌለበት ይገልጻሉ፡፡ የዚህ ትውር የመስክ ትኩረቶች የክዋኔ አውዶች ናቸው፡፡ ከላይ ከተቃኙት ጥናታዊ ጽሁፎች መካከል የሃፍታይ ገ/እግዚአብሔር ጥናት ይህንን አያሟላም፡፡ እነዚህም አውዶች ማህበራዊ እና ባህላዊ በሚል ይከፈላሉ፡፡ በእያንዳንዳቸው ስር ሶስት የአውድና የግንኙነት ደንቦች ይገኛሉ፡፡ ማህበራዊ

አውድ ሁኔታዊ አውድን ፣ ማህበራዊ መዋቅርን ፣ የገቢ ምንጭን (መተዳደሪያን) ይይዛል። ጥናቶቹ ከማህበራዊ አውድ ማህበራዊ አደረጃጀትን እና የኢኮኖሚ መሰረታቸውን በደንብ በስፋት ተመልክተዋል። ለሁኔታዊ አውድ ትኩረት አልሰጡትም። ለባህላዊ አውድም እንደዚሁ።

ተግባራዊ ጽንሰ ሃሳብን ሲመለከቱ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ ማህበረሰቡን እንደሚጠቅም ፣ ጊዜ እና ገንዘብን እንደሚቆጥብ ፣ የማህበረሰቡ አባላት ተስማምተው እና ተቻችለው እንዲኖሩ እንደሚያደርግ ፣ በመካከላቸውም የሚከሰት ማንኛውም ግጭት በሰላማዊ መንገድ እንደሚፈታ ገልጸዋል።

ስነቃል ግጭትን በመፍታት ረገድ ያለውን ሚና በገለጹበት ክፍል ‹‹ ስነቃል ግጭትን በመፍታት ረገድ ያለው ሚና ትንተና ›› ብለው ትንታኔያቸው ግን ስነቃሉ (ተረቱ ፣ ምሳሌያዊ ንግግሩ) የያዘውን ጭብጥ ይሆናል። ስነቃሉም ከመከሰቻ አጋጣሚው አንጻር አልተተነተነም። ክዋኔን በተመለከተ ቅድመ እርቅ ፣ በእርቅ ጊዜ እና ድህረ እርቅ ያለውን ቅደም ተከተል ከመግለጽ ባለፈ የክዋ ሁኔታ ሁነቶች [5]የሚያጠቃልላቸውን ሁሉንም ነገሮች በጥልቀት ተመልክተው የተተነተኑ ናቸው ለማለት አያስደፍርም። እንዲሁም የእነርሱ ስራዎች ከእነርሱ በፊት ከተሰሩት የሚለዩበትን ወይም ያመጡትን ለውጥ አልገለጹም።

በቅማንት ማህበረሰብ ላይ ከተጠኑ ጥናቶች መካከል ቀዳሚው የሰለሞን ሲሳይ ‹‹የቅማንት ብሂረሰብ የጋብቻ ስነ ስርዓት እና የሰርግ ግጥም ትንተና›› በሚል ርዕስ በ1998 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበው ነው። ይህ ጥናት ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎችን ታሳቢ አድርጎ የተጠና ሲሆን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚካሄደው የሰርግ ስርዓት ግንኙነታቸውን እንዴት ያጠናክረዋል? በሰርግ ስርዓቱ ላይ የሚደረደሩት ግጥሞችስ እንዴት ይገልጿቸዋል? የሚለውን በትንታኔ ማሳየት የመጀመሪያው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወደፊት በቅማንት ማህበረሰብ ላይ

[5] Event Of Performance Situation

ጥናት ለሚያከናውኑ አጥኚዎች ይህ ጥናት በምንጭነት እንዲያገለግል ማድረግ የሚሉ ናቸው። ስለ ማህበረሰቡ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ፣ ስለ ስነቃል ምንነትና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ፣ ከቅድመ ጋብቻ እስከ የሰርግ ስነ ስርዓት ያለውን ሂደት የሚገልጽ እና በሰርግ ወቅት የሚዘፈኑ የሰርግ ግጥሞች ትንተና የተደረገበት ነው።

አጥኚው መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ ፣ በምልከታ እና በጽሑፍ መጠይቅ የሰበሰበ ሲሆን መረጃዎችን የመተንተኛ ዘዴውን እና የማቅረቢያ ስልቱን አልገለጸም። በትንታኔ ክፍሉ ስለ ጋብቻ ምንነት ፣ ስለ ቅድመ ጋብቻ ዝግጅት ፣ በጋብቻ ወቅት ስለሚኖረው የተጋቢዎች ተግባር ፣ ስለውል አፈጻጸም እና በጋብቻ ወቅት ስለሚኖር ምልኪ አብራርቷል።

የዚህ አጥኚ ደካማ ጎኖች የመጀመሪያው ንድፈ ሳሃብ አላደራጀም ። ከጥናታዊ ጽሁፉ መገንዘብ እንደተቻለው አንዲት ሴት ከማግባቷ በፊት ‹‹ማንባር ቅጽ›› የሚባለውን ሃይማኖታዊ ስርዓት እንድትፈጽም ትገደዳለች። ሴቷ ይህን ስርዓት እንድትፈጽም የምትገደድበትን ሁኔታ ፣ በሰርግ ስርዓቱ ሂደት ወቅት በመሸራውና በመሸሪት እንዲሁም በቤተሰቦቻቸው ዘንድ የሚፈጸመውን እያንዳንዱን ክወና ትዕምርታዊ ፋይዳ አልገለጸም። ማህበረሰቡ የክብር ዘር ክብርን የይተንቲ ዘር ይተንቲን እንዲያገባ የማይፈቅድበትን ሁኔታ አልገለጸም ። ግጥሞቹን የተነተነው ከይዘት አንጻር ብቻ በመሆኑ ፍክሬያዊ ትርጉማቸውን ለማሳወቅ አላስቻለም ። እንዲሁም መረጃዎችን በፎቶ ግራፍ አላስደገፈም ። የጥናቱን ግኝት አልገለጸም ።

‹‹የቅማንት ማህበረሰብ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ›› በሚል ርዕስ በ2005 ዓ.ም የተጠናው የአብነት ሰለሞን ጥናት ዋና ዓላማ የቅማንት ማህበረሰብ የሚናገሯቸውን ዝርው የቃል ተረኮች ከሚነገሩበት ስፍራ ሰብስቦ ማንነትን ከመገንባትና ከመግለፅ አንፃር ያላቸውን ፋይዳ መተንተን ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካትም ማህበረሰቡ በብዛት ሠፍሮ ከሚገኝባቸው ሁለት ወረዳዎች (ላይ አርማጮሆና ጭልጋ) ውስጥ ከሚገኙ ስድስት ቀበሌዎች (ትክል ድንጋይ፣

ከርከር (ማንጌ)፣ አይክል፣ ተበርሚካኤል፣ ተንብራና አርሁና ጊዮርጊስ) የድምፅ ቀረፃ ፣ ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስቧል። በዚህ ጥናት ስር አስራ አንድ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናቶች ተዳሰዋል። ነገር ግን የማንነት ተረክን መሰረት አድርገው የተጠኑትን ብቻ እንጅ በቅማንት ማህበረሰብ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶችን አላካተተም። ስለ ማንነት ተረክም ቢሆን ርዕሰ ጉዳዩን በሚመለከት በርካታ የመጀመሪያ ዲግሪና የሶስተኛ ዲግሪ ማሚያ ፅሁፎች አሉ። ነገር ግን በዚህ ቅኝት ትኩረት የተሰጠው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናቶች ብቻ ነው።

ከጥናቱ ለማወቅ እንደተቻለው የቅማንት ማህበረሰብ በተረኮቹ የሚያነሳቸው ዋና ዋና የማንነት መገለጫዎች ሃይማኖትና ባህል ናቸው። ነገር ግን አጥኚው የህገ-ልቦና ሃይማኖት ፅሁፍ አልባ መሆኑን እና በዚህ ሃይማኖት ውስጥ እያንዳንዱ ስርአት የሚከናወነው በቃል ብቻ መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር በሃይማኖታዊ ስርዓቱ ወቅት የሚፈጸሙትን ክንዋኔዎች ትዕምርት አላየም። በአንጻሩ የቅማንትን ማህበረሰብ ባህላዊ ማንነት በተመለከተ ማህበረሰቡ ከአጐራባቾቹ ማህበረሰቦች በተለየ ምክንያት የሚያከብሯቸው በዓላት እንዳሉት ፣ እነርሱም ምዝጋናና ግበሩህ ፣ ሽምኩላ (ከረመይኪኩና) ፣ ዳኒቃ ፣ ዘመን መለወጫና ደመራ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ አሳይቷል።

ባህላዊ ማንነታቸው ውስጥ የገለጸው ሌላው ነገር የጋብቻ ሁኔታቸውን ነው። የጥናቱን ግኝቶች ሲገልጽም ተረኮቹ በማህበረሰቡ ውስጥ ማንነትን የመገንባትና የመግለፅ ተግባር እንዳላቸው ፣ በመሆኑም ማህበረሰቡ በሃይማኖቱና በባህሉ ከአጐራባቾቹ የማህበረሰብ ክፍሎች የሚለይበትን እንደሚያስረዱ ፣ ስለዚህ ተረኮቹ ማህበረሰቡ ከሌሎች አጐራባች ማህበረሰቦች የሚለይበትንና የራሱ መገለጫ የሆኑ ማንነቶቹን መገንቢያና ማንፀባረቂያ በመሆን እንደሚያገለግሉ ይገልጻል።

የእኔ ጥናት የቅማንት ማኅበረሰብን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶችና ክዋኔዎችን በመመርመሩ ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ አበይት የግጭት

ዓይነቶችን እና መንስኤዎቻቸውን በመግለጽ ፤ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓቱን አመሰራረት ፣ አወቃቀር እና የአሰራር ሂደት እንዲሁም የሚደነግጓቸውን ህግና ደንቦች በማሳወቁ ፤ በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቱ ላይ የሚቀርቡ የግጭት ዓይነቶችን እና የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች በመግለጽ ፤ ግጭትን በመከላከል ፣ በማብረድና በመፍታት ረገድ ያላቸውን ሚና በማሳየቱ ቅንት ከተደረገባቸው ጥናቶች የተለየ ያደርገዋል።

41

3 ማህበረ ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስለ ቅማንት ማህበረሰብ ማህበረ ባህላዊ ዳራ ትውውቅ ይደረጋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለማህበረሰቡ መገለጫ የሆኑ እንደ ቋንቋ ፣ ሃይማኖት ፣ የጋብቻ ሥርዓት ... ያሉ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ፡፡

3.1 የቅማንት ህዝብ አሰፋፈርና የሚኖርበት አካባቢ

ቅማንቶች ጎንደር ከተማን እንደቀለበት በመክበብ በአብዛኛው ከጎንደር ከተማ በስተሰሜን እና ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በተዘረጋው ሰንሰለታማ እና ኮረብታማ አካባቢ ይኖራሉ፡፡ በዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች በ8ቱ (በላይ አርማጭሆ ፣ በጭልጋ ፣ በወገራ ፣ በመተማ ፣ በቋራ ፣ በደንቢያ ፣ በጎንደር ዙሪያ ፣ በጎንደር ከተማ) እንዲሁም በሌሎች ወረዳዎች በአንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ በሌሎች ደግሞ በተወሰኑ ቀበሌዎች ብቻ ይገኛሉ፡፡

አካባቢው ደጋ ፣ ወይና ደጋና ቆላማ የአየር ንብረት የያዘ በመሆኑ ሁሉንም ዓይነት ሰብሎችና የቤት እንሰሳዎች ይገኙበታል፡፡ በአካባቢው በተለያየ አቅጣጫ ሂደው ሁሉም የአባይ ገባር የሆኑ ትልልቅ ወንዞች (አንገረብ ፣ ጓንግ ፣ ሳንጃ ፣ ሰቪያ ፣ ሸንፋ) እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

በአካባቢው አራት አውራ ጎዳናዎች የሚያልፉ ሲሆን አንደኛው ከአዘዞ ከተማ ተነስቶ በምዕራብ አቅጣጫ ከሱዳን ጋር የሚያገናኘው ክፍለ-አህጉራዊ መንገድ ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ከጎንደር ከተማ በመነሳት ወደ ሁመራ የሚዘልቀው መንገድ ነው፡፡ ሦስተኛው አህንም ከጎንደር በመነሳት ወደ ደባርቅና ሽሬ የሚወስደው ሲሆን አራተኛው ደግሞ ከጎንደር ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመነሳት ወደ አዲስ አበባ እና ደ/ታቦር የሚወስደው ነው፡፡ ከእነዚህ ዋና ዋና መንገዶች በስተቀር ወረዳን ከወረዳ ቀበሌን ከቀበሌ የሚያገናኝ መንገድ የለም፡፡

በ1987 ዓ.ም በኢትዮጵያ በተደረገው ህዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት የቅማንት ህዝብ ቁጥር 172,291 መሆኑ ከዚህ በፊት ተወስቷል። ከነዚህ ውስጥ 6,705 በከተማ ሲኖሩ የተቀሩት 165,586 ሰዎች ደግሞ በገጠር ይኖራሉ። በገጠር የሚኖረው ህዝብ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን በከተማ የሚኖረው ደግሞ በንግድና በመንግስት ሰራተኛነት ይተዳደራል።[6]

3.2 የቅማንት ማህበረሰብ ቋንቋ

Zelealem (2003) Hetzro 1969ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት የአገው ቋንቋ በሰሜን ምስራቅና በሰሜን ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍል በስፋት ይነገር ነበር። ከአገው ቋንቋዎች መካከል አንዱ የሆነው ቅማንትኛ ቋንቋም የቅማንት ህዝብ መግባቢያ ነበር። ምንም እንኳን ቋንቋው አሁን ባለበት ሁኔታ እየተዳከመ የመጣ ቢሆንም የቅማንትኛ ቋንቋ በአሁኑ ጊዜ በጭልጋ ዝቅተኛ ቦታዎች ውስጥ ባሉ መንደሮች የሚነገር እንደሆነ Zelealem (2003:31) ይገልፃሉ። ክመንትነይ (ቅማንትኛ) ቋንቋ በአሁኑ ሰዓት ብዙ ተናጋሪ የሌለውና ማህበረሰቡም ለጸሎት ስነ-ስርዓት ማስፈጸሚያ ብቻ የሚጠቀመውበት በመሆኑ ከመዳከምም አልፎ በመጥፋት ላይ ያለ ቋንቋ ነው።

Zelealem Leyew የቅማንትኛ ቋንቋ ሙሉ በሙሉ የጠፋ ሳይሆን በአደጋ ላይ ከሚገኙት ቋንቋዎች (Endangered Languages) መካከል አንዱ እንደሆነ ያስረዳሉ። ለዚህ አባባላቸው በአስረጅነት የሚዘረዝሯቸው ምክንያቶች :-

- ቋንቋው በቅማንት ህዝብ መካከል አይነገርም ፤ ቢነገርም ለተወሰነ አገልግሎት ማለትም ምስጢራዊ ንግግር እና ለቅዳሴ (ለጸሎት) ብቻ ነው።
- አብዛኛው የቅማንት ህዝብ የሚናገረው ቋንቋ ቅማንትኛ ሳይሆን አማርኛ ነው።
- ቋንቋውን የሚናገሩትም ቢሆን ከቅማንትኛ ይልቅ አማርኛን በጥራት ይናገራሉ።
- ቋንቋው የሚነገረው በአብዛኛው እድሜያቸው ከ50 ዓመት በላይ በሆኑ ሰዎች ነው በማለት ይዘረዝራሉ። Zelealem (2003)

[6] ይህ መረጃ የተገኘው በወረዳው ውስጥ ከሚገኝ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ነው።

ዋና ምክንያት የክርስትና እምነት መስፋፋትና የዘመናዊ ትምህርት መጀመር እንደሆነ Zelealem (2003 ፡ 37) ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም Zelealem (2003) Halevy (1887)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት በዳግማዊ ቴዎድሮስ ዘመን ትልልቅ ባለስልጣኖችና የጦር አመራሮች የነበሩት የቅማንት ማህበረሰቦች ስለ ነበሩ እና የቤተ መንግሥት ቋንቋ ይናገሩ ስለነበር ፖለቲካዊ ተሳትፎንም እንደ አንድ ምክንያት ይጠቅሳሉ፡፡ ይህን ጉዳይ Quirin (1977) ሲያጠናክሩ ቴዎድሮስን በሽፍትነት ወቅት ተቀላቅለው የነበሩት የቅማንት ማህበረሰቦች በኋላ ወደ ጦር አለቅነትና አስተዳደራዊ ማዕረግ እንደተሸጋገሩ በመግለፅ ነው፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ የቴዎድሮስ የጦር መሪ የነበረው የሬንሬሙቁ ተወላጅ ገልሙ ነበር፡፡ በዚህ መንገድ ወደ ፖለቲካዊ ጐራ መቀላቀላቸው በቤተመንግስት አካባቢ የሚነገረውን የአማርኛን ቋንቋ እንዲለምዱና እንዲገለገሉበት አድርጓቸዋል፡፡ እንደ 1994 የኢትዮጵያ ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ቅማንትኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚናገሩት 1,625 ሰዎች ሲሆኑ 3,450 ሰዎች ደግሞ በሁለተኛ ቋንቋነት ይግባቡበታል፡፡

3.3 የቅማንት ማህበረሰብ ሃይማኖት

የቅማንት ማህበረሰብ የእምነት ዓይነት አንዳንድ የብሄረሰቡ ተወላጆች ህገ-ልቦና ሲሉት ሌሎች ደግሞ የኦሪት እምነት ስርዓት ይሉታል፡፡ እምነቱ የሚመራው የሃይማኖትና የፖለቲካ ስርዓት አጣምሮ በሚይዘው ወንበር በሚባለው መሪ ሲሆን ሌሎች በቅዳሴ ስርዓቱ የሚሳተፉ ከሦስት እስከ አምስት የሚደርሱ ቀሳውስቶች ይገኙበታል፡፡

የህገ-ልቦና እምነት ተከታዮች እያንዳንዱ ስርአት (ቅዳሴው ፣ ፀሎቱ ፣ ምስጋናው ...) የሚከናወነው በቃል ነው፡፡ በዚህ እምነት ውስጥ ፅሁፍ የሚባል ነገር የለም፡፡ ይህ ጉዳይ ህገ-ልቦናን ፅሁፍ ካላቸው የእምነት ዓይነቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ የእምነቱ ተከታዮች የሃይማኖታቸውን ፅሁፍ አልባነት ምስጢር የሚያስረዱበት የቃል ተረክ አላቸው፡፡

በጥንት ጊዜ አማራ ፣ እስላምና ቅማንት የሚተዳደሩበትን ህግ ለመቀበል ወደምዝገና ሄዱ፡፡ እሱም ለአማራው ፣ "በል ይሂ ህግህ ደንብህ ይሁን በዚህ እደር" ብሎ መፅሀፍ ቅዱስ ሰጠው፡፡ ለእስላሙም ፣ "በዚህ እደር" ብሎ ቁራን ሰጠው፡፡ ቅማንቱ ፣ "ለኔስ?" ቢለው ፣ "አንተ አስተዋይና የማይዘነጋ ልቦና ስላለህ ህግን በልብህ አኖራለሁ በሱ ህግም ትተዳደራለህ" አለው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በቃል እንጂ በጽሁፍ አይመራም፡፡ (እዮብ ድንቁ መለሰ ፣ የካቲት 18 /2005 ፣ አይክል) ቃለ መጠይቅ፡፡

ቅማንቶች ‹‹አይደራኪ›› ብለው ለሚጠሩት ፈጣሪያቸው በተራራ ላይና በደን (ድግና) ውስጥ የሚደረግ የምስጋና ፣ የጸሎትና የመስዋዕት ስርዓት አላቸው፡፡



ድግና ተብሎ የሚጠራውና የሕገ-ልቦና እምነት ተከታዮች የጸሎት ስፍራ

በህገ-ልቦና እምነት ተከታዮች ዘንድ የዕለት በዕለት የዘወትር ጸሎት ያለ ቢሆንም ቅዳሴ የሚካሄድባቸው ቀናቶች ግን እሁድ ፣ ማክሰኞ እና ሃሙስ ብቻ ናቸው፡፡ ስርዓቱም የሚከናወነው ከጠዋቱ አንድ ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ ነው፡፡ የህገ-ልቦና ቄሶች የሚመረጡት ከክብር ዘር ሲሆን በህዝብ ዘንድ ከተመረጡ በኋላ ወደ ወንበሩ ይላኩና ተባርከው የቅስና ትምህርት መከታተል ይጀምራሉ፡፡ ለቅዳሴውም የሚዘጋጁ ቄሶች ከሁለት ቀናት በፊት ጀምሮ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ይታቀባሉ፡፡ ለእምነቱ ተከታዮች ምግብ በልዩ መቀደስን

አይከለከሉም ለዚህም ምክንያታቸው ‹‹ንጽህና በመብላት አይረክስም›› የሚል ነው።።

በኋላም ቄሶች የቅዳሴው ቀን ጠዋት ሰውነታቸውን ታጥበውና ጸድተው ነጭ ረጅም አላባሽና ሱሪ ለብሰው ኩታ ደርበው መጠምጠሚያ አድርገው ረጅም መቋሚያ በትርና ጭራ ይይዛሉ።። ወደ መቀደሻ ቦታው (ዱቢት ወይም ድግና) ሲደርሱ ለምለም ሳር ይዘው ከታጣም ቅጠል ቆርጠው በቅዳሴው ጊዜ የሚቆሙበትን ቦታ ይጎዝጉዛሉ።። ከዚያም ፊታቸውን ወደ ምስራቅ አዙረው በመቆም ጥምጥማቸውን (ራሳቸው ላይ ያሰሩትን ነጭ ሻሽ) በማውለቅ መሬት ላይ አስቀምጠው መቋሚያቸውን ብቻ ይዘው ይቆማሉ።። ከፊት ለፊታቸው ለመስዋዕት የሚሆን በግ ፣ ደሮ ፣ የጸበል ውሃ ፣ በኩስኩስት (ትንሽ እንስራ) ብርዝ ማር ፣ የጤፍ ቂጣና የገብስ ቆሎ ያቀርባሉ።። ይህ ሁሉ ዝግጅት ከተጠናቀቀ በኋላ የቅዳሴ ስርዓቱ ይጀመራል።።

ሰርዓቱ የሚቋጨው ፈጣሪ ለሰው ልጆች ሁሉ መልካሙን እንዲያደርግ ፣ የሰራ የድካሙን እንዲያገኝ ፣ ሃብቱ እንዲበረክት ፣ መሬት ጥሩ ዝናብ እንድታገኝ እና ጥሩ እንድታበቅል ፣ ለሰው ልጆችና ለእንሰሳት ተስማሚ እንድትሆን ፣ በዝናብ የበቀለ በጸሐይ እንዲበስል እግዚአታ በማድረግ ነው።። በመጨረሻም ለመስዋዕትነት የቀረበው በግ ፣ ደሮ የክብር ዘር በሆነው ቂስ ይታረድና የቀረበው ብርዝና ጠላ በታረደው በግ/ደሮ ላይ ይፈሳል።። ከታረደው ደሮ የቀኝ እግር ስጋ ከበጉ ደግሞ የታችኛው አገጭ በቢላዋ ተቆርጦ እሳት ላይ ይደረግና ሲበስል ትንሽ ትንሽ ስጋ እየቆረጡ ይይዙና ሁለት ቄሶች በመሆን በብሳና ቅጠል ላይ ራቅ ወዳለ ቦታ አስቀምጠውት ‹‹ይደራ አለ ይደራ አለ ይደራ አለ›› ይላሉ።። ይህም ጌታ ሆይ ይድረስህ ማለት ነው።። ይህ መስዋዕት ለፈጣሪያቸው እና ለማይታዩ ፣ ለማይለዩ መላዕክት (ጀካራንቲ ፣ ጊሊጊሎ ፣ ሊጎ ፣ ክብሮ) እንዲደርስ ከተለማመኑ በኋላ ወረብ ሰባት የሚባል የቅዳሴ ማሳረጊያ ዜማ

ያቀርባሉ። እርድ የተከናወነበትን ቦታ በመሳም ፣ የወንበሩን ጉልበት በመሳም እና ወደ ምስራቅ[7] ዞረው በመስገድ ምስጋና ያቀርባሉ።

በመጨረሻም ከታረደው በግ/ደሮ ፣ ከጠላው ፣ ከቂጣው ፣ ከብርዙ ፣ ከጠላው ... ለአስቀዳሾች ይሰጣል። እነዚህ የመስዋዕት ምግቦች የሚዘጋጁት በእማ ወረቴዎች (ሴት መነኮሳት) ነው። በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ እንዲህ ዓይነት የጸሎት ስርዓት ከሚከናወንባቸው ወራቶች ውስጥ ሰኔ እና ጥቅምት በዋናነት ይጠቀሳሉ። የሰኔው የጸሎት ሰርዓት የቸር ክረምት አድርግልን ፣ ዝናብ ስጠን ፣ ልጆቻችንን እና ከብቶቻችንን ጠብቅልን ፣ ተብሎ ልመናና ጸሎት የሚቀርብበት ሲሆን የጥቅምቱ ደግሞ የተዘራው ሁሉ ጥሩ ፍሬ የሚሰጥ አድርግልን ፣ ጥሩ መባጃ ስጠን ፣ ከክፉ ነገር ጠብቀን ተብሎ የሚጸለይበት ነው። በተጨማሪም ኪዳስቲ (በተለይም በክርክር እና ሙንሙቅ) እና አለሪ ወንበር የተባለ የጸሎት ስርዓት አሏቸው። በእነዚህ ስርዓቶች ላይ የሚቀርቡት ጉዳዮች ኪዱስ ምስጋና ፣ ገውተን (የፈጣሪ ምስጋና) ፣ ሽወን (ለፈጣሪ ልመና) ፣ ስኩዋላ (እግዚኦ መሃረነ) ናቸው።



የህገ-ልቦና እምነት ተከታይ ቄሶች በቅዳሴ ላይ

[7] ወደ ምስራቅ ዞሮ መስገድ ዘመኑን ብርሃን ያድርግልን ማለት ነው።

በህገ-ልቦና እምነት ትልቁ ጾም ከነሐሴ 1 ቀን እስከ መስከረም 1 ቀን የሚዘልቀው ነው። የቅማንት ማህበረሰብ ይህንን ጾም የሚጾመበት ምክንያት የኖህ መርከብ በንፍር ውኃ ስትንሳፈፍ የቆየችበትን ጊዜ በማሰብ ነው። በህገ-ልቦና እምነት ዓርብ ፣ ረቡዕ እና ቅዳሜ የታረደ ፈጽመው አይበሉም። በነዚህ ቀናት የአንስሳት ህይወት ማለፍ የለበትም ከሞተም መጣል (መቅበር) ነው ብለው ያምናሉ።

በአሁኑ ወቅት ግን አብዛኛው የቅማንት ህዝብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታይ ሆኗል። Zelealem (2003) Halevy (1877)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት የቅማንት ህዝብ ወደ ክርስትና እምነት የተቀየረው በፋሲለደስ ዘመን (1632-1667) ነው ይላሉ።
ሌላው በምክንያትነት የሚነሳው መሠረታዊ ጉዳይ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ላዕከማርያም የሚባሉ ጳጳስ ወደ ቅማንት ህዝብ በመላክ ህዝቡ የኦርቶዶክስ እምነትን ይቀበል ዘንድ እንዲጠመቅ ማድረጋቸው ነው።

3.4 የቅማንት ማህበረሰብ አስተዳደራዊ ሁኔታ

የቅማንትን ማህበረሰብ አስተዳደራዊ ሁኔታ በተመለከተ Gamst (1967) በሦስት ደረጃ ከፍለው ያስቀምጡታል። ከታች ያለው ደረጃ የአዛውንቶች ሽንጮ ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠር ማንኛውም አይነት ችግር መጀመሪያ ለመፍታት

ቀላውስት ጉባኤ ነው። በመጀመሪያው እርከን ላይ ሊፈታ ያልቻለ ችግር በዚህኛው እርከን ሊፈታ ይሞክራል። በሦስተኛ ደረጃ ያለው ደግሞ የሃይማኖትና የፖለቲካ የበላይ የሆነው ወንበር ነው። ከላይ በተዘረዘሩት ደረጃዎች መፍትሔ ያላገኘ ጉዳይ የመጨረሻ እልባት የሚያገኘው እዚህኛው እርከን ላይ ነው። የቅማንት ማህበረሰብ ወንበሮች በተለያየ ቦታ ይኖሩ ነበር። ለምሳሌ በሞዶጋ ፣ በከርከር ፣ በትክል ድንጋይና ወዘተ። ከከርከር ውጪ ባሉት ወንበሮች የተሰጡ ውሳኔዎች በይግባኝ ወደ ከርከሩ ወንበር ይመጡ ነበር። የከርከሩ ውሳኔ ግን ይግባኝ አልነበረውም።

አብዛኛው የቅማንት ህዝብ (በተለይ በገጠር ያለው) ይህን የአስተዳደር ስርአት ከመንግሥት የአስተዳደራዊ ስርአት ጐን ለጐን ይገለገልበታል። እዚህ ቦታ ላይ ስለዚህ ጉዳይ ከማስተዋወቅ ባለፈ ማብራሪያ አልሰጥበትም። ምክንያቱም አስተዳደራዊ ሁኔታው የዚህ ጥናት ዋና ጉዳይ የሆነውን የግጭት አፈታት ስርዓት የሚያጠቃልል በመሆኑ በአራተኛው ክፍል ሰፊ ማብራሪያ ስለምሰጥበት ነው።

3.5 የቅማንት ማህበረሰብ የጋብቻ ስርዓት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በቅማንት ማህበረሰብ የጋብቻ ሁኔታዎች ውስጥ ጎልተው የሚታዩና ተጠቃሽ የሆኑ ሶስት ሂደቶችን እና የሁለተኛ ጋብቻን ሁኔታ አስቃኛለሁ። እነርሱም ፦ የጋብቻ ዘር ቆጠራ ፣ ማርኮ ፣ የጋብቻ እድሜና ሁለተኛ ጋብቻ ናቸው።

የጋብቻ ዘር ቆጠራ

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሁለት አውራ ዝርያዎች (የዘር ግንዶች) አሉ። አንደኛው ክብር ሲሆን ሌላው ደግሞ ይተንቲ ነው። እነዚህ ሁለት ዝርያዎች አንዱ የሌላውን ያገባል እንጂ እርስ በእርሳቸው አይጋቡም። ለምሳሌ የይተንቲ ወንድ የይተንቲዋን ሴት አያገባም ፤ የክብርም ወንድ የክብሯን ሴት አያገባም። መጋባት የሚችሉት ክብሩ ከይተንቲዋ ወይም ይተንቲው ከክብሯ ነው። እንዲህም ሆኖ እስከ ሰባት ዘር መጋባት አይፈቀድም። ሁለቱ ግንድ ዘሮች ተጋብተው የሚወለደው ልጅ የትኛውን ዘር ይይዛል? ተብሎ ጥያቄ ቢነሳ በቅማንት ማህበረሰብ የዘር ቆጠራ ወቅት ማንኛውም ሰው የሚይዘው የአባቱን ዘር ነው። የክብር ወንድ የይተንቲዋን ሴት አግብቶ የሚወለዱት ልጆች ሁሉ ያባታቸውን የክብር ዘር ይሆናሉ። የይተንቲው ወንድ የክብሯን ሴት አግብቶ የሚወለዱት ደግሞ የአባታቸውን ዘር ስለሚይዙ የይተንቲ ዘር ይሆናሉ።

እንዲህ ከሆነ ደግሞ ሰባት ቤት መቁጠር ለምን አስፈለገ? ምክንያቱም አንዱ የሌላን ዘር አይደለም የሚያገባው? የሚል ጥያቄ መፈጠሩ አይቀርም። ምንም እንኳን ከተለያየ ዘር ቢሆኑም የቀረበ ዝምድና የሚፈጠሩባቸው አጋጣሚዎች አሉ።

ወንድምና እህት የሆኑ ሁለት የክብር ዘሮች ከይተንቲ ሲጋቡ የእነዚህ የሁለቱ ልጆች በተለያየ የዘር ሀረግ ውስጥ መግባታቸው ነው። ከወንዱ ክብር የሚወለዱት ልጆች የክብር ዘር ይሆናሉ። ከሴቷ የሚወለዱት ደግሞ የአባታቸውን ዘር ይዘው ይተንቲ ይሆናሉ። ስለዚህ በእነዚህ ሁለት የአንድ አያት ልጆች መካከል ጋብቻ እንዳይፈፀም ሰባት ዘር መቁጠር ያስፈልጋል።

ማርኩዛ

ማርኩዛ ማለት ምናልባት መባረክ ተብሎ ሊተረጎም ይችል ይሆናል። የክብር ወንድ የይተንቲዋን ሴት ሲያገባ ግንባሯ ላይ ይሰነጥባታል። ይህ የሚሆነው እቤቱ የገባች ዕለት ነው። የምትባረክበት ቦታም ግንባሯ ላይ በሰርኗ አቅጣጫ በሽፋሽፍቶቿ መካከል ነው። ምናልባት ይህ ድርጊት የመነጨው አደራ/አይደረኪ ሲያገባ የባረካትን ሴት መነሻ በማድረግ ሳይሆን አይቀርም። ክብሩ የባረካትን ይተንቲ ማንም ሰው አይመኛትም። እሱም ቢሆን ከባረካት በኋላ በህይወት እያለች ፊፅሞ መፍታት አይችልም። ማርኩዛ ለቅማንቶች የጠበቀ የትዳር መሀላና ቃል ኪዳን እንደሆነ ያስረዳሉ።

የጋብቻ እድሜ

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሴት ልጅ በአስራ አምስት አመቷ ወንድ ደግሞ በአስራ ስምንት አመቱ የመጀመሪያ ጋብቻቸውን ይፈፅማሉ። ወንድ በአስራ ስምንት አመቱ ለማግባቱ የሚያነሱት የቀደመ ተረክ ባይኖርም ቤተሰብ ለማስተዳደር የሚያስችለውን አስተሳሰብና ሰርቶ የመብላት እንዲሁም ሰው የማኖር አቅም የሚያገኘው በዚህ እድሜ እንደሆነ ይገልፃሉ። ሴቷ በአስራ አምስት መአቷ የምትዳርበትንና ከዚያ እድሜ በታች ያለች ሴት መዳር የማይፈቀድበትን ምክንያት ደግሞ በሚከተለው ሁኔታ ያስረዳሉ። ‹‹በክመንት ሴት በአስራ አምስት አመቷ ወንድ ደግሞ በአስራ ስምንት አመቱ ያገባል። ለምን ብትሉ አደራ ወደ ምድር ለመምጣት በፈለገ ጊዜ በምዝገና ትዕዛዝ ሲወለድ አስራ አምስት አመት ከሞላት ድንግል ሴት ተረግዞ ነው።›› (ኢዮብ ድንቁ መለሰ የካቲት 23/ 2005 ፣ አይከል) ቃለ መጠይቅ።

አስራ አምስት አመት የሞላት ሴት ለመፀነስ ብቁ ነች ብለው ስለሚያምኑ ሴት ልጆቻቸውን ከዚህ እድሜ ባነሰ አይድሩም። ለዚህም ፋና ወጊያቸው አደራ (አይደረኪ) ነው። እሱ ልጃገረድ ከሆነች የአስራ አምስት አመት ሴት ነው የተወለደው። ይህች ሴት በቀደመ ዕድሜዋ ከወንድ ያልተገናኘችና ተከብራ የኖረች ናት። ያም የሆነበት ምክንያት እስከዚያ እድሜ ድረስ ራስን ጠብቆ መኖር እንደሚቻል ለማሳየት ነው። ስለዚህ ሴቷ እስከ አስራ አምስት አመት የቆየች እንደሆነ በሁለንተናዋ ስለምትጠነክር እስከዚያ እድሜ ድረስ ትጠበቃለች እንጂ በቀደመ እድሜዋ አታገባም።

ሁለተኛ ጋብቻ

በቅማንት ማህበረሰብ ጋብቻ ውስጥ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ወይም አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ብቻ ተወስነው ይኖሩ ዘንድ የተገባ ነው። ሃይማኖታቸውም ሆነ ባህላቸው ከአንድ በላይ እንዲያገቡ አይፈቅድም። በቀደመው ዘመን ግን አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት በላይ ያገባ ነበር። ለምሳሌ ክብር (በአንዳንድ ተረኮቻቸው አይደረኪ) ሶስት ሚስቶችን አግብቶ ነበር። ያኔ ይህ የሆነበት ምክንያት ዘራቸው ትንሽ ስለነበር ዘራቸውን ለማባዛት ከመሻት እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንደውም እንደነሱ አባባል ፡- ‹‹ድሮን ያነሳሽ እንደሆነ ወንድምና እህትም በአንድ ማህፀን ተወንሶ በአንድ አድጎ ይጋባ ነበር›› (አቶ ፍርዱ ነቃ የካቲት 18/2005 ዓ.ም አይከል) ይላሉ ቃለ መጠይቅ። ምክንያቱም ያኔ በዚህ መንገድ ካልሆነ በስተቀር ትውልድን ማስቀጠል ስለማይቻል ነበር። አሁን ግን ያ የለም። ነገር ግን በቅማንት ሚስቱ የሞተችበት ወንድ ሌላ ሴት ማግባት ይችላል። ለምሳሌ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ አንድ ቄስ ሚስቱ የሞተችበት እደሆነ እና ሌላ ሴት ሊያገባ ቢፈልግ ቅስናውን አፍርሶ ነው። የቅማንት ቄስ ግን ክሶ ያገባል እንጂ ቅስናው አይፈርስም። ክሶ ሲባል ቆርቦ ማለት ነው። አግቢው ድግስ ይደግሳል። ከዚያ የቅማንት ቄሶቸ ተሰብስበው ሲቀድሱ ያድራሉ። ሙሉ ቅዳሴ ሲያድሩ በዋንዛ እንጨት ገበታ ንፁህ ውሃ ይሞላል። ውሃውን በቅል ቀድቶ ከወንዝ የሚያወጣውም ቄስ ነው። ከዚያ ክፍቱን ሲቀደስበት ያድራል። ከዚያ ያ ውሃ እንደፀበል ይቆጠራል። ከዚያ ጠዋት ያቺ የምታገባዋ ሴትና ያ የሚክሰው ቄስ

ቅዳሴ በታደረበት የተባረከ ውሃ ይጠመቃሉ። ከዚያ ቄስ የባረከውን ስጋ እንዲቀማመሱ ይደረጋል።

በቅማንት ካገቡ በኋላ ፈትቶ ማግባት አይፈቀድም ፤ ነገር ግን በሞት የተለያዩ እንደሆነ በሕይወት ያለው ሰው ያገባል። ያም ሲሆን የሃይማኖት ስርዓታቸው እንደሚፈቅደው ደግሰውና ቅዳሴ በተደረገበት ውሃ ተጠምቀው ነው።[8]

[8] በዚህ ምዕራፍ የጠቃቀሱት ጉዳዮች በሙሉ ከግጭት ጋር ግንኙነት ስላላቸው ነው።

4. ግጭት ፣ የግጭት መፍቻ ተቋማትና ሥርዓቶች

በዚህ የጥናቱ ዋና አካል በሆነው ርዕስ ስር የቅማንት ማህበረሰብ አባላት ለግጭት ምንነት የሚሰጡት ትርጓሜ ፣ ማህበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ዋና ዋና የግጭት ዓይነቶችና የግጭቶቹ መንስዔዎች የተሰጡ ውሳኔዎች እንዲሁም ግጭቱ የሚፈታባቸው ተቋማት ምንነት ከሚከተሉት የግጭት አፈታት ስልት ጋር ቀርቧል፡፡

4.1 የግጭት እሳቤ በቅማንት ማህበረሰብ

የቅማንት ማህበረሰብ ለግጭት የሚሰጠው ትርጓሜ እንደየሰው ማንነትና ነገሮችን የመረዳት ብቃት የተለያየ ቢሆንም የሁሉም ትርጓሜና ብየና ግን በይዘቱ የተለየ አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ ‹‹ጥል በቃ ጦርነት ነው›› ይላሉ (አቶ ፍርዱ ነቃ የካቲት 18/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ፡፡ ግጭት ከጸብነቱ ባሻገር የህይወትና የሰላም ጸር መሆኑን የሚገልፁት ደግሞ አቶ አየልኝ ናቸው፡፡ ‹‹ግጭት ህብረተሰቡን ከህብረተሰብ እንዲጋጭ የሚያደርግ ፣ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው ጥቅም የሌለው ፣ ማህበረሰቡ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ እንዲፈልስ የሚያደርግ እና ለልማት ፀር የሆነ ነገር ነው፡፡›› (አቶ አየልኝ መጋቢት 1/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ለግጭት የሚሰጠው ብያኔ በአብዛኛው ተቀራራቢ ነው፡፡ ሰላም አደፍራሽነቱ ፣ አካባቢ ማናጋቱ ፣ ዘረፋ ማምጣቱና በአንድ ሰው ተነስቶ ለሌላው መትረፉና መተላለቅን ማምጣቱ ነው፡፡ የፖሊስ ባልደረባው እዮብ ድንቁ ስለ ግጭት እንዲህ ይላል ‹‹ግጭትን ለማረጋጋት ከፍተኛ ሃይል ይጠይቃል፡፡ በአንድ ሰው የተነሳው ሁከት ለሌላው ይተርፋል፡፡ ትንሽ ነገር በመጠዋ ሃይል ገፋፊነት ወደ ትልቅና ወዳልተፈለገ ደረጃ በመድረስ የሰውን ነፍስ የሚነጥቅበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡›› (እዮብ ድንቁ ፣ የካቲት 18/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ፡፡

የፀቡ ወይም የግጭቱ ዓይነት እና ደረጃም የሚሰላው ግጭቱ ባስከተለው የንብረት ፣ የአካል እና የሕይወት መጥፋት መጠን እና ደረጃ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳትም ግጭቶችን ቀላል እና ከባድ እያሉ የመፈረጅ ልማድ አለ፡፡ ግጭትም ለቅማንት ማህበረሰብ የለውጥ ማነቃቂያ እና ማህበረሰባዊ ዕድገት ግብ መምቻ መንስኤ

አይደለም፡፡ ይልቁንም መደባደቢያ ፣ አካል ማጉደያ ፣ ንብረት ማውደሚያ እና መግዳደያ ነው፡፡ ስለሆነም አዎንታዊ ገጽታ የለውም፡፡

4.2 በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ግጭቶች መንስኤ

በቅማንት ማህበረሰብ የሚፈጠሩ ዓበይት የግጭት ዓይነቶች ከኢኮኖሚ ፣ ከባህላዊ እሴት ፣ ከሞራልና ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ከቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ መገንዘብ ችያለሁ፡፡

ለግጭቶቹ መንስኤ የሚሆኑ በጣም ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ የባልና ሚስትን ያየሽ እደሆነ ፣ በደንበር ገፋሽኝ ገፋሽኝ ይጣላሉ ፣ እ... የመጀመሪያ ወንድ ልጅ የአባቱን የጀግንነት ዕቃዎች ፣ ልብስ ይወርሳል፡፡ በዚህ ግዜ ትንሹ ለኔ ነው የሚገባ ካለ በዚህ ይጋጫሉ፡፡ ሴትን ልጅ አስገድዶ በመድፈር ግፍ ሲፈጽሙ በደፋሪውና በተደፈረችው ልጅ መካከል ቤተሰቦቻቸው ይጋጫሉ፡፡ አሁን ግን ቀርቷል፡፡ ትልቁ ደሞ ጠብ ጫሪው ነገር የመሬት ሽግሽግ ወቅት የሚደረገው የማሳ ክፍፍል ከአንዱ ተቆርሶ ለአንዱ የተሰጠ ጊዜና ተይው ፍጅት ነው ፍጅት (የካቲት 21/2005 ዓ.ም አይከል) የቡድን ውይይት፡፡

4.2.1 ከኢኮኖሚ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች

በቤተሰብ ፣ በጎረቤት ፣ በጎሳ ወዘተ... ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ቤተሰብ ከቤተሰብ ፣ ባልና ሚስት ፣ እህትና ወንድም ፣ አባትና ልጅ ከጎረቤት ጋር በማሳ (ድንበር) ፣ በግጦሽ መሬት ወዘተ ዙሪያ ይጋጫሉ፡፡ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ጥያቄ በማንሳት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እርስበርሳቸው የከረረ ግጭት ይፈጥራሉ፡፡ ቡተለይም በማሳ ክፍፍል ወቅት ከአንዱ የመሬት ይዞታ ተቆርሶ ለሌላው እንዲሰጥ በቀበሌ የመንግስት መዋቅር በኩል ይደረጋል ስለሚባል በማህበረሰቡ ውስጥ ሽኩቻ ፣ ብሶትና ለቅሶ መኖሩን ከቡደን ውይይቱ መገንዘብ ችያለሁ፡፡

4.2.2 ከእሴት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች

በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ልዩ ባህላዊ እሴቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህም አንዱ ለአንጋፋ ወይም ቀድሞ ለተወለደ ወንድ ልጅ የሚሰጥ ማህበራዊ እሴት ሊጠቀስ

ይችላል፡፡ አባት ሲሞት ከቤተሰብ ውስጥ ከተወለዱት ወንዶች ልጆች ውስጥ ታላቅ የሆነው ልጅ የአባቱን ጦር ፣ ጎራዴ ፣ ጋሻ... እንዲወርስ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶች የአባቱ ማንነት መገለጫ ትዕምርቶች ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ ስለሆነም ታላቁ ልጅ የአባቱን ቁሳቁስ መውረሱ በአባቱ ምትክ ቤተሰቡን እንዲያስተዳድር ሃላፊነት መረከቡን ያመለክታል፡፡ ከማህበረሰቡ ደንብ አፈንግጦ በእነዚህ ቁሳቁሶች ላይ ታናሽ ‹‹የይገባኛል ጥያቄ›› ቢያነሳ በወንድማማቾች መካከል ግጭት ይፈጠራል፡፡

4.2.3 ከሞራል ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች

የማህበረሰቡን ሞራል የሚነኩ ድርጊቶች ሲፈፀሙ በግለሰቦች በጎረቤቶችና በቤተዘመዶች መካከል ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ለአካለ መጠን ያልደረሱትን ህፃናት መድፈር ፣ ዘመድ ለዘመድ የግብረ ስጋ ግንኙነት መፍጠር ወዘተ በግለሰቦች ፣ በቡድኖች መካከል የከረረ ግጭትን ይፈጥራል፡፡ በተለይም በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ እህቱን ፣ አክስቱን ፣ (የእህትና የአክስት ልጅ) የደፈረ በህብረተሰቡ ውስጥ በነፍሰ ገዳይነት ይፈረጃል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በሰላም የመኖር እድልም የለውም፡፡

4.2.4 ከሃይማኖት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች

በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ አብዛኛው የማህበረሰቡ ክፍል የሚከተለው እምነት ህገ-ልቦና እንደሆነ በቀደመው ክፍል ተገልጿል፡፡ ይህ ማህበረሰቡ ከጥንት ጀምሮ ይዞት የቆየው የራሱ ሃይማኖት ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ግለሰቦችና የሃይማኖት ተቋማት የሃይማኖት ነፃነት አለን በሚል ሽፋን በተከታዮቻቸው ዘንድ ስብከት ሲያካሂዱ የማህበረሰቡን እምነት አንቋሸሸው ፣ ከጣዖት አምላኪነት ጋር አያይዘው ያቀርባሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቼ እንደገለፁልኝ በጥንት ጊዜ በተለይም በአፄው ስርዓት የቅማንት ማህበረሰብ የሚከተለውን የህገ ልቦና እምነት ለማስተው ማህበረሰቡን በግድ የማጥመቅና ክርስትና የማስነሳት ድርጊቶች እንደተፈፀሙበት ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ምክንያት አንዳንዶቹ ከአባት የወረስነውን እምነት አንተውም በሚል ብዙ ግጭቶች እንደተፈጠሩ ይገልፃሉ፡፡

እንዴ ድሮማ በነ አጤ ኃ/ሥላሴ ግዜ በሃይማኖት የተነሳ ብዙ እልቂት ሆኖ ነበር፡፡ ንጉሱ አባ መላክ የተባለ ጳጳስ ልከው እንዳለ የቅማንትን ህዝብ ታልተጠመቀ አለ፡፡ ህዝቡም እምቢ አሻፈረኝ ካባት የወረስኩትን ሃይማኖት አለቅም አለ፡፡ ግማሹ ደግሞ ግርፋቱን ፈርቶ እሺ አለ፡፡ እምቢ ያሉት ታዲያ ብዙ ግፍና በደል ደርሶባቸዋል፡፡ እሺ ያሉትን ግን አንድ ላይ አጥምቀዋቸዋል፡፡ (የካቲት 21/2005 ዓ.ም አይከል) የቡድን ውይይት፡፡

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ የማህበረሰቡ ተወላጆች እርስበርስ በሚያደርጉት መስተጋብር የሚፈጠሩ ግጭቶችን ፣ ሰላምን የሚያናጉ ሁከቶችን የሚፈቱባቸው ከተፈጥሮ ጋር ያለውን የሕይወት ትስስር ትርጓሜ የሚሰጡባቸው የፍትህ አካላት አሏቸው፡፡ በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል በሚፈጠሩት ግጭቶች ሳቢያ የሚከሰቱትን የህይወት ህልፈት ፣ የአካል ጉድለት ፣ የንብረት መውደም ወዘተ የሚያስከትሉትን ማህበራዊ ቀውሶች ለመፍታት የሚጠቀሙባቸው ደንቦች ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር በግለሰቦች ፣ በቡድኖች ፣ በቤተሰቦች ፣ በጎረቤቶች ፣ በጎሳዎች ወዘተ መካከል በህይወት ማለፍና በአካል ጉድለት ምክንያቶች ቅራኔ እየተባባሰ ለእርስ በርስ እልቂት እንዳይዳረግ በቂም በቀል ህዝቡ ተጨራርሶ የተናጋ ዓለም እንዳይፈጠር የሚጠቀሙበት የሰላም ማውረጃ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ከእምነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ምክንያት የሚፈጠሩትን ሥነ ልቦናዊ ግጭቶች ለመፍታት ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ስልቶች ናቸው፡፡ በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ማህበረሰቡ በአብዛኛው ባህላዊውን የፍትህ ተቋም ጎን ለጎን ደግሞ ዘመናዊውን (መደበኛውን ፍርድ ቤት) እንደግጭቱ ሁኔታ ደግሞ ሁለቱንም በጋራ ሊጠቀም ይችላል፡፡

ዘመናዊ የፍትህ ሥርዓት የሚከናወነው የሀገሪቱን የተለያዩ ዘመናዊ ሕጎች መሰረት በማድረግ በቀበሌ የፍርድ ሸንጎዎች ፣ በወረዳ ፣ በዞን እንዲሁም በክልልና በፌደራል ፍርድ ቤቶች ውስጥ ነው፡፡ ይህም ተግባሩ ተፈጻሚ እንዲሆን መደበኛ ፍርድ ቤቶች ፣ የቀበሌ የፍርድ ሸንጎዎች ፣ ፖሊስ ጣቢያዎች ፣ የመንግስት

የሰላምና የጸጥታ ኮሚቴዎች በማዋቀር ስራዎችን ይሰራል። በቅማንት ማህበረሰብም እነዚህ የፍትህ ተቋማት አገልግሎት ይሰጣሉ።

4.3 ባህላዊ የፍትህ ተቋማት

በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ማንኛውም ዓይነት ግጭት ሲፈጠር በቅድሚያ የሚኬደው የአካባቢ ሽንጎ ተብለው ወደሚጠሩት የፍትህ አካላት ሲሆን ጉዳዩ በእነርሱ የማይፈታ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ አፈሊቅ ወደተባሉትና በወንበሩና በአካባቢ ሽንጎዎች መካከል ወደሚገኙት የፍትህ አካላት ይሄዳሉ። ጉዳዩ አሁንም በእነዚህ የፍትህ አካላት እልባት ካልተሰጠው ወደ መጨረሻው ደረጃና ወደ ወንበሩ (ከፍተኛ ቅሬታ ሰሚ) ተብሎ ወደሚጠራው የፍትህ ውሳኔ ሰጪ ይሄዳሉ።

እነዚህ የፍትህ አካላት እንደ ፎክሎራዊነታቸው በክዋኔ ይተረጎማሉ ፣ በማህበራዊና በባህላዊ አውድ ይወሰናሉ። በተሳታፊዎች ሚና ውጤት ላይ ይደረስባቸዋል ፤ በተባባሪ ወገኖች መካከል የሚደረጉ ግጭቶች ተፈትተው ወደ ሰላማዊ ህይወት ይደረስባቸዋል። እርቅና ሠላም ይወርድባቸዋል። እያንዳንዱን በዝርዝር እንመልከት።

4.3 .1 የአካባቢ ሽንጎ

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ የአገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ክብርና ስልጣን ይሰጣቸዋል። ሽንጎው ህዝባዊ ሆኖ በጉባኤው ላይ የሚገኙት በብዛት ወንዶች ናቸው። ከዚህም አልፎ በዕድሜ ገፋ ያሉና ጸጉራቸው የነጣ በአነጋገርም ሆነ በአስተሳሰብ የተከበሩ ናቸው። የሚመረጡት በህዝብ ሲሆን የሚመረጡበት መስፈርት በዕድሜ ገፋ ያሉ ፣ በዳኝነት ስርዓት ልምድ ያላቸው ፣ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ታዋቂ የሆኑ ፣ ሃይማኖቱንና ቋንቋውን ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆን ይጠበቅባቸዋል። የአካባቢ ሽንጎ አባላት የሚመረጡት ከማንኛውም የቅማንት ማህበረሰብ (ከተራው ሰው ፣ ከቀሳውስት ፣ ከገበሬው ...) ሲሆን በቁጥር ከአምስት እስከ ሰባት ይደርሳሉ።

እነዚህ የፍትህ አካላት ከሀብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶችን ፡- መሬትን፥ ድንበርን፥ የግጦሽ ቦታን፥ የውኃን፥ የከብት ዝርፊያን፥ ብድርንና የመሳሰሉትን ምክንያት አድርገው የሚነሱ ጠቦችን ፤ የቤተሰብ ጠብ ፡- ከጋብቻ፥ ከልጆች፥ ከውርስ ወዘተ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶችን ፤ ወንጀል ፡- ድብድብና ግድያን በመሳሰሉት ምክንያት የሚነሱ ግጭቶችን ፤ ተራ ወንጀሎች ፡- ስርቆትንና የመሳሰሉትን ፤ የቡድን ጠብ ፡- ይመለከታሉ፡፡ ይህንን አስመልክቶ አቶ ኢዮብ እንዲህ ይላሉ፡፡ ‹‹የአካባቢ ሽንጎ አባላት የማያዩት ጉዳይ የለም፡፡ ሁሉንም የግጭት ዓይነቶች ያያሉ፡፡ ውሳኔም [illegible] በማሳወቅ ወንበሩ እንዲፈርዱ ያደርጋሉ እንጂ፡፡›› (የካቲት 18/2005 ዓ.ም አይክል) ቃለ መጠይቅ፡፡

የአካባቢ ሽንጎ አባላት የዳኝነት ቦታቸው የተወሰነ አይደለም፡፡ ለምን ቢባል እንደጉዳዩ ክብደትና ቅለት ከቦታ ቦታ ፤ ከአካባቢ አካባቢ እየተንቀሳቀሱ ሥራቸውን ሊከውኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የግድያ የግጭት አፈታት ስርዓት (ምንም እንኳን በእነሱ ውሳኔ የሚሰጥበት ባይሆንም) ሲኖር ጉዳዩን ለማጣራት ፤ ወንጀለኛውን አድኖ ለመያዝ ፤ የሟች ወገንን እፎይታ ለመስጠት ከቦታ ቦታ ከአካባቢ አካባቢ በመዘዋወር ሊዳኙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ እንደባልና ሚስት ፤ የቤተሰብ ጥል ፤ የድንበር መገፋፋት ... ሲሆን በተወሰነ ቦታ ሁሌም በሚቀመጡበትና ወንበሩ ለታዛቢነት በሚገኙበታ ቦታ ሆነው ይዳኛሉ፡፡ ከእነርሱ አቅም በላይ የሆነ ፤ እልባት ያልተሰጠው ፤ ወይም ውሳኔ አስተላልፈው አንደኛው አካል በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ሲጠይቅ ጉዳዩን ለአፈሊቅ በማሳወቅ ወንበሩ ውሳኔ እንዲሰጡበት ያደርጋሉ፡፡

4.3.2 አፈሊቅ

አፈሊቅ የሚመረጠው (የሚሾመው) በወንበሩ ሲሆን የሚመረጠው በቅማንት ማህበረሰብ ከተከበረውና ቁንጮ ከሆነው ከክብር የዘር ሀረግ ነው፡፡ ተጠሪነቱም ለወንበሩ ነው፡፡ በአፈሊቅነት ተመራጭ የሆነው ሰው በሚኖርበት መንደር ተወዳጅነትን ያተረፈና ተቀባይነት ያለው ሰው መሆን አለበት፡፡

ማህበረሰቡ የሚተዳደርባቸውን ህግና ደንቦች ፣ ሥርዓት ልምዶች ፣ እንዲሁም በግጭት ወቅት ለሚሰጡ ውሳኔዎች በስሩ በተዋቀሩት አባላት አማካኝነት ተፈፃሚ መሆናቸውን የሚቆጣጠር የበላይ ጠባቂ ነው፡፡ እንዲሁም በአካባቢው ሽንጎ የፍትህ ተቋም እልባት ያላገኙ ጉዳዮችን ለወንበሩ የሚያስተላልፍ ነው፡፡

አፈሊቅ ለምን ከክብር የዘር ሀረግ እንደሚመረጥ አቶ አየልኝ ተሰማ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹ አፈሊቅ ማለት እኮ ለወንበሩ በጣም ቅርብ የሆነ ፣ በህዝቡ መካከል የሚፈጠሩትን ግጭቶችና በአካባቢ ሽንጎዎች የተላለፉለትን ጉዳዮች ለወንበሩ የሚያቀርብ ነው፡፡ ስለሆነም ታማኝ ፣ ታዛዥ ፣ ፈጥኖ ደራሽ ፣ መሆን አለበት፡፡ ታዲያ ወንበሩ እንዲህ ያለው ሰው ከክብር የዘር ሀረግ እንዲመረጥ የሚያዙት ከእርሳቸው በታች ሆኖ ጉዳዮችን በበላይነት እንዲያስፈጽም በማለት ነው፡፡ (አቶ አየልኝ ተሰማ መጋቢት 1/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ፡፡

ለእርሱ የሚመረጡትን ጉዳዮች እራሱ ወደ አቋቋማቸው ንዑስ ሽንጎዎች በመምራት ጉዳዩ ተፈጻሚነት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ ንዑስ ሽንጎው አንድ አለቃና አምስት ወይም ከአምስት የበለጠ አባላትን የያዘ ነው፡፡ ይህም ስራ እያንዳንዱ የቅማንት ሰው (ወንዶች) በህይወቱ ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ በዚህ ስራ ተሳታፊ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ንዑስ ሽንጎው ጉዳዮችን ከአጠና በኋላ ወደ ዋናው ሽንጎ በመምራት ውሳኔ ያስወስናል፡፡ በአለፈው ጊዜ አፈሊቆች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በአገሩ ውስጥ ያሉትን ግጭቶች የሚያረጋጉ ሲሆን ማንኛውም የቅማንት ማህበረሰብ በፍትህ ተቋማቱ የተሰጠውን ብያኔ የማስፈጸም ሃላፊነትም ተጥሎባቸዋል፡፡ አፈሊቆች በድሮው የዳኝነት አሰራር ቅጣት የመወሰን ፣ ገንዘብ የመቅጣት ስልጣን ነበራቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት ግን ወሳኝ አካላት አይደሉም፡፡ እያንዳንዱ ወንበር በርከት ያሉ አፈሊቆች ነበሩት፡፡ በአፈሊቆች መወሰን ያልተቻለ ጉዳይ ወደ ወንበር ቀርቦ ይወሰናል፡፡ እኔ የመስክ ጉብኝት ባካሄድኩበት ወቅት የነበረው አንድ አፈሊቅ ሲሆን እርሱም

መወሰን አይችልም። ነገር ግን ውሳኔ የተሰጠባቸውን ጉዳዮች በስሩ በተዋቀሩት አካላት አማካይነት ተፈጸሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።

4.3.3 ወንበር

ወንበር በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበረሰባዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን በበላይነት የሚመራ እና የሚቆጣጠር ከፍተኛ ሃላፊነት የተሰጠው ነው። ወንበር የሚመረጠው በህዝብ ሲሆን መስፈርቱም የክብር ዘር መሆን ፣ የሃይማኖት እውቀት ፣ የቋንቋ እውቀት ፣ የዳኝነት ብቃት እና የአመራር ጥበብ ነው።

ወንበሮች በቅማንት የቤተ ክህነት መሪ በመሆን ከሚያከናውኑት ስራ በተጨማሪ የአስተዳደሩንና የዳኝነቱንም ስራ ደርበው ይሰራሉ። በአገር ሽማግሌዎች ሸንጎ መወሰን ያልተቻሉ ግጭቶች ባጋጠሙ ጊዜ ጉዳዩ በቀጥታ ወደ ወንበሩ ይመራል። የመረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝ ቀደም ሲል በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሁለት ከፍተኛ ወንበሮች ነበሩ። እነርሱም አንደኛው በክርክር አንደኛው ደግሞ በጭልጋ ይኖሩ ነበር። በተጨማሪ በልዩ ልዩ የቅማንት መንደሮች የሚኖሩ ከአስር የሚበልጡ ምክትል ወንበሮች ነበሩ። እነዚህ ምክትል ወንበሮች በጉዋንግ ወንዝ በስተ ምዕራብ በኩል የሚኖሩ ከሆነ በጭልጋ ወንበር ትዕዛዝ ስር ይተዳደሩ ነበር። በወንዙ በስተ ምስራቅ በኩል የሚኖሩ ከሆነ ደግሞ የሚተዳደሩት በክርክር ወንበር ትዕዛዝ ስር ነው። እነዚህ አካላት ብዙ የህዝብ ጉዳይ እየመረመሩ ውሳኔ የሚሰጡ ሲሆን በጣም ከባድ የሆኑና ከእነርሱ ስልጣን በላይ የሆኑ ጉዳዮች በሚያጋጥሟቸው ጊዜ ለተከበሩት ሁለቱ ከፍተኛ ወንበሮች ጉዳዩ እንዲቀርብ ይደረጋሉ። ከዚያም ይህ ሁሉ ቀርቶ ሁለቱ ከፍተኛ ወንበሮች ብቻ በስልጣን ላይ እንደነበሩ ቆዩ። ከሁለቱ ወንበሮች የክርክሩ ታላቁ ወንበር በመባል በበላይነት ይመሩ ነበር። ሆኖም በ1955 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ እርሳቸውን የሚተካ ባለመገኘቱ የጭልጋው ወንበር የቅማንት አጠቃላይ ወንበር ሆነው በበላይነት መምራት ጀመሩ።

የወንበር የገቢ ምንጪ፡- ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበሩት ወንበሮች የገቢ ምንጭ በአንዳንድ በዓላት ላይ በህዝቡ የሚደረገውን አስተዋጽኦ ፣ ስርዓት በመተላለፍ ከሚቀጡት ሰዎች የሚከፈለውን ገንዘብ ለራሳቸው ገቢ በማድረግ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ እያንዳንዱ የግል ሰው በዓል ላይ ማለትም እንደክርስትናና ተዝካር ዓይነት በዓል ሲከበሩ ሁለት ጣሳ ጨው ወይም ሁለት ክብር የተሰሩ የማርትሬዛ ብር ለወንበሩ ይከፈላሉ፡፡ በአለፉት መቶ አመታት የክርክር ወንበር የቅማንትን ምስራቃዊ ክፍል መንደሮች ግብር ያስገብሩ ነበር፡፡ የጭልጋ ወንበር ደግሞ ግብር የሚያስከፍለው ምዕራባዊውን ክፍል ነበር፡፡ የዚህ ዓይነቱ የግብር አከፋፈል ያቆመው በ1888 ዓ.ም በክርክር በጭልጋ ደግሞ በ1920 ዓ.ም ነው፡፡ የሚተዳደሩበት ዋነኛው ገቢም በህዝቡ የሚታረስላቸው የእርሻ ምርት ነበር፡፡[9]

ወንበሩ በአብዛኛው ከከፍተኛ እና ከዝቅተኛ ቀሳውስቶች ጋር በመሆን በመንደሩ ውስጥ የሚፈጠሩትን ግጭቶችና ክርክሮች ያዳምጣሉ፡፡ ሦስቱም (በየደረጃው ያሉ የፍትህ አካላት) ሁኔታውን ከአዳመጡ እና ካጣሩ በኋላ ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡ እነዚህ የፍትህ አካላት የስልጣን ገደብ የላቸውም፡፡ ነገር ግን አሰራራቸው በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ካላገኘ ፣ የማህበረሰቡን መብትና ጥቅም የማያስከብር ውሳኔ በየትኛውም የፍትህ አካል ከተሰጠ ከስልጣናቸው ይሻራሉ፡፡ ይህ ግን ወንበሩን አይጨምርም፡፡ ምክንያቱም ወንበሩ ምንም እንኳን በህዝብ የተመረጡ ቢሆንም ስልጣናቸው የሚሻረው ሲሞቱ ብቻ ነው፡፡

[9] ስለ ወንበር የተነገረው መረጃ በሙሉ የተገኘው በቡድን ውይይት ወቅት ነው፡፡



የቅማንት ማህበረሰብ ወንበር ሙሉነህ መርሻ እና ልጃቸው ቄስ አማረ ሙሉነህ

4.4 መደበኛው ፍርድ ቤት እና ባህላዊው የፍትህ ተቋም ያላቸው ትስስር

ሁሉም የሚፈጠሩ ግጭቶች በአንድ ዓይነት የፍትህ ሥርዓት ተስተናግደው መፍትሔ ያገኛሉ ማለት እንደማይቻል ከሚፈጠሩ የግጭት ዓይነቶችና ምክንያታቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የፍትህ ሥርዓቱን የተሟላ አድርጎ የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት በተሻለ ሁኔታ አሟልቶ ለመጓዝ የሚፈጠሩ ግጭቶችን እንደባህርያቸው መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ማስረጃ የሌላቸው ፣ በድብቅ የተፈጸሙ ግድያዎችና የገንዘብና የንብረት መካካዶች በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት የግጭት አፈታት ወቅት ፤ ወንጀል መሆናቸው የሚረጋገጡ ጉዳዮች ሲገኙ ጉዳዩን ለመደበኛው ፍ/ቤት አሳልፎ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በሌላ ጎኑ ማስረጃ ያላቸውና ወደ ህግ መቅረብ የሚችሉ ጉዳዮች በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ይዳኛሉ፡፡

በቅማንት ማህበረሰብ ግጭቶችን በመፍታት ባህላዊው የፍትህ ሥርዓትና ዘመናዊው /መደበኛው/ የፍትህ ሥርዓት የማይተካካ ሚና ስላላቸው ሁለቱም የየራሳቸውን አገልግሎት እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ አንዱ የአንዱን ክፍተት በመመላትና በመደጋገፍ ስራዎችን እየሰሩ ነው፡፡ የጋራ ዓላማቸው የህብረተሰቡን ደህንነት ማስጠበቅ መሆኑ የመጀመሪያ የመደጋገፊያ መንገዳቸው ነው፡፡ ስለሆነም በሰው ግድያ/ ነፍስ በማጥፋት/ እና ማስረጃ በማይቀርብባቸው ወንጀሎች ላይ በጋራ ይሰራሉ፡፡

ትብብሩ ማዕከል የሚያደርገው የግጭቶችን ዓይነት እንደሆነ ደግሞ አቶ እዮብ ይገልፃሉ፡፡ የሚፈጠሩት የግጭት ዓይነቶች የሚፈቱበት የየራሳቸው ሥርዓትና አግባብ እንዳላቸው በርካታ ተመራማሪዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ የግጭቶቹን አፈጣጠር ሰበብ ፣ የተጋጭዎቹን ሁለንተናዊ ማንነት ማየትና በመፍትሔውም ተገቢውን አቅጣጫ ለማስቀመጥ ይሞክራሉ፡፡ ትስስራቸውንና በአንድ የመስራታቸውን ሁኔታ መቶ አለቃ ጥጋቡ ሲገልፁ ‹‹በየሶስት ወሩ ግንኙነት እናደርጋለን፡፡ የፀጥታ ፎረም አለን፡፡ የሃይማኖት መሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው ለህግ ጉዳዮችን እንዴት እንደሚያቀርቡ እንወያያለን፡፡›› (መቶ አለቃ ጥጋቡ የካቲት 18/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ፡፡ ስለሆነም የሁለቱ የፍትህ ሥርዓቶች መደጋገፍ የሚያመጣው የተሻለ ውጤትን ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የግድያ ወንጀል ቢፈጠር ግጭቱን ፈጥኖ ለማብረድና ዘላቂ የሆነና በመተማመን ላይ የተመሰረተ እርቅ ለማውረድ ሁለቱም የፍትህ ሥርዓቶች የማይተካካ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በግድያው ሳቢያ የሚቀሰቀሰውን የመበቃቀል መንፈስ ለማስወገድና ወንጀለኛውን በሰራው ወንጀል ለመዳኘት መደበኛ ፍ/ቤት መቅረቡ ተመራጭ ነው፡፡ በዚያው መጠን ደግሞ የገዳዩ መታሰር ወይም ለህግ መቅረብ ብቻውን በቀሪ ወገኖች ላይ የሚፈጠረውን የበቀል ስሜትና ደም የመመለስ ቁጣ ለማብረድ በባህላዊው የፍትህ ሥርዓት መጓዝ ያስፈልጋል፡፡

ከሰው ግድያና በስውር ከተፈጸሙ ወንጀሎች በተጨማሪ አልፎ አልፎም ቢሆን በሌሎች የግጭት አፈታት ጉዳዮች ላይም መደበኛው የፍትህ ሥርዓትና ባህላዊው የፍትህ ሥርዓት ትብብር ያደርጋሉ፡፡ በዚህ ዘርፍ ከሚጠቀሱት ውስጥ የድንበር መገፋፋትን በተመለከተ የሚነሱ ጸቦችን የአካባቢ ሽንጎ አባላት የሆኑ ሽማግሌዎች እንዲዳኟቸውና ውሳኔ እንዲሰጡባቸው መደረጋቸው ነው፡፡

የእነዚህ የፍትህ አካላት ዋና ተግባር የተቻላቸውን ጥረት በማድረግ የተፈጠረው ጠብ ረግቦ ወደ ሰላማዊ ኑሮ መመለስ ነው፡፡ በአጠቃላይ የእነዚህ የፍትህ ተቋማት ውህደት የእርቅ ስርዓቱ አመርቂ ውጤት እንዲያመጣ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

4.5 የፍትህ ተቋማቱ ግጭትን የሚያስወግዱበት ስርዓት

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ባህላዊ የፍትህ ተቋመቱ ግጭትን የሚያስወግዱበት ስርዓት ሽወን[10] ይባላል። ሽወን በባህላዊው ዐውድ ሰላምን ፣ ፍቅርን ፣ ዝምድናን ከማጠናከር አንፃር የሚታይ ነው። ሰዎች በግጭት ምክንያት ሁከት ፣ ብጥብጥ ፣ ስደትና የስነ ልቦና ቀውስ ውስጥ ገብተው እንዳይቀሩ የሽወን ስርዓት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ስለሆነም የሽወን ምንነት መገንዘብ የሚቻለው ከሚኖረው ማህበረሰባዊ ጠቀሜታ አንጻር ነው።

ሽወን እንደ መደበኛው ፍርድ ቤት የህግ አንቀፅ እየተጠቀሰ በዘመናዊና መደበኛ ፍ/ቤት ውሳኔ የሚሰጥበት ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ ነው። ባህላዊ እሴቶችን መሰረት በማድረግ በመሃላ ፣ በምርቃት ፣ በእርግማን ፣ በውግዘት ፣ ከማህበረሰቡ በመገለል... እየተቀናበረ የሚከወን ነው። ይህም የራሱ ከዋኞች ፣ ተሳታፊዎች ፣ መቼቶች እና ዐውዶች ያሉት ባህላዊ ስርዓት ነው። ስለዚህ ሽወን በማህበረሰባዊና ባህላዊ ዐውድ ይወሰናል። በተሳታፊዎች ጉልህ ሚና ለውጤት ይበቃል። እርቀ ሰላም ይወርድበታል። ተቃርኖ ውስጥ በገቡ ወገኖች መካከል የሚከሰቱ ግጭቶች ተወግደው ወደ ሰላማዊና የተረጋጋ ህይወት ውስጥ ይገቡበታል።

የቅማንት ማህበረሰብ ቀድሞ ጀምሮ ከነበረው የፍትህ ሥርዓት ጎን ለጎን ይጠቀምባቸው የነበሩትን ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት የአሰራር ደንብና ሥርዓት ይዞ በመቀጠል እስካሁን ድረስ በአካባቢው ለሚከሰቱ ግጭቶች በማህበረሰቡ ልማድና ደንብ መሰረት መፍትሄ እየሰጠ ይገኛል። በቅማንት ማህበረሰብ ከቀላል እለታዊ ጠቦች አንስቶ እስከ ከባድ የነፍስ ግድያ ድረስ የሚከሰቱ በርካታ ግጭቶች ይኖራሉ። የግጭቶቹ መነሻዎቹ በአብዛኛው በማህበረሰቡ መካከል ካለ ማህበረሰባዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ አስተዳደራዊና ባህላዊ እውነታዎች ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። በመሆኑም በማህረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጠሩ ግጭቶችን እንደየባህሪያቸውና ደረጃቸው ለመፍታት በባህላዊ የሽወን የግጭት አፈታት ሥርዓት ይጠቀማሉ።

[10] ይህ ቃል በአማርኛ እርቅ መፈጸሚያ እንደማለት ነው።

4.6 በባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ የቀረቡ አቢይ ግጭቶችና ውሳኔዎቻቸው

በዚህ ርዕስ ስር በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ በዋናነት ጎልተው የሚታዩ ግጭቶችና እነዚህ ግጭቶችን ለመፍታት በተለያዩ ተቋማት የተሰጡ ዓይነተኛ ውሳኔዎች ቀርበዋል።

4.6.1 የነፍስ ግድያ

በማህበረሰቡ የነፍስ ግድያን የሚያስታርቁ ወንበሩ ናቸው። ወንበሩ በሰብሳቢነት ተሰይመው ከአካባቢ ሽንጎ አባላትና ከሀገር ሽማግሌዎች ከሃይማኖት መሪዎች ተመርጠው ይጨመራሉ። እነዚህ የሚመረጡ ሽማግሌዎች የገዳይና የሟች ወገን (ዘመድ) ያልሆኑ ፣ ጥሩ ሥነ ምግባር ያላቸው ፣ ተሰሚ የሆኑና በአካባቢው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውና በማስታረቅ ልምድ የተካኑ የዕድሜ ባለፀጎች ናቸው።

በመጀመሪያ በወንበሩ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ ትልቅ ዛፍ ስር[11] በመሆን የገዳይና የሟች ቤተሰቦች ወይም ድርጊት ፈፃሚው ራሱ (ገዳይ) የሚናገሩት ይደመጣል። መቶ አለቃ ጥጋቡ የገዳይ ቤተሰቦች የሚሉትን ሲገልፀ ‹‹ልጃችን ሰይጣን አሳስቶት ወንጀል ፈጽሟል። በእጁ የሰው ህይወት አልፏል። የደረሰበትን በደል ለአካባቢ ሽንጎ መክሰስና ማሳወቅ ሲገባ ባህላዊ ህጉን በመጣስ ጥፋት ስለሰራ እኛንም እንድንረበሽ ፣ እንድሰደድ ስለጋበዘን ከሟች ቤተሰብ ጋር እንድንታረቅ እርዱን ይላሉ›› በማለት ነግረውኛል። ከዚያም ወንበሩ ግድያ የተፈፀመበትን ምክንያትና አካባቢ ይጠይቃሉ። ሁሉንም መረጃዎች አጣርተው ከጨረሱ በኋላ ፀሎት ያደርጋሉ። የተፈጠረው ችግር እንዲቃለል አምላካቸውን ይጠይቃሉ። በአካባቢያቸው የተፈጠረው ግጭት የሰው ህይወት እንዲጠፋ በማድረጉ ፈጣሪያቸው የዚህ አይነት አሰቃቂ ጥፋት ዳግም እንዳይከሰት እገዛ እንዲያደርግላቸው ይማፀናሉ። የሟች ወገንን ልብ እንዲያራራላቸው ፣ ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታም ጭምር ይለምናሉ።

[11] ወንበሩ በጣም ከማርጀታቸው የተነሳ ከቦታ ቦታ እንደልብ አይዘዋወሩም። ስለሆነም ለእርሳቸው ሲባል እርቁ በእርሳቸው ቤት አቅራቢያ እንዲሆን ይደረጋል።

በገዳይ ቤተሰብ ማመልከቻ የቀረበላቸው ወንበሩ ጉዳዩን ከሰሙበት ሰዓት ጀምሮ ለጉዳዩ ክብደት በመስጠት ባዋቀሩት ንዑስ ኮሚቴ አማካይነት እንቅስቃሴ ይጀምራሉ፡፡ የገዳይ ቤተሰቦች ጉዳዩ ተጣርቶ ልጃቸው በወንበሩ ቁጥጥር ስር እስኪገባ ከወንዝ ፣ ከግጦሽ ቦታ ፣ ከለቅሶና ከገበያ አካባቢ ይርቃሉ፡፡ ምክንያቱም የሟች ወገን የሆነ አንድ ሰው ቢያያቸው በስሜት ተነሳስቶ ጥፋት እንዳያደርስ ሲባል ነው፡፡ ስለሆነም የሟችና የገዳይ ወገን የሽወን ሥርዓት እስኪከናወንና ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ ከአንድ ወንዝ ውሃ ቀድተው አይጠጡም ፤ በአንድ ገበያ አብረው አይውሉም ፤ ከብቶቻቸው አንድ ላይ አያሰማሩም ፤ ልጆቻቸው አንድ ላይ አይጫወቱም ፤ በለቅሶና በሰርግ ቦታ አይገናኙም፡፡

ለዚህ ጉዳይ ሲባል በወንበሩ ስር በተዋቀሩት ንዑስ አባላትና በማህበረሰቡ አማካይነት ገዳዩ ያለበት ቦታ ከታወቀ በኋላ ወንበሩና[12] ንዑስ አባላት ወደ ሟች ቤተሰቦች ቤት ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም በቤታቸው በመገኘት የተፈጠረው ነገር በጣም መጥፎ መሆኑን ፣ እነርሱም ጉዳት እንደደረሰባቸው በማንሳት ያፅናናሉ፡፡ ገዳዩም ሰይጣን እንዳሳሳተውና መጥፎ አጋጣሚ መሆኑን አውስተው የዚህ ዓይነት ክስተት እንደሚያጋጥም ይጠቁማሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች ወንበር በማህበረሰቡ በጣም ክብር ያለው በመሆኑ የሚናገሩትን በጥሞና ያዳምጣሉ፡፡ ወንበሩም በመጨረሻ የመጡበት ጉዳይ እርቅ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በማህበረሰቡ ባህል መሰረት እርቅ ቢፈልጉም እንኳን የመጀመሪያ ቀን እሺ ማለት ያልተለመደ በመሆኑ ‹‹እኛ ብቻችን መወሰን አንችልም ስለሆነም ከዘመድ ጋር እንምከርበት›› ይላሉ፡፡ በባህሉ የዚህ ዓይነት ደረጃ ሲደርስ ጥሩ ፍንጭ የሚሰጥ በመሆኑ ሽማግሌዎችና ወንበሩ ፈጣሪያቸው (ምዝገና) ይህን እንደማይወድ ፤ በምድር ላይ ሳለ ይቅር ማለትን እንዳስተማረ ፤ እምነታቸውም ይህን ነገር እንደማይፈቅድ በመግለጽ ‹‹ለሁለተኛ ጊዜ የምንመለሰው ከእናንተ ይሁንታን ለመስማት ነው›› ብለው ተሰናብተዋቸው ይወጣሉ፡፡

ወንበሩ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ሟች ቤተሰብ ዘንድ ከመሄዳቸው በፊት የሟችን ወገን የሚያግባባ ሰው ያመቻቻሉ፡፡ የሟችን ወገን የቅርብ ዘመድ (ከሟች ቤተሰብ ጋር

[12] በድሮው የግድያ ማጭት አፈታት ላይ እንጂ ፣ አሁን አይሄዱም፡፡

በጋብቻ ፣ በአበ ልጅነት ወዘተ. የተሳሰረ) ፣ ጎረቤት ፈልጎ የማግባባትና የማሳመን ስራ እንዲሰራ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ የተመረጡ ሰዎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚችን ወገን ለማግባባት ይጥራሉ፡፡ ከዚያም የሚችን ወገኖች ፈቃደኝነት ሲያስተውሉ በምስጢር ለሽማግሌዎች ይነግሯቸዋል፡፡

ከዚያም ሽማግሌዎች ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ሚች ቤተሰቦች ቤት ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ እንዲያግባቡ የተመረጡትም ሰዎች በሆነ ሰበብ በሚች ቤተሰቦች ቤት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳን ጉዳዩ ውስጥ ውስጡን ያለቀ ቢሆንም ሽማግሌዎች ‹‹ያለፈውን ጉዳይ እምን አደረሳችሁት›› ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ከብዙ ማቅማማት በኋላ የሚች ወገኖች ፈቃደኝነታቸውን ይገልጻሉ፡፡ ሽማግሌዎችም በመደሰት ይደራ አገውተ (ያሰባችሁት ይሳካ) ፣ ይሸሸክብተ ድንገተ ሞትሊ (ከድንገተኛ ሞት ይጠብቃችሁ) እያሉ ይመርቋቸዋል፡፡ ከዚያም ቤት ያፈራው ቀርቦ ይበላል ይጠጣል፡፡

ከዚያም ውጤቱ ለወንበሩ ይነገራቸዋል፡፡ ሽማግሌዎቹ ሃላፊነታቸውን ስለተወጡ ምስጋና ያቀርባሉ፡፡ ከዚያም ቀጠሮ ይሰጧቸዋል ከዚህ በኋላ ገዳዩና ቤተሰቦቹ ለካሳ የሚጠየቀውንና ለእርቅ ማስፈጸሚያ የሚያገለግሉ ነገሮችን ያዘጋጃሉ፡፡ ገዳዩ ሀብትና ንብረት ከሌለው ቤተሰብ የቅርብ ዘመድ እና ጎረቤት ይረዱታል፡፡ ከዚህ በኋላ የሽወን ስርዓት እንዲከናወን በተያዘው ቀጠሮ መሰረት ሽማግሌዎች፣ ወንበሩ፣ የሚችና የገዳይ ቤተሰቦች ገዳዩን ጨምሮ በቦታው ይገኛሉ፡፡
የዚህ ባህላዊ የፍትህ ተቋም የበላይ ወንበሩ በሽወን ሥርዓት ዋና ተዋናይ ናቸው፡፡ እርቁ ከመጀመሩ በፊት ሰይጣን በልባቸው ውስጥ ገብቶ አድሎ እንዲፈጽሙ እንዳያደርግ ምዝገናን (ፈጣሪን) ይለምናሉ፡፡

የገዳይ ቤተሰቦች ለካሳ የሚጠየቁትን ነገር በወንበሩ ትዕዛዝ ሰጪነት ሽማግሌዎች ስለሚያደርሷቸው ለካሳ የተጠየቁትን ሁሉ ይዘው ይቀርባሉ፡፡ እንደ አቅማቸው እና እንደ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ስለሚጠየቁ እንደ በሬ፣ ላም፣ በግ፣ የእህል ዘር፣ ብር፣ ... ይዘው ይቀርባሉ፡፡ ይህ ሁሉ መዘጋጀቱን አፈሊቁ ያጣራል፡፡[13]

---

[13] ይህ መረጃ የተገኘው በቡድን ውይይት ወቅት ነው፡፡

በቅማንት ማህበረሰብ ወንበሩ ፍርድ የሚሰጡት የሚች ቤተሰቦችን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ይህ ሲባል የሚች ቤተሰቦች ጉዳቱ በጣም የከፋ ነው ፤ ሀዘናችንን መቋቋም አንችልም ፤ ከዚህ በኋላ ከገዳይ እና ከቤተሰቦቹ ጋር በአንድ ላይ አንኖርም ፤ ለማህበራዊ እንቅስቃሴያችን እንቅፋቶች ናቸው ፤ ካሉ ከማህበረሰቡ ፣ ከቀየው ፣ ... እንዲሰደዱ (ሀገር እንዲለቁ) ይደረጋል። ይህንን ሃሳብ አስመልክቶ መቶ አለቃ ጥጋቡ እንዲህ ይላሉ ፡-

ይገርምሻል በቅማንት ማህበረሰብ ወንበሩ የግድያን ግጭት በሚፈቱበት ጊዜ የሚች ቤተሰቦችን ሞራል በጣም ነው የሚጠብቁት። እንዴት ካልሽኝ ሚች መሞቱ ከታወቀና ገዳይም ተፈልጎ ከተገኘ በኋላ የሚችን እና የገዳይን ቤተሰብ የማስታረቁ ሂደት ይጀመራል። በዚህ ጊዜ የሚች ቤተሰቦች ሀዘኑ ጎድቶናል ፣ ከአንድ ወንዝ ውሃ ቀድተን አንጠጣም ፤ በአንድ ገበያ አብረን አንውልም ፤ ከብቶቻችን አንድ ላይ አይሰማሩም ፤ ልጆቻችን አንድ ላይ አይጫወቱም ፤ በለቅሶና በሰርግ ቦታ አንገናኝም ብለው አሻፈረን ካሉ ገዳዩም ሆነ ቤተሰቦቹ ፅጣ ፋንታቸው መሰደድ ይሆናል። (መቶ አለቃ ጥጋቡ የካቲት 19/2005 ዓ.ም አይክል) ቃለ መጠይቅ።

4.6.1.1 የደም ካሳ አፈጻጸም

እንደ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቼ[14] አባባል ህግ በሚደነግጉበት ጊዜ ለካሳ ክፍያ አፈፃፀም የሚረዱ ዋናዋና የሆኑ ጉዳዮች አስቀድሞ በደንቡ ውስጥ ይካተታሉ። ከእነዚህም መካከል አቢይ የሆኑት የግድያ አፈፃፀምና የአካል ማጉደል ሁኔታዎች ፣ ጉዳት የደረሰበት ሰው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ማህበረሰባዊ እርከን ፣ ለአካባቢው ህብረተሰብ የጋራ የሆኑ እምነት ስፍራዎች ላይ የሚፈጸም ጉዳት ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች ጋር ካሳ የማይከፈላቸውና ከካሳ የተለየ ልዩ ቅጣት የሚበየንባቸው በእነዚህ የፍትህ አካላት ውስጥ ይካተታሉ።

[14] (መቶ አለቃ ጥጋቡ ዘገየ ፣ አቶ ፍርዱ ነቃ ፣ አቶ እዮብ ድንቁ እና አቶ አየልኝ ተሰማ የካቲት 21/2005 ዓ.ም አይክል) የቡድን ውይይት።

4.6.1.1.1 ሀፊዝ

ይህ ነፍሰ ገዳይ አስቦ ፣ አልሞና ተዘጋጅቶበት በአደባባይ እየፎከረ የሰውን ህይወት ሲያጠፋ ለተፈጠረው ጉዳት መፍትሔ ለመስጠት የሚጠቀሙት የካሳ ክፍያ ዓይነት ነው፡፡ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቹ እንደሚሉት በዚህ የነፍስ ግድያ ግጭቱ ስር እየሰደደ ከፍተኛ የበቀል ደረጃ ላይ ሲደርስ የሚፈጸም ድርጊት ነው፡፡ ገዳዩ ግድያው በግልጽ እንዲታወቅለት እየፎከረ በያዘው መሳሪያ ተጠቅሞ በሰው ላይ ግድያ ይፈጽማል፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በሰብአዊ ፍጡር ላይ ግድያ ሲፈጽም ውሎ ሳያድር የአካባቢ ሽንጎዎችና ወንበሩ ጣልቃ ይገባሉ፡፡ ሁሉም የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች በብቀላ የመጠፋፋት ሁኔታ እንዳይቀጥል በየደረጃው እንዲተባበርና ልቡን እንዲያረግብ በወንበሩ ይጠየቃል፡፡ ነገር ግን እንደ መረጃ አቀባዮቹ አባባል ይህ ጉዳይ አሁን የቀረ ቢሆንም እንዲህ ዓይነት ወንጀል ለፈጸመ ሰው የሚበየንበት ብያኔ የሞት ቅጣት እንደነበር ይገልፃሉ፡፡

4.6.1.1.2 ድንገተ ሞትሊ

ራስን ለመከላከል ፣ ከጨለማ ፣ ካለማወቅና ከባህላዊ የጨዋታ ስርዓቶች ጋር ተያይዞ ለሚከሰት የህይወት ህልፈት ወይም ለአካል መጉደል የሚከፈል ካሳ ነው፡፡ ራስን መከላከል የሚባለው ጨለማን ተገን አድርጎ ወይም በቀጥታም ይሁን በሌላ ከለላ ውስጥ አድፍጦ አንዱ ሌላውን ለመግደል ሲዘጋጅ ሊገደል የታሰበው መልሶ ራሱን በመከላከል ሂደት ውስጥ ህይወት ሲያጠፋ ነው፡፡ ወይም ሌላ የአካል ጉድለት ሲያደርስ ነው፡፡ በዚህ ዓይነት የሚፈፀም ግድያ በድንገተ ሞትሊ ይታያል፡፡ በሌላም በኩል ብርሃን በሌለበት በጨለማ ምክንያት አንዱ ማንንም ሳይለይና የሰውን ህይወት ለማጥፋት ምንም ዓይነት ሃሳብ ሳይኖረው በእርሱ አማካይነት የሰው ነፍስ ሲጠፋ በድንገተ ሞትሊ ደንብ ካሳ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ከዚህም ሌላ በባህላዊ የስፖርት ጨዋታዎች ፣ በአደን ስፍራዎች የሚከሰት የህይወት ህልፈት ወይም የአካል ማጉደል ካሳ የሚከፈለው በድንገተ ሞትሊ ደንብ መሰረት ነው፡፡

4.6.1.1.3 ሂሸንኻ

የዚህ ዓይነት የደም ካሳ በጥንቃቄ ጉድለት ለሚመጣ የህይወት ህልፈት የሚዳርግ የካሳ አፈፃፀም ደንብ ነው፡፡ ለምሳሌ ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አቶ ኢዮብ እደ ነገሩኝ

አንድ ጊዜ አቶ ምትኩ የተባለ ሰው ለስራ ጓደኛቸው ለአቶ ነጋ የጦር መሳሪያቸውን ያውሳሉ፡፡ አቶ ነጋ ደግሞ ባላሰቡት ሁኔታ ሲተኩሱ የሰው ህይወት ያጠፋሉ፡፡ ነገር ግን የአካባቢ ሽንጎ እና ወንበሩ ለጠፋው ህይወት በሂሽነንካ የደም ካሳ ዓይነት ካሳ አስከፈሉት፡፡ በዚህ ደንብ መሰረት የደም ካሳ የሚያስከፍለው የነፍስ ማጥፋት ወይም የአካል መጉደል ድርጊት ፣ ታስቦና ታልሞ የተፈፀመ ባለመሆኑ ለደም ብቀላ ወዲያው መነሳሳት ላይኖር ይችላል፡፡ ይሁንና እንደግድየለሽነት ሊቆጠር ስለሚችል የእርቅ ሂደቱ ወዲያው እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

4.6.1.1.4 ዘመድሻ

ይህ የደም ካሳ ዓይነት በማህበረሰቡ ውስጥ በቤተሰብ ወይም በዘመድ መካከል የነፍስ ማጥፋት ወይም የአካል ማጉደል ድርጊት ሲፈፀም ነው፡፡ ለምሳሌ ወንድም ወንድሙን ወይም ወንድም እህቱን ፤ እህት ወንድሟን ወይም እህቷን... ቢገድል የደም ካሳ የሚፈጸመው በዚህ ህግና ደንብ መሰረት ነው፡፡ ወንድም ወንድሙን ቢገድል ደም ለመበቀል የሚደረግ እቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ አይኖርም ባይባልም ጎልቶ ግን አይታይም፡፡ ይሁንና ሟቹ ልጆች አፍርቶ ከሆነ በቀዳሚነት በልጆቹ ውስጥ የብቀላ መንፈስ ሊጠነሰስ ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡ ‹‹ሚስቱም ልጆቿን ያለ አባት አስቀርታለች፡፡›› ብላ ወንድሞቿና ሌላ ቤተዘመዶቿን ይዛ ለብቀላ ልትነሳ እንደምትችል ማህበረሰቡ ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

ከዚያም በባህሉ መሰረት ነፍሰ ገዳይ እጁን ለወንበሩ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ ወግና ስርዓቱ በሚፈቅደው መሰረት ፈጣሪያቸው ሰላም እንዲያወርድላቸው ፣ የተፈጠረውን ግጭት እንዲፈታላቸው ፣ የሟቹን ነፍስ እንዲምርላቸው ይለምናሉ፡፡ ሁሉም ቤተሰብ ፣ ሌላ ዘመድ ፣ ተሰብስበው በአንድ ላይ ለሞተው ሰው ያለቅሳሉ፡፡

4.6.2 ከህብትና ከንብረት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች

እነዚህ መሬትን ፣ ድንበርን ፣ የግጦሽ ቦታን ፣ የከብት ዝርፊያን ፣ ብድርንና የመሳሰሉትን ምክንያት አድርገው የሚነሱ ጸቦች ናቸው፡፡ በቅማንት ማህበረሰብ ብዙውን የከብት ዝርፊያ ያጋጥማል፡፡ ዝርፊያዎቹ ደግሞ የሚፈጽሙት በስውር በመሆኑ ዘራፊውን ለማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ከብቱ የጠፋበት ሰው ወደ መንግስት አካላት ከማመልከት ይልቅ የከብቱን ወላጅ ማንነት ለማወቅ እና

እንዲውጣጣለት በቅድሚያ ለአካባቢው ሽንኑ ያሳውቃል። ሰርቋል የተባለው ተጠርጣሪ የእምነት ክህደት ቃል እንዲሰጥ ይደረግና ባያምን እና ማስረጃ ባይገኝበትም የተሰረቀው ሰው ግን ይግባኝ ካለ በአፈሊቁ አማካይነት ጉዳዩ ወደ ወንበሩ ይመራና ወንበሩ እንዲምል ይጠይቁታል። በዚህ ጊዜ ምዝገና በህሰት መማልን አላስተማረንም ስለዚህ እውነቱን እናገራለሁ በማለት ወስጃለሁ ወይም አልወስድም ብሎ ይናገራል። አቶ አየልኝ ተሰማ በድሮ ጊዜ ከብት ሲጠፋ እንዴት በአውጫጭኝ ሲጠቀሙ እንደነበር በትውስታ እንዲህ ይላሉ፡-

ድሮ አንድ ከብት ሲሰረቅና የወሰደው ሲጠፋ ትልቅ አውጫጭኝ ይደረጋል። በዚያን ጊዜ አውጫጭኝ በጣም ትልቅ ጉዳይ ነበር። አንድ ጊዜ አቶ ነጋ የሚባሉ ሰው ናቸው ጊደራቸው ተሰረቀች። እናም ጉዳዩን የአካባቢ ሽንኑዎች ስላልፈቱት በአፈሊቁ አማካይነት ወደ ወንበሩ ይግባኝ ይላሉ። ወንበሩ አውጫጭኝ ጠርተው ሊባው ለጊዜው ተደበቀ። ነገር ግን በጓላ ከገባበት ጎሬ ይዘው አመጡት። እና አውጫጪኝ ጥሩ ባህል ነበር በድሮው። አሁን ከአካባቢ ሽንኑና ከወንበሩ ጋር በመሆን ህዝቡ አብሮ የሚሰራው ነው። (አቶ አየልኝ ተሰማ መጋቢት1/2005 ዓ.ም ቁልጋ አይከል ከተማ) ቃለ መጠይቅ።

ከአቶ አየልኝ ንግግር መገንዘብ እንደሚቻለው በአብዛኛው የሚፈጠሩት ግጭቶች ማስረጃ የለሽና በስውር የሚፈጸሙ በመሆናቸው የሚፈቱት በአካባቢ ሽንኑና በወንበሩ ወይም በባህላዊ ተቋማቱ እንደሆነ ነው። በተለይም አውጫጭኝ የተባለው ጉዳይ በድሮው ጊዜ ማህበረሰቡ እንደ ትልቅ ተቋም የሚቆጥረውና ስውር ወንጀሎችን ለማግኘት የሚጠቀምበት ዘዴ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

4.7.2.1 የቤተሰብ ፀብ

እነዚህ ከጋብቻ ፣ ከልጆች ፣ ከውርስ ወዘተ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ግጭቶች ናቸው። በቅማንት ማህበረሰብ በቤተሰብ መካከል ግጭት ሲኖር በቅድሚያ የተጋጭዎቹ የቅርብ የሆነ ሰው በእነሱ አጠራር ‹‹የቤተ ዘመድ ጉባኤ›› መፍትሄ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። በተለይም ጉዳዩ ከውርስ ጋር የተያያዘ ከሆነ ሌላ (ባዕድ) ሰው እንዳይገባባቸው ሲባል ይህ ይደረጋል። ይህ ካልሆነ

ደግሞ በመጀመሪያ ወደ አካባቢ ሽንኑ ይሄዳሉ፡፡ አቶ አየልኝ ይህንን ጉዳይ እንዲህ በማለት ያብራሩታል፡፡

በቤተሰብ መካከል ግጭት ሲከሰት በቅድሚያ የቤተ ዘመድ ጉባኤ ተብሎ ይሰየምና እንዲዳኙቸው ፣ እንዲያስታርቃቸው ይደረጋል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ በተለይ ግጭቱ በውርስ እንደሆነ ፤ ‹‹በእናት በአባታቸው ገንዘብ ተፋጁ እያለ›› እንዳይሳቅባቸው የቅርብ የሆነ ፣ ገመና የማያወጣ ሰው ይሻላል ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ ይህ ታልሆነ ግና ያው እንደተለመደው ፣ እንደአባቶቻቸው ደንብ ውደ አካባቢ ሽንኑ መሽድ ነው፡፡ (አቶ አየልኝ ተሰማ መጋቢት 1/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ፡፡

4.7.2.1.1 በቅማንት ማህበረሰብ የባልና ሚስት ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት አውዳዊ ክዋኔ

ጋብቻ በአንድ ማህረብሰብ ባህል ፣ እምነት ፣ የኑሮ ደረጃና የአኗኗር ዘይቤ ሁኔታ የሚወሰን እና የሚዳኝ ነው፡፡ በምግባሩም ከወሲባዊ ስሜት ማርኪያነት ያለፈ ቤተሰባዊ አካልን ለመመስረትና የወደፊቱን ዜጋ ለመተካት የሚያስችል የህብረተሰቡ መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሁለት ተቃራኒ ጾታዎች ከብቸኝነት ኑሮ ልማድ ተላቀው ትዳር መስርተው በጋራ የሚኖሩበት ፣ መንገድ የሚቀይሱበት ፣ በህብረተሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡ የህብረተሰብ መሰረት የሆነው ቤተሰብ መመስረቻ ማዕከልም ነው፡፡ ቀድሞ የነበሩትን የህይወት መስመር በመተው ወደዚህ በሃላፊነት ወደተሞላው ተቋም ለመሸጋገር የፈለጉ ሁለት ተጣማሪዎች ወደ ጋብቻ ሲገቡ በልባቸው የመፈቃቀድ ስሜት ሊኖር ይገባል፡፡ ወደፊት ሊገጥማቸው የሚችለውን ነገር ከወዲሁ አውቀው እና በሥነ ልቦናም ሆነ ለማህበረሰባዊ ተጽዕኖ ገጽታዎች ቅድመ ዝግጅት እና አካላዊ ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው አልፎ አልፎ ግጭት መፈጠሩ የማይቀር ነው፡፡ ለግጭቱ መንስኤ የሚሆኑት ደግሞ ባል ወይም ሚስት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ባልና ሚስት ኑሯቸውን ለማሸነፍና የተሳካ ለማድረግ የበኩላቸው ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ የኑሮ ውጣ ውረድ እንቅስቃሴ የጋራ ጥረታቸው ተሳክቶ የተቃና ሰላማዊ ህይወት እንዳይኖሩ የሚያደርጉ መሰናክሎች ይፈጥራሉ፡፡ ባልና ሚስት

አብረው በጋራ መኖር ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ከውጪ በሰው ጣልቃ ገብነት ወይም በራሳቸው ምክንያት የሁለቱም ሰላማዊ ኑሮ ቀስበቀስ እየተናጋ እስከ መፋታት የሚደርሱበት አጋጣሚ አለ። እነዚህም እንደ ሀብታሙ (1998 ፡ 19) ገለፃ የወሲብ አለመጣጣም እና የገንዘብ አቅም ማነስ በባልና ሚስት መካካል ለሚከሰቱ ግጭቶች ዋነኛ ጉዳዮች ናቸው። "Sexual incompatibility and financial problems are the main causes for conflicts between husbands and wifes.››

በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች በባልና ሚስት መካከል ግጭት ይፈጠራል። በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ባልና ሚስት ቅራኔ ውስጥ ሲገቡ እንደ ግጭቱ ቅለትና ክብደት በጎረቤት ፣ በሁለቱ ቤተሰቦች ፣ እና በጓደኞቻቸው ቅራኔውን ለመፍታት ይሞክራሉ። የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት በሁለቱ መካከል ያልተግባቡበትን ጉዳይ ለመፍታት ጠቀሚታ አለው። ይህንን ሃሳብ ለማጠናከር ሀብታሙ ወንድሙ በሶስተኛ ወገን የሚከናወን እርቅ ግጭትን ለማስወገድ ጠቃሚ እንደሆነ የገለፁትን ሃሳብ ማንሳት ተገቢ ነው። ‹‹mediation and arbitration by a third party and accommodating the disagreements and conflict are some of the main techniques of conflict resolution in most families.›› (1998 : 71)

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ምንም እንኳን ሴት ከ15 ዓመት በላይ ወንድ ደግሞ ከ25 ዓመት በላይ እንዲጋቡ የሚወስን ባህላዊ ህግና ደንብ ቢኖራቸውም ፤ ዞሮ ዞሮ ‹‹ከሰው ልጅ ስህተት ከብረት ዝገት አይጠፋም›› እንዲሉ በተለያዩ ምክንያቶች መንስኤነት ግጭት ይፈጠራል። ጎላ ጎላ ብለው የሚጠቀሱትን መንስኤዎች እንመልከት ፦

ሚስት በቤት ስራ እና በንብረት አጠቃቀም ረገድ ጉድለት ሲታይባት ፤ ለምሳሌ በወጥ አሰራር ፤ እንጀራ አገጋገር እና ሌሎች ቤት ውስጥ ያሉ በሴትየዋ የሚሰሩ ነገሮች ጉድለት ሲታይባት ፤ ባል የእርሻ ስራውን ትቶ በየመንደሩ የሚዞር ሲሆን ከዚህም የተነሳ ቤተሰቡ ለረሃብ ሲዳረግ ፤ ባል ከሚስቱ ውጭ በድብቅ ከሌላ ሴት ጋር ዝሙት ሲፈጽም (ቀደም ሲል ለሚስቱ የነበረው ፍቅር እየቀነሰ በመምጣት ወይም ይህ ሁኔታ በአጋጣሚ ከሚስቱ ጆሮ ደርሶ ሚስቱ በቅናት መንፈስ ተነስታ ለስድብና ለጥል ስትጋብዝ) ፤ ባልየው ከውጭ ስራ ሰርቶ ውሎ ደክሞት ፤ ርቦት ሲመጣ

ሚስትየው ክብር ሳትሰጠውና ምግብ ሳታቀርብ ስትቀር ፤ ባል ሰርቶ የሚያገኘውን ገንዘብ ለመጠጥ በማዋል ብሎም ወደ ቤቱ ገብቶ ሚስቱን ሲደበድብ ፣ ለመጠጥ የሚያጠፋው ገንዘብ በቤተሰቡ ላይ ችግር እያስከተለ መሆኑን በተደጋጋሚ ስትነግረው ምክሯን ሳይቀበል ሲቀር ፣ የባል ቤተሰቦች (እናት ፣ አባት ፣ እህት) አብረው የሚኖሩበት አጋጣሚ ሲኖር እና ለሚስቱ ጥሩ አመለካከት ካለመኖራቸው የተነሳ አለባልታ በማናፈስና ለባል በማድረስ ባልና ሚስት የሚፈጥሩት ግጭት ፣ ከሁለቱ መካከል በአንዱ በሚፈጠር የጤና ችግር ምክንያት በእነዚህ ምክንያቶች ግጭት ሲፈጠር በቅድሚያ ወደ አካባቢ ሽንኑ አባላት ይኬዳል።

ባልና ሚስት በጓደኛ ፣ በጎረቤት ፣ ብሎም በቤተሰብ ግጭቶቻቸው ካልተፈቱ በመጀመሪያ ወደ አካባቢ ሽንኑ ይሄዳሉ። በዚህ ደረጃ ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት የግጭታቸው መንስኤ ይመረመራሉ። ጉዳዩን ከመረመሩና ካጣሩ በኋላ ስህተት የፈጸመው አካል ተመክሮ ከመጥፎ ድርጊቱ እንዲመለስ ይነግረዋል። ዳግምም ጸብ ላይጭር ቃል ይገባል። እርቅ ተከውኑኖ በሰላም እንዲኖር ይደረጋል። ነገር ግን አሁንም ጉዳዩ ወደ ተባባሰ ደረጃ ደርሶ ከአካባቢ ሽማግሌዎች አቅም በላይ ሲሆን በአፈሊቂ አማካይነት በወንበሩ እንዲዳኙ ይደረጋል። በወንበሩ ተዳኝተው እልባት ወይም ውሳኔ ካልተሰጠው ግን በሰላም እንዲለያዩ ይደረጋል።


እኔ የመስክ ጉብኝት ባካሄድኩበት ወቅት የባልና ሚስት ግጭት በአካባቢ ሽንኑ ዳኝነት ሰጭዎች ሲካሄድ የማየት ዕድል አጋጥሞኝ ነበር።

ባል አቶ ማሩ ሞልቶታል እና ሚስት ሺማጫሽ ጥሩነህ ከሁለት ወር በፊት ይጣሉና ጉዳያቸው በቤተሰብ ፣ በጉረቤት ፣ እንዲሁም በአካባቢ ሰዎች እልባት ስላላገኘ ጉዳያቸውን ወደ አካባቢ ሽንኑ ይዘው ይመጣሉ። የአካባቢ ሽንኑ ያለበትን ጉዳዮች ከግምት ወስጥ አስገብቶ ከ15 ቀን በኋላ እንዲመጡ ቀጠሮ ሰጥቶ ያሰናብታቸዋል። በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ የባልና ሚስት ጉዳይ ወደ አካባቢ ሽንኑ ሲመጣ ዕለታዊና ቀላል ችግር ነው ለግጭት የሚዳርገው ብለው ስለሚያስቡ የቤታቸውን ገመና ሽማግሌ ከመስማቱ በፊት ራሳቸው ቤት ውስጥ እንዲታረቁ በማሰብ ረዥም ቀጠሮ

ይሰጣል፡፡ ባልና ሚስትም ጉዳያቸው በነዚህ ቀናትም ያልተፈታ በመሆኑ በቀጠሯቸው ቀን የካቲት 30/2005 ዓ.ም በቦታቸው ይገኛሉ፡፡

በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ባልና ሚስት ሲጣሉ ባል ሽማግሌዎችን በማነጋገር ወይም ሰው በመላክ እርቅ ይጠይቃል፡፡ ከዚያም ቀኑ ተቆርጦ ሽማግሌዎች ሁሌም ዳኝነት በሚሰጡበት ስፍራ ይቀመጣሉ፡፡ በዚሁ ዕለት ወንበሩ ዳኝነቱን ለመታዘብ በቦታው ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን ታዛቢ እንጂ ተሳታፊ አይሆኑም፡፡ ሽማግሌዎች ቦታ ቦታቸውን እንደያዙ ባልና ሚስት ጥግ ይዘው መጨቃጨቅ ይጀምራሉ፡፡ ሽማግሌዎችም ባልየውን በመጥራት የግጭታቸውን መንስኤ እንዲናገር ይጠይቁታል፡፡ ባልም ‹‹ የበደልኳት ነገር የለም፡፡ ልጆችን እናሳድግ ነው እያልኩ ያለሁት፡፡ እሷ ግና አሻፈረኝ እያለች ናት፡፡ እና ያገሬ ሽማግሎች ፣ አባቶች እባካችሁን ለምኑልኝ፡፡›› ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ጭልጋ/አይከል፡፡ ይላል፡፡

ሽማግሌዎች የእርሱን ሃሳብ ካዳመጡ በኋላ የሚስቱ አባት እንዲጠሩ ያደርጋሉ፡፡ አባትም የልጃቸውን በደል ይገልጹና እንዲያስታርቁላቸው ይለምናሉ፡፡ ይህንን የሰሙት ሽማግሌዎች ሚስትየዋን ለብቻ ጠርተው ምን እንደተበደለች ያናግሯታል፡፡ እርሷም የተበደለችውን በሙሉ ትዘረዝራለች፡፡ ‹‹ይጠጣል፡፡ ይሰክራል፡፡ ስራ አይሰራም፡፡ ልጆቼ ተርበዋል ፣ በዚህም ምክንያት ከቤት ወጠዋል፡፡ ፣ አልከርምም ፤ እኽዳለሁ፡፡›› ትላለች፡፡ ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም

ግጭት ውስጥ የገቡት ባልና ሚስት በየተራ እየመጡ ሲጠየቁ

ሽማግሌዎችም ‹‹ እባክሽ ተለመኝ መጪው ክረምት ከባድ ነው ፤ ዝናብ እየዘነበ አትኽጅ፡፡ ልጆቻችሁን አሳድጉ፡፡›› ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ጭልጋ/አይከል፡፡ ብለው ይለምኗታል፡፡ እርሷም ‹‹በፍጹም አይሆንም፡፡›› ትላለች፡፡ በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ ቆመው ይለምኗታል፡፡ ‹‹እባክሽን ልጆቻችሁን አትበትኑ፡፡ አብራችሁ አሳድጉ፡፡ ቤታችሁን አታፍርሱ፡፡ ሀብት ንብረታችሁን አታባክኑ፡፡ ለልጆቻችሁ ቅርስ ለማቆየት የናንተ መስማማት ጥሩ ነውና እባክሽን ተለመኝ፡፡ ሰው ይክበድሽ፡፡ ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ጭልጋ/አይከል፡፡ ብለው ይለምኗታል፡፡



ሽማግሌዎች ሚስትየዋን ከመቀመጫቸው በመነሳት ሲለምኑ

በመጨረሻም አባቷ ከመቀመጫቸው ተነስተው ‹‹ ሰው ሁኖ የማይበድል ወይ የማይበደል የለ ልጄ ምን ሁነሽ ነው፡፡ ሁሉም ሰው ተደስቶ ወይም ደልቶት አይኖርም ፤ ግን ቤት የሚያዘው ልጅ የሚያድገው እንደዚህ ተሁኖ ነው፡፡ እባክሽን ልጄ›› ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ጭልጋ/አይከል፡፡ ብለው ይለምኗታል፡፡ ሚስትየዋም ‹‹ይሽ ባሪውን ታስተካክለ እኔ ምን ገደደኝ›› ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ጭልጋ/አይከል፡፡ በማለት እሽታዋን ትገልጻለች፡፡ ከዚያም ባልየው በእርቁ ተደስቶ ሽማግሌዎችን በሙሉ እየዞረ ጉልበት ይስማል፡፡ ምስጋና ያቀርባል፡፡



አባቷም ‹‹እግዚአብሄር ይስጥልኝ ፣ እናንተን አያሳጣን ፣ አይለያየን ፣ አገራችን ሰላም ያርግልን›› ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ጭልጋ/አይከል፡፡ ብለው ምርቃት እና ምስጋና ያቀርባሉ፡፡



አባቷ ለሽማግሌዎች ምስጋና ሲያቀርቡ

ወንበሩ ከመቀመጫቸው በመነሳት ‹‹ትዳራችሁን ያለምልመው ፣ ሰው የወደደው ምዝገና የወደደው ነውና ሰው ይውደዳችሁ ፣ እርቁን የእውነት ያድርገው ፣ በመካከላችሁ የገባውን ምዝገና አመድ ያድርገው ፣ ጠላታች ይጥፋ ፣ ልጆቼ አትለያዩ ዛሬ ግዜው ከፍቶ እንጂ እንኳን ባልና ሚስት ባላንጀራም ሆነን በአንድ አጎዛ ሦስት አራት ሁነን ነበር ምናድር እና ሰላም ግቡ ፣ ሰላም ሁኑ›› ቅዳሜ የካቲት 30/2005 ዓ.ም ጭልጋ/አይከል፡፡ብለው ይመርቃሉ፡፡ በዚህ ዓይነት መልኩ የእርቁ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ጸብ ውስጥ ገብተው የነበሩት ባልና ሚስት ለሽማግሌዎች የሚበላ እና የሚጠጣ እንጀራ ፣ ወጥና ጠላ አዘጋጅተው ስለ ሚመጡ ለሽማግሌዎች ይቀርባል፡፡[15]

[15] በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ በማንኛውም ደረጃ ለሚካሄድ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ግጭት ውስጥ የገቡ ተጋጭዎች ለዳኝነት ለተቀጠሩበት ቀን የሚሆን እህል ውኃ ቀድመው ያዘጋጃሉ፡፡ ምክንያቱም እርቅ ተፈጠረም እርቅ አልተፈጠረም ሽማግሌዎች ከቤታቸው የሚበላ ነገር ሳይቀምሱ ነው የሚመጡት እናም ለነርሱ ሲባል ግዴታ ይዘጋጃል፡፡



ከእርቅ በኋላ ለሽማግሌዊች ምግብ ሲቀርብ

4.7.3 ጠለፋ

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ሴትን ልጅ በፍላጎት ወይም በኋይል አስገድዶ በመውሰድ የትዳር ጓደኛ ማድረግ የተለመደ ነው። ነገር ግን በዕድሜ ይገደባል። ማንኛውም በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ያለ ጉብል (ወጣት) አንዲትን ልጃ ገረድ ከ15 ዓመት በፊት ጠልፎ አይወስዳትም። ምክንያቱም በማህበረሰቡ ዘንድ ጋብቻም የሚፈቀደው ከጥንት ጀምሮ ከ15 ዓመት በላይ ነው። ለዚህ ደግሞ ምንጫቸው ምዝገና (ፈጣሪ) በእምነታቸው እንዳስተማራቸው ሴትን ልጅ ከ15 ዓመቷ በፊት መገናኘት በጣም በጥብቅ የተከለከለ እንደሆነ ነው።

በማህበረሰቡ ዘንድ ድርጊቱ የሚከናወነው በሁለት መንገድ ነው። የመጀመሪያው በመፈቃቀድ /በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ጠላፋ ነው። ይህም ጠለፊው ከምትጠለፈው ልጅ ጋር ተግባብቶ በወያየት የሚፈጸም ነው። ሁለቱ መግባባትና መፈቃቀራቸው እየጠነከረ ሲመጣና ከሁለቱ ቤተሰቦች የአንደኛው መጋባታቸውን የማይፈልጉ መሆኑን ሲያረጋግጡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ልጁ ጠልፎ እንዲወስዳት ተስማምተው የሚፈጽሙት ነው።

ሌላው የጠለፋ አፈጻጸም በወንዱ ውሳኔ በጉልበት የሚደረግ ነው። ይህን ድርጊት የሚፈጽመው አካል ከልጅቱም ሆነ ከቤተሰብ ፈቃደኝነት ሳይኖር ሲቀር ነው።

ከፍላጎት ውጭ የሚከናወን ጠለፋ በማህበረሰቡ የማይፈለግና ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር ነው፡፡ ምክንያቱም የሴቷን ፍላጎት አይጠብቅም፡፡ በዚህም ምክንያት በተጠላፊዋ ልጅ ላይ አካላዊና አዕምሯዊ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ይህን ጉዳት የተጠላፊዋ ቤተሰቦች ስለሚረዱ የተጠላፊዋ ቤተሰቦችና ጠላፊው ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ከፍላጎት ውጭ የሚፈጸም ጠለፋ ብዙ ችግር አለበት፡፡ በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ለጠለፋ መከናወን ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች ፡-

- በይተንቲና ይተንቲ የዘር ሀረግ ወይም በክብርና ክብር የዘር ሀረግ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ለጋብቻ ሲፈላለጉ እና ለቤተሰቦቻቸው ሲያሳውቁ ቤተሰቦቻቸው ፈቃደኛ ስለማይሆኑ፤ [16]
- የልጁ ስንፍና ፣ መጥፎ ባህርይ ፣ እና ኑሮውን በአግባቡ ለመምራት አይችልም የሚለው ጉዳይ በቤተሰቦቿ እና በልጅቷ የሚታወቅ ከሆነ ለትዳር ሲጠየቁ ልጅም ቤተሰብም ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡
- በልጅቱ ውበት በመማረክ ድንገተኛ ፍቅር ይዞት ግብታዊ በሆነ መንገድ ተነሳስቶ የሚፈጸም ፤
- በገንዘብ እጦት ምክንያት ለጥሎሽ የሚከፈል ሃብት ሳይኖረው ሲቀር ፣ በድርድር ማግኘት እንደማይቻል ሲረዳ ጠለፋን እንደ አማራጭ መጠቀም የሚሉት ናቸው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ጠለፋ ሲፈጸም ፤ ጠላፊው የጠለፋትን ልጅ በስውር ቦታ ያስቀምጣታል፡፡ ጠላፊው ከቤተሰቡ ሳይመካከር የፈፀመው ከሆነ የቅርብ ዘመድ ጋር ሄዶ መጥለፉን ለወላጆቹ እንዲነግሩ ያሳውቃል፡፡ ይህም ለሁለት ነገር ይጠቅመዋል፡፡ የመጀመሪያው የጠለፈው እሱ መሆኑ ከታወቀ የልጅቷ ቤተሰቦች በቤተሰቦቹና በቅርብ ዘመዶቹ ላይ አደጋ እንዳያደርሱ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ሁለተኛው ማግባት መፈለጉንና በራሱ ፈቃድ ጋብቻ መመስረቱን በማሳወቅ እውቅና ለማግኘት ነው፡፡

[16] በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ በምዕራፍ ሦስት እንደተጠቀሰው የይተንቲ የይተንቲን የክብር ዘር የክብርን ማግባት አይችሉም፡፡ ምክንያቱም የስጋ ዝምድና አለ ብለው ስለሚያስቡ

የልጅ ቤተሰቦች የዚህ ዓይነት ዱብ እዳ ሲመጣ ይረበሻሉ። ሃሳብ ውስጥ ይገባሉ። እኛ በአግባቡ መኖር ስንችል ሳንዘጋጅ የዚህ ዓይነት ነገር መደረግ አልነበረበትም ብለው ይቆጣሉ። ከሰው ጋር ልታቃቅረን ነው ብለው ይበሳጫሉ። ቤተ ዘመድ ተሰብስቦ የሆነው ሆኗል የሚያዋጣው መፍትሔ መፈለግ ነው በማለት ያግባባል። ቤተሰብም እውቅና ይሰጣል። የአካባቢውን ሰው በመጥራት የተወሰነ ዝግጅት ያደርጋል። ባልና ሚስት መሆናቸውን የልጁ ቤተሰብና ዘመድ እንዲያውቁ ያደርጋል።

ያለፍላጎቷ ልጃቸው የተጠለፈባቸው ቤተሰቦች የጠለፈውን ልጅ የሚያውቁት ከሆነ ወይም ጥቆማ ከደረሳቸው በተፈፀመው የጠለፋ ድርጊት ይበሳጫሉ ፤ ከፍተኛ ድፍረትና ጥቃት እንደተፈጸመባቸው ስለሚሰማቸው የክብራቸው መነካት እንደ እግር እሳት ያንገበግባቸዋል። ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ አቶ ፍርዱ ነቃ እንዲ ይላሉ፡-

በአመንት ልጅ የተጠለፈችበት አባት ጥቃቱ መቼም እንደግር እሳት ያቃጥለዋል። ተዋረድኩ ፤ ተናኩ ፤ ተደፈርኩ ብሎ እሪ ይላል። የልጅም ቤተሰቦች አሞ አጥፍተናል ፤ እንክሳለን ፤ ይቅር በሉን ይላሉ። ተዚያ በኋላ የልጅቷ ቤተሰቦች እሺ ታሉ በቃ ፅዳው ገብስ ነው። ድግስ ይደገሳል ፤ ሰርጉ ይፋ ይሆናል ፤ አስታራቂዎች (የአካባቢ ሽንጎዎች) በወሰኑት እና ማንበሩ ባላሰቡ ካሳ ይቀበላሉ የልጅቷ ወገኖች ተዚያ በኋላ እርቅ ይወርዳል። ሰላም ይፈጠራል። ድርጊቱ ግን በማህበረሰቡ በጣም የተጠላ ነው። (አቶ ፍርዱ ነቃ የካቲት 19/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ።

የልጁ ቤተሰቦች ልጃቸው ጉዳዩን መፈፀሙን ካረጋገጡበትና ለጋብቻው እውቅና ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ቀጣዩ ስራቸው ለካሳና ለጥሎሽ የሚሆን ነገር እና አስታራቂ ሽማግሌዎችን ማዘጋጀት ነው። ሽማግሌ ወዲያውኑ ነው ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች የሚላከው ምክንያቱም የልጅቷ ቤተሰቦች ተንቀናል በሚል ሃሳብ የከፋ አደጋ ሊያደርሱና ይችላሉና። ነገር ግን ሽማግሌ በወቅቱ ከተላከ በእርቅ ስነ ስርዓቱ ወቅት መካረር እንዳይኖር ያግዛል።

ለእርቅ የሚላኩት ሽማግሌዎች ከተመረጡ በኋላ በጠላፊው አባት ቤት ተሰብስበው ይመክራሉ፡፡ ዕቅድ ያወጣሉ፡፡ ጉዳዩን ለአካባቢ ሽንጎ ያሳውቃሉ፡፡ የአካባቢ ሽንጎ አባላትም በቅድሚያ የልጅቷን ቤተሰቦች እንዲጠይቁ እና እንዲያግባቡ ከዚያም ወደ ተቋሙ ይዘዋቸው እንዲመጡ ይነግሯቸዋል፡፡ በልጁ ቤተሰብ ቤት የሚበላና የሚጠጣ ከቀመሱ በኋላ ፀሎት በማድረግ ፈጣሪያቸው ይለምናሉ፡፡ የሚሄዱበት ጉዳይ የተሳካ እንዲሆን አምላካቸው እንዲረዳቸው ይማጸናሉ፡፡ የልጁ አባትና እናት ‹‹መንገዱን ቀኝ ያድርግላችሁ ፤ ሰዎችን ያራራላችሁ›› ብለው ይሸኟቸዋል፡፡

እርቅ ለማውረድ የተላኩት ሽማግሌዎች ወደ ልጅቱ ቤተሰብ ቤት በቀጥታ አይገቡም፡፡ ከቤተሰቦቿ መኖሪያ ቤት አካባቢ ከሚገኙ ጎረቤቶች መካከል ለልጅቷ ቤተሰቦች የሚቀርቡትንና የሚግባቡትን በመምረጥ እና አብረዋቸው እንዲሄዱ በማድረግ እንጂ ከዚያም ከሽማግሌዎች ጋር አብሮ የሄደው ሰው ቀስ በቀስ እያዋዛ ‹‹ሰዎች መጥተዋል፡፡ እርቅም ጠይቀዋል፡፡›› በማለት ይናገራል፡፡ ጎረቤት በመሆኑና የሰዎችን ባህርይ በማወቁ ንግግሩ ሁሉ ጥንቃቄ የተሞላበት ነው፡፡ በባህሉ በጠለፋ እርቅ በመጀመሪያ ቀን እሺ አይባልም፡፡ ጠላፊው እና ቤተሰቦቹ መጨነቅ አለባቸው ምክንያቱም ችግሩን በመጨነቅና በመጉላላት ካላዩት ሌላው የቤተሰቡ አባል ደግሞ ሌላ ጠለፋ ሊያካሂድ ይችላል ተብሎ ስለሚታመን ከዚያም ከ20 ቀን በኋላ እንዲመጡ ይነገራቸው እና በቀጠሮ ይለያያሉ፡፡

ሽማግሌዎች በቀጠሮ ቀን ሲሄዱ ሰላምታ ተለዋውጠው ሁሉም ሽማግሌዎች እንደቆሙ ‹‹ጥፋት ፈጽመናል ፤ ስህተት ሰርተናል ፤ አጥርዎን ሰብረናል ፤ ቤቱንም ደፍረናል ፤ ክብርዎን ገፈናል ስለሆነም ጥፋታችንን አምነን ልንክስ መጥተናል›› ይላሉ፡፡ የልጅቷ አባት እንዲቀመጡ በምልክት ያሳይዋቸዋል፡፡ ከዚያም ፊታቸው ሲያገኙ ‹‹እሺ›› ብለው ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያ ሽማግሌዎች ጉዳዩን የአካባቢ ሽንጎ መርምሮት የጠየቃችሁትን ሁሉ ልንክስ ዝግጁ ነን እና እባካችሁን በአካባቢ ሽንጎ ታረቁልን ብለው ይለምናሉ፡፡ ከዚያም እሺ ይባሉና ቤት ያፈራውን ቀማምሰው ቀጠሮ አስይዘው ይሄዳሉ፡፡

በቀጠሮው ቀን የአካባቢ ሽንጎ በተገኘበት የልጁም የልጅቷም ቤተሰቦች እና የተመረጡት ሽማግሌዎች ይገኛሉ። በቅድሚያ ዕድሉ የሚሰጣቸው ሽማግሌዎች ናቸው። እነርሱም የተፈጸመውን ገልፀው ነገር ግን የልጅቷ ቤተሰቦች በብስጭት ጥፍት ባለማድረሳቸው ፤ ተበደልን ብለው ክስ ባለመጀመራቸው ፤ ወደዚህ ባህላዊ የፍትህ ተቋም ለእርቅ በመምጣታቸው ያመስግኗቸዋል። ከዚያም የልጅቷ እና የልጁ ቤተሰቦች እንዲናገሩ እድል ይሰጣቸዋል። የልጅቷም ቤተሰቦች ‹‹የተፈፀመብን ጥቃት የሚያሳምም ቢሆንም ለወላጆቹ ስንል ፤ ለቀሪው ቤተሰብ ስንል ፤ አብሮ ለመኖር ላለመለያየት ስንል ያቅማቸውን ክሰው እንድንታረቅ መጥተናል›› ይላሉ የልጁም ቤተሰቦች ‹‹ምዝገና የሚወደውን ፤ ያስተማረውን አድርጋችሁልናል እና በጣም እናመሰግናለን፡ አቅማችን የፈቀደውንና በወንበሩ ትዕዛዝ ካሱ የተባልነውን ሁሉ እንክሳለን።›› ይላሉ። ከዚያም ወንበሩ እንዳዘዙት በሬ ፤ ላም ፤ በግ ፤ የእህል ዘር ፤ ብር ወዘተ ያቀርቡና የልጅቷ ቤተሰቦች በቤታቸው ባዘጋጁት ድግስ እንዲታደሙላቸው ይጋብዛሉ። ልጅቷም ቤተሰቦች የሚያገናኙበትን ቀን ቆጥረው እና እርቁ ተፈጽሞ ይለያያሉ።

የልጁ እና የልጅቷ ቤተሰቦች በሚገኙበት የቀጠሮ ቀን ጠላፊው እና የተጠለፈችው ኮረዳ ከተደበቁበት በመውጣት ወደ ልጁ ቤተሰቦች ቤት ይመጣሉ። የልጅቷ ቤተሰቦች ሲመጡ ‹‹ጋብቻውን ወደናል›› ብለው ማረጋገጣቸው ነውና የልጅ ወገኖች በሙሉ ወጥተው ‹‹እልል›› እያሉ ይቀበሏቸዋል። ከዚያም ይበላል ፤ ይጠጣል ፤ ይዘፈናል። የልጅቷ ቤተሰቦችም ከልብ ይቅር ለማለታቸውና ዝምድናውን ለማጠናከራቸው አመላካች እንዲሆን በልጁ ቤተሰቦች ዘንድ ለሶስት ቀናት ያህል ይቆያሉ። ወደ ቤታቸው በሚሄዱበት ቀንም ፤ ልጆቹን መርቀው ፤ በደስታና በሀዘን ላለመለያየታቸው ቃል ኪዳን ይሆን ዘንድ ነጭ ድምድም[17] አውራ ዶሮ በር ላይ አርደው ረግጠው በማለፍ ይሄዳሉ።

ጠለፋው በልጅቷ እና በልጁ ስምምነት የሚፈጸም ከሆነ ደግሞ ፤ በቅድሚያ ከልጁም ሆነ ከልጅቷ የመፈላለግ ሁኔታ የሚያሳዩ ፍንጮች ይኖራሉ። ይህም በቤተሰቦቻቸውና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንዲታወቅ ወይም ጥርጣሬው ጎልቶ

[17] ራሱ ላይ ያለው ቀይ ስጋ ድምድም ያለ ወይም ያልረዘመ

እንዲወጣ የሚያደርግ ምልክት ነው። ልጁና ልጅቷ አብረው በብዙ ቦታዎች ይታያሉ (በግሮሽ ፣ በወንዝ ዳር ፣ በተራራ አካባቢ....) በተለይ የልጁ ጓደኞችና የቅርብ ዘመዶች ሁለቱ ልጆች መፋቀራቸውን ሊያውቁ የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ ይሆናል። ይህም በልጁና በልጅቷ ቤተሰቦች ጆሮ ይደርሳል ምክንያቱም የልጁና የልጅቷ መቀራረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሰማ ስለሚሆን ነው። ስለሆነም ጠለፋው እንደተከናወነ በቀጣዮቹ ቀናት ወደ ልጅቷ ቤተሰቦች ሽማግሌ እንዲላክ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ የተጣላን ማስታረቅ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ማሸማገል ሞራላዊ ግዴታ ቢሆንም ማህበረሰባዊ ክበሬታን ስለሚያስኝ ሽማግሌዎች ለሚጠየቁት የማሸማገል ስራ እምቢ አይሉም። በመሆኑም ጉዳዩን ከአካባቢ ሽንኑ ጋር ለመፍታት እንቅስቃሴ ይጀምራሉ።

የልጅቷ አባት ጉዳዩ እንዲጣራላቸው ለአካባቢ ሽንኑ ጥቆማ ያደርጋሉ። ይህን የሚያደርጉት በቅማንት ማህበረሰብ ባህል አንዲት ልጃገረድ ክብረ ንጽህና ከሌላት እንደ ጋለሞታ ስለምትቆጠር ፣ ክብሯ ስለሚቀነስ ከተጠለፈች በኋላ ወደ ቤተሰብ መምጣቷ በማህበረሰባዊ ግንኙነቷ እና በቤተሰቦቿ ላይ ችግር ይፈጥራል። ጠላፊውም ይህን የማህበረሰብ ሁኔታ ስለሚያውቅ ከጠለፋ በኋላ የመጀመሪያ እርምጃው ክብረ ንጽህናዋን መግሰስ ነው። ይህን ጠንቅቆ የሚያውቀው አባት የልጁ ሞራል እንዳይነካ ፣ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ መዘባበቻ እንዳትሆን ፣ ልጅቷ ገለሞታ እየተባለች የትዳር ጓደኛ እንደማታገኝ ስለሚያውቅ አባት ጉዳዩ እንዲጣራለት ያደርጋል። ጉዳዩን ካጣራ በኋላ ሽማግሌ ከቤቱ ሲመጣ ለመግደርደር ካልሆነ በስተቀር እምቢታን አያበዛም። ይሁን ይባላል።

የልጁ ቤተሰቦች በማህበረሰቡ ተረት ‹‹ከሞትና ከጋብቻ የሚቀር የለም›› የልጅ ነገር ሆኖ ራሳቸው ፈጽመውታል›› ይላሉ። የልጅቷ ቤተሰቦች ግን ልጃቸው ራሷ ፈቅዳ ፣ ወዳ የሄደች መሆኑን ሲያውቁ ከጠላፊው ይልቅ በእርሷ ይበሳጫሉ። የርሷ ወዳ መሄድ ክብራቸውን ዝቅ እንዳደረገው ይገምታሉ። ወግ ማዕረጉም ከሌላው የጋብቻ ዓይነት ያነሰ በመሆኑ ያዝኑባታል።የልጁም ቤተሰቦች ለደንቡ ያህል የካሳና የጥሎሽ

፣ ለልጅቷ ቤተሰቦች ክብርም ሲባል መለስተኛ ድግስ ይደግሳል። ከዚያም እርቅ ይፈጸማል።[18]

4.8 በግጭት አፈታት ወቅት ሂደቱን የሚያግዙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች

እርግማን፡- የቅማንት ማህበረሰብ ግጭትን በሚፈቱበት ጊዜ እርግማን ፣ ምርቃትና ምሳሌያዊ ንግግሮች ጉልህ ስፍራ የሚሰጣቸው ፎክሎራዊ መሳሪያዎቻቸው ናቸው። በእነዚህ እየታገዙ እርቁን ለመቀበል አሻፈረኝ ያለውን ወደ እርቅ መድረክ ያመጣሉ። በመሰረታዊ ሃሳቡ ላይ ተስማምቶ አፈጻጸሙ ላይ ልዩነት የሚያሳየውን ወገን ይረቱባቸዋል።

እርግማን በቅማንት ማህበረሰብ ‹‹ሚቶሎጅ›› ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው በመሆኑ አረጋዊያኑ በዚህ መሳሪያነት በመጠቀም ፣ ከሥርዓት ያፈነገጠውን ወደ መደበኛ ቦታው እንዲመለስ ያደርጉበታል። ግጭት ውስጥ የገቡ ሰዎች በሚያንገራግሩበት ጊዜ ማስፈራሪያቸው እርግማን ነው። በሽማግሌ የተረገመ ዘሩ ይጠፋል ፣ ዘላለም ምቾት የሌለው ህይወት ይመራል ተብሎ ይታመናል። ስለሆነም እርግማን ደንብ ማስከበሪያ ፣ ስርዓት ማስጠበቂያ ባህላዊ መሳሪያ ነው። ስለ እርግማን በቅማንት ማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ወቅት የሚኖረውን ሁኔታ በተመለከተ የመረጃ አቀባዮቼ እንዲህ በማለት ይገልጹታል።

አንድን ሌባ ወይም በዳይ ጥፋቱን እንዲያምን በፈጣሪ ስም እንለምነዋለን። እናግባባዋለን። ነገር ግን ይህንን አሻፈረኝ አልቀበልም ቢል ይረገማል። ምን ተብሎ ያልሸኝ እንደሆነ ምዝገና መዓት ያውርድብህ ፣ በሄድክበት እርጉም ሁን ፣ አይቅናህ ፣ እንደተንከራተትክ ኑር ፣ መከራ አይለይህ ፣ ኑሮህን ያሳር ያድርገው ፣ የኛ የደካሞች ሀዘን ጦር ሆኖ ይውጋሕ ፣ ዘር ይንሳህ ፣ ሰው ይጥላህ ፣ ብትሞት ቀባሪ ብትታመም ጠያቂ ይንሳህ ይባላል። ነግር ግን ይህን ስለሚፈራ ሳይረገም ቀድሞ ያምናል። (የካቲት 23/2005 ዓ.ም አይከል) የቡድን ውይይት።

[18] ይህ መረጃ የተገኘው በቡድን ውይይት ነው።

ከላይ የተገለጸው እርግማን ማንኛውንም የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ያስደነግጣል። መዓት እንዲወርድበት ፣ በሄደበት እርጉም እንዲሆን ፣ እንደተንከራተተ ኑሮ እንዲያልፍ የሚመኝ ማንም የለም። ይህ ሁሉ ሳያንስ ደግሞ ዘር እንዲያጣ ፣ ሰው እንዲጠላው ፣ መከራ እንዳይለየው ሲረገም መንፈሱ ያረበሻል። አስቀድሞም ያምንበታልና የሚገጥመውን ችግር ሁሉ እርግማን ጋር ስለሚያያይው በኑሮው ስኬት አይገጥመውም።

የተረገመው እርግማን በሰው ላይ እንደሚደርስ በደንብ ይታመንበታል። እጅግ ከፍተኛ ጥቅም የሚያገኙበትን ጉዳይ እንኳን እርግማንን በመፍራት እንደሚተውና ለባህላዊ ደንቡ ትልቅ ከበሬታ በመስጠት ታማኝነታቸውን እንደሚያሳዩ መቶ አለቃ ጥጋቡ ይናገራሉ። ‹‹ እርግማንን በመፍራት በጣም ብዙ ጥቅም ሊያገኙበት የሚችሉትን ጉዳይ ይተዋሉ። ይህ ደግሞ የሚያሳየን ለደንቡ ያላቸውን ክብርና ታማኝነት ነው።›› (መቶ አለቃ ጥጋቡ የካቲት 27/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ። እርግማን መድረሱ ብቻ ሳይሆን ፈጣን መሆኑ ደግሞ ጉዳዩን የበለጠ አስፈሪ ያደርገዋል። ማንኛውም የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ዕድሜና ጾታ ሳይለይ ይህንን እንዲያምን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ይነገረዋል።

በእርቅ ሥርዓቱ ላይ እንደ ግጭቱ ዓይነትና ደረጃ የተለያዩ እርግማኖች ሊኖሩ ይችላሉ። አስቀድሞ እንደተገለጸው የባልና ሚስት ግጭት እርቅ ሲፈጸም እርግማንም ምርቃትም ሰምተናል። ለምሳሌ ወንበሩ በምርቃት መሃል ‹‹ በመካከላችሁ የገባውን ምዝገና አመድ ያድርገው ፣ ጠላታች ይጥፋ›› ብለዋል። ይህ የሚያሳየን እርግማኑ አንድም ክፉ የሚያስብባቸው ካለ ከወዲሁ መግቻ ፣ አንድም እንዳያስቡባቸው ማስጠንቀቂያ ነው። [19]

[19] ወንበሩ ለምን እንደዚህ ብለው እንደ ረገሙ ከሥርዓቱ በኋላ ለማጣራት ስሞክር ግጭቱ የባል ወገኖች አሉባልታ እንዳለበት ለማወቅ ችያለሁ።

ምርቃት ፡- በአንጻሩ ምርቃት ደግሞ እርግማን የሚፈራውንና የሚጠላውን ያህል የሚፈለግ ጉዳይ ነው። በቅማንት ማህበረሰብ ዘንድ ምርቃት በብዛት የተለመደ ነው። በጎ ተጠጥቶ ፣ ምግብ ተበልቶ ፣ ለእንግድነት ተሂዶ ምርቃት የማይቀር ነው። ምርቃቱ የሚጀምረው በዕድሜ አንጋፋ የሆነና ምርቃት የሚያውቅ አዛውንት ካለ በእርሱ ይሆናል። እርሱ ሲመርቅ ሌላው ሰው ‹‹አሜን›› በማለት ይከተላል።

የሀገር ሽማግሌዎች በእርቅ ሥርዓት ወቅት ለእርቅ እሺ የሚልን ሰው በጣም ይመርቃሉ። ‹‹ምዝገና ይባርክህ ፣ እኛን እሺ እንዳልከን አንተንም እሺ ይበልህ ፣ እርቅ ፈጥረሃል ሰላም አውርደሃል እና የሰላም ኑሮ ይስጥህ ፣ ልጆችህን ይባርክልህ ፣ ሃብት ንብረትህን ያብዛልህ ፣ የሰው መውደዱን የቀና መንገዱን ይስጥህ ፣ ተባረክ ብሩክ ሁን›› (አቶ ፍርዱ ነቃ የካቲት 21/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ።

በባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ወቅት በማንኛውም ግጭት እርቅ ከተካሄደ በኋላ ምርቃት ይኖራል።[20] በምርቃት ውስጥ ምክር ፣ ታሪክ ፣ ተረትና ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል። ለምሳሌ በባልና ሚስት የግጭት አፈታት ሥርዓት ወቅት ከቀረበው ምርቃት ውስጥ ‹‹ሰው የወደደው ምዝገና የወደደው›› የሚል ተረትና ምሳሌ ቀርቧል። ይህ ተረትና ምሳሌ የመጣው አንድም እናንተን ለማስታረቅ የመጡት ፣ የለፉት አስታራቂ ሽማግሌዎች ይወዷችኋል። በመሆኑም ምዝገናም ወዷችኋል። በማለት ለማሳመን ፤ አንድም ይህ እነርሱን አክብረው ፣ ማህበረሰቡን ወክለው የመጡ ሽማግሌዎችን ማክበርና ለእነርሱ ተገዢ መሆን እንደሚያስፈልግ ለመጥቀስ እንደሆነ እንገነዘባለን።

በምርቃት ታሪክን የሚያስተምሩበት አጋጣሚ ደግሞ የቅድመ አያቶቻቸው ፣ የአያቶቻቸውና የአባቶቻቸው ማህበራዊ ኑሮ ምን መልክ እንደነበረው ያስታውሳል። ተደጋጋፊነታቸው እስከምን ድረስ እንደሚዘልቅም ይጠቁማል። በባልና ሚስት የግጭት አፈታት ሥርዓት ወቅት ወንበሩ አንድ አጎዛ ለሦስትና

[20] በማንኛውም የግጭት አፈታት ሥርዓት መራቂው ወንበሩ ናቸው።

አራት ሰው መኝታነት ሲያገለግል እንደነበር ገልጸዋል። ይህ ጉዳይ የፍቅራቸውን ሃያልነት ለማሳት የተጠቀሰ ፣ የአባቶቻቸውን ጥንካሬ ለማጉላት የቀረበ ነው። በአባቶቻቸው ዘመን የነበረ ምግባር ዛሬ ተሸርሽሮ ከቶም ከመጣላት ደረጃ መደረሱ የነሱ ጥፋት ሳይሆን የጊዜው መክፋት መሆኑ ሁለቱንም ጥፋተኛ ላለማድረግና እርስ በርሳቸው እንዲደጋገፉ ፣ ልዩነትም እንዳይፈጥሩ ታሪክን አስታኮ የቀረበ ምክርም ነው። ምርቃቱና ከምርቃቱ ጋር የሚቀርበው ምክርና ታሪክ እንዲሁም ተረትና ምሳሌ በዘፈቀደ የሚጠቀስ ሳይሆን ከጉዳዩ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያለው እየተመረጠ ነው። በባልና ሚስት የግጭት አፈታት ሥርዓት ወቅት እንደ ግጭቱ ቅለትና ክብደት የአባቶቻቸው ትዳር መልካም ገጽታ እየተጠቀሰ ምክር ከምርቃት ጋር ሊቀርብ ይችላል። ምርቃቱም ፣ ተግሳጹም ፣ ምክሩም ፣ ተረትና ምሳሌዎችም በማንኛውም የግጭት አፈታት ሥርዓት ወቅት ሲመጡ ተጋጭዎችን ላለማስቀየም ብርቱ ጥንቃቄ ከማድረግ ጋር ተያይዘው ሊሆን ይችላል።[21]

ተረትና ምሳሌ ፦ በቅማንት ማህበረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ሲካሄድ ትልቅ ሚና ያለው የፎክሎር አካል ተረትና ምሳሌ ነው። ተረትና ምሳሌ በግጭት አፈታት ሂደቱ ወቅት በፍርድ ቤት ውስጥ ለጉዳዩ ተስማሚ አንቀጽ እየጠቀሱ እንደመሟገት የሚቆጠር ላቅ ያለ የንግግር ጥበብ ነው። በባህላዊ የፍትህ ተቋማት ውስጥ በአስታራቂነት የሚመረጡት ሽማግሌዎች ጉዳዩን የሚጀምሩት በተረትና ምሳሌ ነው። ተረትና ምሳሌ የጉዳዩ ማጠንጠኛ እንዝርት ወይም ምሰሶው ነው ማለት ይቻላል። የሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች ሁሉ በምሳሌ የታሸሙ ናቸው። በዳይና ተበዳይ የሚሰጧቸው መልሶች እንደዚሁ በብዛት ተረትና ምሳሌዎች የተቀላቀሉባቸው ናቸው። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ አቶ ፍርዱ ነቃ አንድ ጊዜ በሽምግልና ወቅት ያጋጠማቸውን ገጠመኝ እንስተው እንዲህ በማለት አጫውተውኛል።

አንደዜ አንድ ሊባ ሰርቆ ይያዝና ወደኛ ይመጣል። እኛም ቀድመን ጉዳዩን ሰናጣራ ዛዲያ ውነትም ሰርቋል። ግና ድርቅ ብሎ አይኔን ግንባር ያርገው አለ። ተያ በጓላ ነገሩ አልጥመነ ሲል በነገር ወጋ ወጋ አረግነው። ሰማህ

[21] በቡድን ውይይት ወቅት ያገኘሁት መረጃ ነው። ነገር ግን ቀጥተኛ የእነርሱ ሃሳብ አይደለም።

ወንድማችን 'ዳኛ የበላው እሳት የበላው ነው።' አንተም ‹‹አይተንብሃል›› ስትባል እሺ በል። የተናገርኸውንም ሰምተናል። እሱም የተናገረውን ሰምተናል። ነገሩ ወዴት እንደሆነም አውቀናል። 'ሐሰት ብለህ ነፍስህን አውጣ' እንዲለ ሁኖ 'ይ ፤ አንተም ብትሆን ውነቱን ሳታውቀው ቀርተህ አይደለም። ልቦናህ እያወቀ ብታደክመን ምን ትጠቀማለህ። 'የሞተ ማንሳት መሳሳት' ነውና አሁን እሺ በለኝ። ተንግዲ ያለፈውን አንመለስበትም። ይኸው ስንት ቀን ተነጋገርንበት ፤ 'በድሎም ታገር ተበድሎም ታገር' ነውና ወንድማችን እሺ በል አልነው። ተዚያና ደነገጠ ፤ ሚገባበት ጠፋው ፤ አቅሉ ተዘቅዝቆ አምኖ ኸደ። (አቶ ፍርዱ ነቃ የካቲት 27/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ።

መረጃ አቀባዬ በተናገሩት ንግግር ውስጥ አራት ተረትና ምሳሌዎች ተጠቅሰዋል። ‹‹ዳኛ የበላው እሳት የበላው›› ሲሉ እሳት ማንኛውንም ነገር ካወደመ ዳግም ሊመለስ እንደማይችል ሁሉ ሽማግሌ የወሰነውም እንደማይሻር ሲገልጹ ነው። እውነታው በግልጽ የሚታይ ስለሆነ ሽማግሌዎች የበየኑትን ከመቀበል ውጭ በውሸት መከራከር ተገቢ እንዳልነ ለመጥቀስ ‹‹ሐሰት ብለህ ነፍስን አውጣ›› ብለው ተርተዋል። በዚህም ንግግር እየካደ እራሱን ነጻ ለማውጣት መጣሩን ጠቁመውታል። ድርጊቱ ግልጽ ስለሆነ እኛም አውቀንብሃል በኸንቱ አታድክመን ሲሉ በለዘበ አነጋገር እየገሰጹት እንደሆነም ያሳያል።

‹‹የሞተ ማንሳት መሳሳት›› ያሉትም ከላይ ዳኛ የበላው እሳት የበላው ከሚለው ጋር የሚመሳሰል ብሂል ነው። ‹‹በድሎም ታገር ተበድሎም ታገር›› የሚለውን የተጠቀመበት ደግሞ ፤ በደለኛም ሆነ ተበዳይ መኖር የሚችሉት ከህዝቡ ጋር ሲስማሙ ብቻ እንጂ ሕዝቡን ካስቀየመ ማናቸውም ቢሆኑ መኖር እንደማይችሉ ለማመላከት ነው። ስለሆም ሽማግሌዎች የበየኑትን ካልተቀበለ ማህበረሰቡን እንደማ ያስቀይምና ይህ ደግሞ የከፋ መዘዝ እንደሚያመጣበት ለማስጠንቀቅ ፤ እንኳን በደለኛው የተበደለም ቢሆን ከእነርሱ ቃል (ብይን) ከወጣ ተቀባይነት እንደማይኖረው ለመስረዳት ፤ ማህበረሰቡ የሚጥልበት ማህበራዊ ቅጣት ጠንካራ እንደሆነ ለማስታወስ የመጣ ነው።

ተረትና ምሳሌዎች በሽማግሌዎች ብቻ የሚባሉ ሳይሆኑ ተበዳይ ጉዳዩን ግዝፈት ለመስጠት በዳይም ለመከራከር ይጠቅሷቸዋል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አቶ ፍርዱ ነቃ ከዚህ በፊት በተሳተፉበት የእርቅ ሥርዓት ተከሳሽ ተረትና ምሳሌዎችን እያመጣ እንደተከራከረ በማስታወስ እንዲህ አጫውተውኛል፡፡

መቼም በክመንት ግጭት ሲፈታ ሁል ግዜም ተከሳሽ ቢሆን ፣ ክሳሽ ቢሆን እኛም ስናስታርቅ ተረትና ምሳሌ አይቀሬ ነው፡፡ እናልሽ አንደዜ አንድ ሰው ይሞትና ሬሳው ከዚህ በፊት ጠበኛው የነበረ ሰው በር ላይ ወድቆ ስለተገኘ ጉዳዩ ወደኛ ይመጣል፡፡ ሰውየው ደሞ ከተጣሉ በኋላ አገር ለቆ ሌላ ቦታ ነበር የሚኖር ፣ ተዛም መዘዙ አለቀቀውም ተሱ በር ላይ ተገኘ እሬሳው ፣ እኛም ተከሳሽን አስጠርተን ስንመረምረው አባቶቹ እኔስ ብሆን ይህን ያህል በለሊት ጥለውብኝ እንጂ ባልሰማሁ ፣ ባላየሁ እንዴት እ... እንዲ ታረጉኛላቹ፡፡ መቼም 'ቀን የማይጥለው ጠጅ የማያሰክረው የለም' ቀን ተጣለኝ ምን አደርጋለሁ፡፡ 'የተረሳ የተፋሰሰ' ነገርስ ይመጣብኛልም አላልሁ ነበረ፡፡ አሁንም 'ዝናብ ጣለ እየ ደጃፍህ' እንዲሉ አይታችሁ ፍረዱ፡፡ እንግዲ 'አፈር ላይ የወደቀ ሥጋ አፈር ሳያነሳ አይነሳም'ና ምን ላርግ አለኑ፡፡
(አቶ ፍርዱ ነቃ የካቲት 27/2005 ዓ.ም አይከል) ቃለ መጠይቅ፡፡

እኚህ ተከሳሽ ‹‹ቀን የማይጥለው ጠጅ የማያሰክረው የለም›› ሲሉ ከልክ በላይ ጠጅ የጠጣ ሰው እንደሚሰክር ሁሉ ፣ ቀን የማይጥለው ፣ አጋጣሚ ከችግር ውስጥ የማይከተው የለም፡፡ እኔም አጋጣሚ ከእንዲህ መሳይ ችግር ቢያስገባኝ ነው እንጂ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት እየካዱ ነው፡፡ ‹‹የተረሳ የተፋሰሰ›› የሚሉት ከብዙ ጊዜ በፊት ከሚች ጋር ጸበኛ በመሆናቸው አካባቢውን ለቀው ወደ ሌላ ቦታ ሂደው ጸባቸውን ረስተውት ፣ እንደፈሰሰ ውሃ ትተውት ሲኖሩ ፣ ከብዙ ጊዜ በኋላ መዘዙ እንዳለቀቃቸው ለመግለጽ ነው፡፡ ‹‹ዝናብ ጣለ እየደጃፍህ›› ማለታቸው ዝናብ በጣለ ጊዜ ቆሻሻ ከሩቅ መጥቶ አካባቢውን [illegible] ያላሰቡት ችግር እንደደረሰባቸው ለማሳሰብ ነው፡፡ ሲጨርሱም ‹‹ቀን ጣለኝ›› ያሉትን በማስታወስ አፈር ላይ የወደቀ ሥጋ አፈር ሳያነሳ እንደማይነሳ ሁሉ

እኔም የዚሁ ተምሳሌት ነኝ በማለት ምሬታቸውን ገልጸዋል። በአጠቃላይ ከወንጀሉ ነጻ መሆናቸውን እየገለጹ ፤ የንግግራቸው መንፈስ ግን ውሳኔያችን እቀበላለሁ ፤ ነገር ግን ቀን የጣለኝ ነኝና ፍርዱን አቅሉልኝ የሚል ይመስላል።

ከሳሽም በበኩሉ ሃሳቡን በሚገልጽበት ጊዜ ተረትና ምሳሌዎችን ይጠቀማል። እርሱም ሊገልጽ የፈለገውን ጉዳይ አትብቶ ለመንገር ፣ ሽማግሌዎችን ለማሳመን ሲል ለአውዱ ተስማሚ የሆኑ ምሳሌዎችን ይጠቅሳል። መረጃ አቀባዬቼ እንደነገሩኝ እኔ ወደ አካባቢው ለመስክ ከመውጣቴ ሁለት ወር በፊት አንድ ሰው ወንድሙ በሰው እጅ ተገድሎበት በወንበሩ ዳኝነት እንደተሰጠው ገልጸው ታሪኩን እንዲህ በማለት ነገሩኝ፡-

ሰውየው ከሰሜን ሸዋ መጥቶ በኛ አካባቢ የሚኖርና ብቸኛ አንድ ወንደሙ የተገደለበት ሰው ስለነበር ምሬቱን እንዲህ በማለት ነበር የገለጸው ስሙኝ አባቶቼ እኔ 'አገሬ ሌላ ወንዜ ገሊላ' ሁኖ ፤ ወገን የሌለኝ ተቆርቋሪ ያጣሁ ብቸኛ ሁኜ ቢያገኙኝ ያለኝን አንድ ወንድም ገደለብኝ 'ሽማግሌ ተለለ ጭብጥ ጎመን የለም' እንዲለ እናንተ ዘንዳ ተደረሰኩ ይሽን ሰው እፋረደዋለሁ። 'አይበሰብስ ሥጋ አይሞት ነፍስ የለም'ና[22] *ቴይህ ሰው በቀር ወንድሜን የገደለው የለም በማለት ተከሳሹን ተሟግቷል።* (የካቲት 21/2005ዓ.ም አይከል) የቡድን ውይይት።

ከሳሽ የሰው አገር ሰው መሆናቸውን ለመግለጽ ፣ ባይተዋርነታቸውን ለማሳየት ‹‹አገሬ ሌላ ወንዜ ገሊላ›› ሲሉ ተረቱ ፤ የሩቅ አካባቢ ነዋሪ ዘመዶቻቸው በቅርብ የሌለ መሆናቸውን መግለጻቸው ነው። ሽማግሌ ከሌለ አገሩን የሚያስተዳድር ስለማይኖር ሰላም ይጠፋል። እንኳንስ ሰርቶ መኖር ቀርቶ ጥቂት ጎመን ማግኘት አይቻልም። ስለዚህ የሽማግሌን አስፈላጊነት አጠንክረው በተረትና ምሳሌያቸው ሲገልጹ አንድም ሽማግሌዎቹ እንዲራሩላቸው ፤ አንድም ያዘናቸውን ጥልቀት እንዲረዱ ያደርጋል። እንዲሁም እርሳቸው ዘላለም ነዋሪ ሳይሆኑ መዋቲ መሆናቸውን ፣ ሥጋቸው እንደሌላው ሰው በስባሽ

[22] በዚህ ርዕስ ስር ባሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች ውስጥ አጽንኦት የሰጠሁት እኔ ነኝ።

መሆኑን አውቀው በእውነተኛ መንገድ የከሰሱ እንጂ ሐሰተኛ አለመሆናቸውንም በምሳሌ ያስረዳሉ።።

ሽማግለዎች በባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ ውስጥ ከሳሽን (በተለይም ገዳይ ከሆነ) በጥያቄ ያጣድፉታል።። በዚህ ጊዜ ተከሳሽ ጉዳዩን ግራና ቀኝ እያወሳሰበ ካስቸገረ ‹‹ውሃን ከጥሩ ነገርን ከስሩ›› በማለት ይተርቱና ወደ ነገሩ ስረ መሰረት ይመለሳሉ።። አንድ ነገር ከመነሻው ካልተያዘ በመካከል የተለያዩ ጉዳዮች ሲገቡ አቢዩ ነገር እየተዘነጋ ፣ ጭብጡ እየተረሳ የትኩረት አቅጣጫውን እየቀየረ ሌላ መልክ ሊይዝ ይችላል።። የሽማግሌዎች ነገሩን ከጅምሩ ለማወቅ መጣርና ሂደቱን መከታተል ደግሞ ይህ ጉዳይ ቀድሞ እንደገባቸው ያስገነዝበናል።።

በተለያዩ መንገዶች ጉዳዩን ሲያጣሩ ያልተጠበቀ ውጤት ሊያገኙ ይችላሉ።። በዚህም ጊዜ ‹‹አይሆንም ሲሉት ይሆናል ፤ ይሆናል ሲሉት አይሆንም›› በማለት ይተርታሉ።። ይህ የሚያሳየው አንድም አይሆንም ብለው ያሰቡት ጉዳይ እነርሱ በገመቱት መንገድ ሳይሆን በሌላ አቅጣጫ ተከስቶ ሲያገኙት ፤ ይሆናል ብለው የጠበቁት ነገር በተቃራኒው ተለውጦ ሲመለከቱት የተሰማቸውን ስሜት ለመግለጽ ያመጡት ነው።። አንድም ካለፈው የህይወት ገጠመኛቸው ተነስተው የወደፊት ጥርጣሬያቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው።። አንድም ነገሩን በተለያየ አቅጣጫ መመልከት እንዳለባቸው ራሳቸውን ለማሳሰብ የጠቀሱት ነው።።

በገዳይና በሟች ቤተሰቦች መካከል በካሳ ክፍያ እርቅ ይወርዳል።። በዚህ ጊዜ የሟች ቤተሰቦች ካሳው አንሶናል ብለው ካጉረመረሙ ‹‹ካሳ በልቶ የከበረ አንት ጠጥቶ የሰከረ የለም›› በማለት የተሰጣቸውን ነገር በሰላም ተቀብለው እርቅ እንዲፈጥሩ ያደርጓቸዋል።። ካሳ መክበሪያ ሳይሆን የስሜት መጠገኛ ፣ የእርቅ ማጽኛ ፣ ይቅር መባባያ እንደሆነ ይጠቁማሉ።። የካሳው ገንዘብ መብዛት በእርቁ ሂደትና አፈጻጸም ላይ የጎላ ተጽዕኖ ስላለው አስታራቂዎቹ በዚህ ረገድ ጥንቃቄ ያደርጋሉ።። በተቻላቸው መጠንም በካሳ የሚገኝን ገንዘብ ያናንቃሉ።። ጠያቂውም የበዛ ካሳ ሲያቀርብ ሃሳቡን ያጣጥሉበታል።። ይህን ሁሉ

የሚያደርጉት ከተቻለ ገንዘቡን ለማስቀረት ካልተቻለም መጠኑን ለመቀነስ ነው።

ሁሌም ቢሆን የከሳሽም ሆነ የተከሳሽ እንዲሁም የአስታራቂ የፍትህ ተቋማቱ ሽማግሌዎች አነጋገር እነዚህን በመሳሰሉ ለአውዱ ተስማሚ በሆኑ ተረትና ምሳሌዎች የተሞሉ ናቸው። ተረትና ምሳሌዎቹን ለምክርም ፣ ለተግሳጽም ፣ ለተማጥኖም ፣ ለማስጠንቀቅም ይጠቀሙባቸዋል። በባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ ውስጥ በእርቅ ሂደት ወቅት ተረትና ምሳሌዎች ከእርቅ በኋላ ደግሞ ምርቃት ትልቅ ቦታ አላቸው። እነዚህ ጉዳዮች ደንብና ሥርዓትን ማስተማሪያ ፣ ማስከበሪያ ፣ ማስተላለፊያ ሆነው ያገለግላሉ።

4.9 ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ፋይዳዎች

በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥ ግጭት የሚፈታባቸው ባህላዊ ተቋማት በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው። ዘዴዎቹ ጥንት የነበሩ ፣ ከሞላ ጎደል ከነሥርዓታቸው አሁንም ያሉ ፣ ወደፊትም ሊቀጥሉ የሚችሉ ናቸው የጥንታዊነታቸውን ያህል ወደኋን ያልተገኘ ፣ እንዲያውም ከመደበኛው ፍርድ ቤት በተሻለ (ጎንለጎን) ህብረተሰቡ እየተገለገለባቸው ያሉ እና የሚመርጣቸው ናቸው። በመሆኑም ሰፊ ማህበራዊ ፋይዳዎች እንዳሏቸው መገንዘብ እንችላለን። ስለሆነም ከሚኖራቸው ማህበረሰባዊ ጠቀሜታ አንፃር የተወሰኑትን በዝርዝር ማሳየቱ ለግንዛቤ ይጠቅማል። ከሚኖራቸው ጠቀሜታ የመጀመሪያው ፍትህን ማስገኘት ነው። ፍትህ ሲባል አንድ ህብረተሰብ በሚመራበት ህግ ላይ ተመስርቶ ሁሉም በእኩልነት የሚዳኝበት ሚዛናዊ የውሳኔ አሰጣጥ ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ህግን ምርኩዝ አድርጎ በማጉላላት ጊዜ ፣ ጉልበትና ገንዘብ ሳይባክን ዜጎች ለችግርና ለመከራ ሳይዳረጉ በሐቀኝነት ፍርድ የሚሰጥበት የዳኝነት ስርዓት እንደሆነ እንረዳለን።

ከዚህ የፍትህ ጽንሰ ሃሳብ አንጻር እነዚህ የፍትህ አካላት በአፈጻጸማቸው ፍትሃዊነትን ለማህበረሰቡ ያጎናጽፋሉ። ዳገት ወጥተው ቁልቁለት ወርደው ጎጂና ተጎጂ ወገኖችን አንድ ላይ ለማምጣት ደፋ ቀና የሚሉት የአካባቢ ሽንጎዎችና ወንበሩ ከአድልዎ ነፃ መሆናቸው በማህበረሰቡ ውስጥ በእርግጠኝነት ይነገራል። ምኞታቸውና

ፍላጎታቸው የተፈጠሩትን ግጭትና ግጭት ያስከተለውን ጉዳት መርምረው ለሁለቱም ወገኖች የሚበጅ ውሳኔ መስጠት ነው። ይህንን ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ በጎጂና ተጎጂ ወገኖች መካከል ቅራኔ ተባብሶ ወደ ሌላ የጥፋት ድርጊት ሳያመራ ወዲያው የእርቁ አፈጻጸም ሂደት ይጀመራል። የተፈጠረው ግጭት እንዲረግብ ይደረጋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ «እምነት» ጉልህ ስፍራን ይይዛል በማህበረሰቡ አስተሳሰብ መሰረት «እውነት» ከማንኛውም ነገር በላይ ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል። በአንፃሩ ሀሰት በብዙ መልኩ ለግጭት መንስኤ ከመሆኑም በላይ ግጭትን ሲያባብስ ይታያል። ግለሰብን ከግለሰብ ፣ ቤተሰብን ከቤተሰብ ፣ ጎረቤትን ከጎረቤት... ጋር ያበጣብጣል። በእነዚህ የፍትህ አካላት ግን ትውልድ የእውነትን ጠቀሜታ ይማርበታል። ለምሳሌ አንድ የሰው ነፍስ ያጠፋ ወይም በአካል ላይ ጉዳት ያደረሰ የማህበረሰቡ ተወላጅ «እጄ በእገሌ ደም አድፏልና ካሳ እንድከፍል አድርጉኝ» ለአካባቢ ሽንኃ አባላት ተማፅኖ ይልካል። የገደለውን ሰው (ያቆሰለውን አካል) ያለማንም አስገዳጅነት ይናገራል። ለጠፋውም ድርጊት ህሊናዊ ቁስል እንደደረሰበት ይገልፃል። ስለዚህ ሁለቱም የፍትህ አካላት ለተጎጂው ወገን የሞራልና የቁሳቁስ ካሳ ይከፈላል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ማህበረሰቡ የደነገገው ደንብ ተፈፃሚነቱም በተግባር ይረጋገጣል።

ሁለተኛው ዘላቂ የሆነ ሠላም መፍጠራቸው ነው። ሠላም ለግላዊም ሆነ ለማህበረሰባዊ ህይወት መሰረት መሆኑ አይካድም። ሰላም በሌለበት የተረጋጋ ህይወት እንደማይኖር ጉልህ ነው። ሰዎች በሚናቆሩበት አውድ ውስጥ ስለ ልማትና ስለ ግላዊም ሆነ ማህበረሰባዊ ኑሮ የተረጋጋ ህሊናን ይዞ ማሰብ ፣ አስቦ መስራት ፣ ሰርቶ መሻሻል (የተሻለ ውጤት ማምጣት) እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን እንረዳለን። ስለሆነም ሽወን በሚተገብርበት ህዝብ ውስጥ ዘላቂ ሰላምን ለማስገኘት ከፍተኛ ድርሻ አለው። በሽወን አማካይነት እርቅ የሚደረገው በጎጂና በተጎጂ ወገኖች መካከል ብቻ አይደለም። በማህበረሰቡ ህግና ደንብ መሰረት ከልጅነት እስከ አዋቂነት ባሉት ወገኖች መካከል የሚፈጠር የሰላም ማውረጃ ዘዴ በመሆኑ በእርቅ ላበቃለት ጉዳይ ተመልሶ ብቀላ አይኖርም። ይህም ማለት በቤተሰብ ወይም

የቤተዘመድ አካል የተገደለበት ወገን ጊዜው ሲያመቸው በደም ለመበቀል ለአመጽና በብጥብጥ አይቀሰቀስም፡፡ ስለሆነም ሽወን እርቅ ከተፈጸመ በኋላ አንድ ጊዜ እልም ሌላ ጊዜ ብቅ የሚል የውስጥ ብጥብጥ (ቁርሾ) ያከትምለታል፡፡

በሽወን እርቅ ካልተፈጸመ ግን የገዳይና የሟች ቤተሰቦች (የጎጅና ተጎጂ) ‹‹እሳትና ጭድ›› ሆነው ይፈላለጋሉ፡፡ ለምሳሌ አንዱ የሌለውን ወንድም ቢገደል የተገዳይ ወንድም ‹‹የወንድሜን ደም እመልሳለሁ›› በማለት ለነፍስ ግድያ ያደፍጣል፡፡ ግድያው ለጊዜው የማይሳካለት ከሆነ በገዳይ ቤት ወይም በገዳይ ቤተሰብ ቤቶች ላይ እሳት ይለኩሳል፡፡ የእህል ማሳቸውን በእሳት ያጋያል፡፡ ይህ ደግሞ በራሱ እያደረ ሌላ በቀል እየወለደ ተመሳሳይ ጥፋቶችን እንደሚያስከትል የሀገር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡

ከዚህም ሌላ ነፍሰ ገዳይ የተባለው በመደበኛ ፍርድ ቤት የእስራት ቅጣት እንኳን ቢፈረድበት በገዳይና በሟች ቤተሰቦች መካከል በደመኝነት መፈላለጉ አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ የካሳ ክፍዮችና የካሳ ተቀባዮች ቤተሰቦች ጭምር ናቸው፡፡ ከሳም በመሰረተ ሃሳቡ ለወገን ዘመድ የሚከፈል ይሆናል፡፡ በመሆኑም ሽወን ከፍ ብሎ የተጠቀሱትንጥፋቶች ለማስወገድ ጉልህ ሚናን ይጫወታል፡፡ በሽወን አማካይነት እርቅ ከተፈጠረ በኋላ ለሁለቱ ወገኖች አብረው በሰላም መኖር ይጀምራሉ፡፡ አንዱ በምንም መልኩ በሌላው ላይ እጁን አይቀስርም ፤ በመካከለኛው አዲስ ፍቅር እያቆጠቆጠ ይመጣል ፤ አንዱ ለሌላው እንደሁኔታው ሚዜ፣ አበልጅ ይሆናል፡፡ በጋብቻም ሊተሳሰሩ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የቂም እርሾ ሳይኖር አዲስ የህይወት ጎዳናን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

ሥነ ልቦናዊ መረጋጋትን መፍጠር ደግሞ ከሁለቱ ለጥቆ የሚመጣ ነው፡፡ ቀደም ብሎ የነበረው የበቀል የፍርሃት ፣ የጥርጣሬና ያለመረጋጋት ስሜት ከእርቅ በኋላ ስለማይኖር በበዳይና በወገኖቹ በኩል ሥነልቦናዊ መረጋጋት ይፈጥራል፡፡ የተበዳይ ወገኖች በተለይም የሟች ወገኖች ከማህበረሰቡ ‹‹ደሙን የማይመልስ›› የሚል ሃሜትና ሽሙጥ ስለማይሰነዝርባቸው ህሊናዊ ነፃነት ያገኛሉ፡፡ ከዚህም በላይ አጥፊ ነህ ተብሎ በሽማግሌ የተነገረው ሰው ጥፋቱን አምኖ ለጥፋቱ ማስረሻ የሚሆን

ካሳ በመክፈሉ ማህበራዊ ደህንነትና ዋስትና ያገኝበታል። ተከታዩ ትውልድም ከጠቅላላው የእርቅ አፈፃፀሙ እውነትን ፣ ለጥፋቱ ይቅርታ መጠየቅንና መፀፀትን ፣ ጥፋት ለፈፀመበት ወገኑ ይማርበታል።

በሚችና በገዳይ ፣ በጎጂና በተጎጂ ቤተሰቦች አዕምሮ ውስጥ የሚርመሰመሱትን የጥላቻ መንፈሶች ስለሚያስወግድ የሥነ ልቦና መረጋጋት ይፈጥራል። ተጎጂው ወገን በምንም ዓይነት መንገድ ጉዳት አድራሹን ልበቀል ብሎ ህሊናውን እረፍት የሚያሳጣውን ፣ እንቅልፍ የሚነሳውን የውስጥ ጭንቀት ያስወግድለታል። በጎጂውም ወገን በኩል በደም ብቀላ አማካይነት የህይወትና ንብረት ጥፋት ይደርስብኛል በማለት ህሊናውን እንደወሰፌ የሚጠቀጥቀውን ያረጋጋለታል። ሲተኛ የሚያባንነውን ሲሄድ ብቻውን የሚያስለፈልፈውን የህሊና ህመም ያድንለታል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ እነዚህ የፍትህ አካላት የቅማንት ማህበረሰብ ርዕዮታዊ አተያይ መገለጫ ሆነው ያገለግላሉ። የማህበረሰቡ አስተሳሰብ ፣ እምነትና ፍልስፍና ይንጸባረቅበታል። እንዲህ በመሆኑ ከእምነቱና ከተፈጥሮ ጋር ሳንካ ሳይገጥማቸው በሽወን አማካይነት ከራሱ ፣ ከዙሪያ ገባው ወይም ከአካባቢው ከእንስሳቱ ከአራዊቱ ጋር የሚኖሩትን የሥነ ልቦና ግጭቶች ፈትተው ሰላማዊ የህይወት ድባብ ይፈጥራሉ።

ሽወን ከትውልድ ወደ ትውልድ ከዘመን ወደ ዘመን ሲተላለፍ የቆየ እንደመሆኑ ማህበረሰቡ በኑሮ ሂደት ውስጥ ያካበተውን ልማዳዊ እውቀት ለሌላው ያስተላልፍበታል። ስለሆነም ልማዳዊ እውቀትን ማስጨበጥ አንዱ ጠቀሜታው ይሆናል። በሁለት ወይም ከዚያም በላይ በሆኑት ወገኖች መካከል ግጭት ሲከሰት እርቅ ለማውረድ ባህላዊ አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች የጎጂና የተጎጂ ወገኖችን ውስጣዊ ስሜት ተገንዝበው ለማስታረቅ የሚጠቀሙበትን የአሰራር ጥበብ ለመቅሰም ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪም ማህበረሰቡ በእምነቱ ጥላ ስር የአኗኗር ስርዓት ተፈጥሮ በባህላዊ አባቶችና ለአስታራቂ ሽማግሌዎች የሚሰጠው ክብር ፣ ለእምነቱ ያለውን የመንፈስ ጽኑነት በመመልከት እውቀት ይገኝበታል። ስለሆነም የማህበረሰቡን ህይወት ለመመርመር የተነሳሽነት ስሜት ሊፈጥር ይችላል።

ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳም አላቸው፡፡ ባህላዊው የግጭት አፈታት ሂደት እንደመደበኛው ፍ/ቤት በርካታ የጊዜ ቀጠሮ የሚጠየቅበት አይደለም፡፡ በአጭር ጊዜ ይከናወናል፡፡ በመሆኑም የተገልጋዮችን ጊዜ ይቆጥባል፡፡ ፍ/ቤት በመመላለስ የሚያሳልፉትን ጊዜ በምርት ስራ ላይ ስለሚያውሉት የተሻለ ገቢን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በስራቸውም ላይ ጫና አይፈጥርም፡፡ እንደመደበኛው ፍ/ቤት አጥፊዎች በእስር ስለማይቀጡ ከመደበኛ ስራቸው አይስተጓጎሉም፡፡ ስለሆኑም የበዳዩ ቤተሰቦች ለችግር ፣ ለስደትና ለልመና አይጋለጡም፡፡ ግጭቱ ቶሎ ስለሚበርዱና ስለሚፈቱ ተጨማሪ ግጭት ተፈጥሮ ንብረት እንዳይወድም ያደርጋል፡፡ የበደለው ወገን በተለይም (ገዳይ ከሆነ) በርከት ያለ ካሳ ስለሚጠየቅ ሁለተኛ ወንጀልን ደፍሮ አይሰራም፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ አስተዳደራዊ ፋይዳ እንዳላቸው ማወቅ ይቻላል፡፡

አንድ ግጭት ወደ ሌላ አካባቢና ሰው ከመዝመቱ በፊት ወይም ሳያድግና ሌላ መልክ ሳይኖረው በፍጥነት ስለሚፈታ አካባቢን (አገርን) ያረጋጋል፡፡ በባህላዊ የግጭት መፍቻ የራሳቸውን ባህልና ልምድ በተጠቀመ ቁጥር በራስ የመተማመናቸው ብቃት ይጨምራል ተብሎ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያም ተጋጭዎች ወደ ተቋመ ሲሄዱ ችግራችንን ያቃልለዋል ብለው አስበው ስለሚሄዱ በራስ የመተማማን ሁኔታ ይጨምራል፡፡

ማህበራዊ ፋይዳቸው ደግሞ ግጭቶች በጋራ ስምምነት ላይ ተመስርተው የሚፈቱ በመሆናቸው ሁለቱም ወገኖች ከእርቅ በኋላ ወደ ቀድሞው ማህበራዊ ግንኙነታቸው እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል፡፡ የማህበራዊነቱም ደረጃ እንደግጭቱ ቅለትና ክብደት እስከ ጋብቻ ሊዘልቅ የሚችል በመሆኑ ቋሚ የሆነ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ እርቃቸውን መሰረት አድርጎ በሚፈጠር ቀረቤታ በስራ ፣ በሰርግ ፣ በመከራ ወዘተ እንዲተጋገዙ ያደርጋቸዋል፡፡ ውሸት የሌለበት ፣ በሃቅ ላይ የተመሰረተ ሚዛናዊ ዳኝነት የሚሰጥበት በዳዩ ጥፋቱን አውቆ ይቅርታ የሚጠይቅበት ፣ ተበዳዩም በአብዛኛው ከአንጀቱ ይቅር የሚልበት በመሆኑ ከልብ እንዲቀራረቡ ያደርጋቸዋል፡፡

5 ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሃሳቦች

5.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዋና ዓላማ በቅማንት ማኅበረሰብ ውስጥ የማኅበረሰቡ አባላት እርስ በእርስም ሆነ ከሌሎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የሚፈጠሩ ግጭቶች የሚፈቱበትን ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ማሳየት ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ መረጃዎች በምልከታ ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ተሰብስበዋል። ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን ክዋኔ አውዳዊ ትንተና ለማካሄድ Contextual Methdological Approachን ተጠቅሚያለሁ።

በማህበረሰቡ ውስጥ ለግጭት መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች ከኢኮኖሚ ፣ ከእሴት ፣ ከሃይማኖት እና ከሞራል ጋር የተያያዙ ናቸው። ብዙ ጊዜ በቅማንት ማህበረሰብ ባህላዊ የፍትህ መስጫ ተቋም ቀርበው መፍትሄ የሚያገኙት ግጭቶች ማስረጃ የሌላቸው ግጭቶች ናቸው። የማህበረሰቡ አባላት በአጥፊውም ወገን ሆነ በበዳይ ወገን የሚያደርሱት አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት በጣም የከፋ ነው ብለው ከሚፈርጇቸው የግጭት ዓይነቶች ነብስ ማጥፋት (የግድያ ወንጀል) ፣ ጠለፋ ፣ የድንበር መጋፋት ፣ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከእነዚህ ግጭቶች መካከል የመጀመሪያው የግድያ ግጭት ነው። ይህ ግጭት የሚዳኘው በወንበሩ ሲሆን ድርጊቱ እንደተፈጸመ ለአካባቢ ሽንጎ አባላት ጥቆማ ይደረጋል። እነርሱም አፈለቁ ለወንበሩ እንዲያሳውቁ በማድረግ እንቅስቃሴ ይጀምራሉ። ከዚህ በኋላ ጉዳዩ ተጣርቶ ገዳዩ ወይም የገዳዩ ቤተሰቦች የደም ካሳ የሚፈጽመባቸው ደንቦች ሀሬዝ ፣ ድንጉተ ሞትሊ ፣ ሂሽነንካ እና ዘመድሻ ይባላሉ።

ሌላው የግጭት ዓይነት ጠለፋ ሲሆን ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ በሁለት ዓይነት መልኩ ይከናወናል። የመጀመሪያው በመፈቃቀድ በፍላጎት ላይ የተመሰረተ ጠላፋ ነው። ይህም ጠላፊው ከምትጠለፈው ልጅ ጋር ተግባብቶ በወያየት የሚፈጸም

ነው። ሁለቱ መግባባትና መፈቃቀራቸው እየጠነከረ ሲመጣና ከሁለቱ ቤተሰቦች የአንደኛው መጋባታቸውን የማይፈልጉ መሆኑን ሲያረጋግጡ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ልጁ ጠልፎ እንዲወስዳት ተስማምተው የሚፈጽሙት ነው። ሌላው የጠለፋ አፈጻጸም በወንዱ ውሳኔ በጉልበት የሚደረግ ነው። ይህን ድርጊት የሚፈጽመው አካል ከልጅቱም ሆነ ከቤተሰብ ፈቃደኝነት ሳይኖር ሲቀር ነው።

ጠለፋው ከተፈጸመ በኋላ የጠላፊው ቤተሰቦች ጠለፋው የተከናወነበትን መንገድ ያጣራሉ። በሁለቱ መፈቃቀድ ከሆነ የሚሰጠው ካሳ እና የእርቅ ስርዓቱ ብዙም ትኩረት የሚሰጠው አይሆንም። ነገር ግን ጠላፊው ተጠላፊዋን አስገድዶ ከሆነ የጠለፋት የልጅቷ ቤተሰቦች ተደፍረዋል ፣ ተንቀዋል ... ተብሎ ስለሚታመን የካሳ አፈጻጸሙም ሆነ ስርዓቱ ይለያያል።

በዚህ ጥናት የተቃኘውና ሦስተኛው የግጭት ዓይነት በቤተሰብ መካከል ከሚደረጉ የግጭት ዓይነቶች የሚፈረጅ ነው። ይኸውም የባልና ሚስት ግጭት ነው። በማህበረሰቡ ባህል መሰረት ባልና ሚስት ሲጣሉ በቅድሚያ በጓደኛ ፣ በቤተሰቦቻቸው ፣ በአበልጅ እና በጎረቤቶቻቸው ችግሩን ለመቅረፍ ይሞክራል። ይህ ካልሆነ ግን ጉዳያቸውን ይዘው ወደ አካባቢ ሽንጎ ይመጣሉ። ባህላዊ የፍትህ ተቋሙ ጉዳዩን መርምሮ የበደለ እንዲክስ ተደርጎ እርቅ ይወርዳል። ካልሆነ ደግሞ በሰላም እንዲለያዩ ይደረጋል።

ከላይ የተገለጹት የፍትህ አካላት በውስጣቸው ማህበረሰቡ ባመነባቸውና በማህበረሰቡ ውስጥ ልዩ ክብር በሚሰጣቸው አባላት የተዋቀረ ነው። እነዚህ አባላት ለዚህ ተቋም የሚመረጡበት መስፈርት እንደተዋረዳቸው ይለያያል። ነገር ግን ሁሉም የፍትህ ተቋማቱ አባላት የሰጡት ውሳኔ ይከበራል።

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚከተሉትን እንደ ግኝት መውሰድ ይቻላል። የመጀመሪያው በማህበረሰቡ ዘንድ ስለግጭት ያለው አሉታዊ አተያይ ነው። በማህበረሰቡ አባላት ግጭት አውዳሚ ፣ ሰውን ከቀየው የሚያፈናቅል ፣ ቤተሰብን የሚበትን ... ተደርጎ ስለሚወሰድ አዎንታዊ ጎን የለውም።

ሁለተኛው ግጭት ሲፈጠር ተለሞ መፍትሄ ማግኘት እንዳለበት ይታመናል። ለዚህም በዚህ ጥናት ውስጥ የቀረቡት የግጭት ዓይነቶችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ሦስተኛውና የመጨረሻው ባህላዊ የፍትህ ተቋማቱ የሚያስገኙት ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ አስተዳደራዊ ፣ ስነልቦናዊ ... ፋይዳዎች ናቸው።

5.2 የይሁንታ ሃሳቦች

በዚህ ጥናት የቀረቡት የቅማንት ማህበረሰብ የግጭት መፍቻ ተቋማት እና የግጭት አፈታት ስርዓት ጥንት በነበሩበት በስፋት ቢቀጥሉ ለአሁኑም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ ከፍተኛ ጠቀሚታ ይኖራቸዋል። ስለሆነም በባህላዊው ስርዓት እና በተቋማቱ የበለጠ ለመጠቀምና ማህበራዊ ፋይዳቸውን እንደያዙ እንዲቆዩ ለማድረግ የሚከተሉትን ይሁንታዎች መተግበሩ መልካም ነው።

በማህበረሰቡ ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ የተለያዩ ግጭቶችን የሚፈቱት የሀገር ሽማግሌዎች እና የግድያ ግጭትን የሚፈቱት ወንበር የተከሰተው ግጭት መፍትሄ እሰኪያገኝ ድረስ ደክመኝ ፣ ሰለቸኝ ፣ ስራ አለብኝ ወዘተ ሳይሉ ይለፋሉ ፤ ይደክማሉ። ነገር ግን እነዚህ ሽማግሌዎች ከመንግስት ፣ ከማህበረሰቡ እና ከታራቂዎች የሚያገኙት ጥቅም የለም። የእነሱ ጥረት የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት ማስጠበቅ ነው። ቢሆንም አንድ ስራ እንጀራ የማያበላ ከሆነ ሰራተኛው እስከመጨረሻው በዛ ስራ ይቀጥላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ይመስለኛል። ስለዚህ እነዚህ ማህበራዊው ሕይወት ሰላማዊ እንዲሆን የሚተጉ የሀገር ሽማግሌዎች በበጎ ምግባራቸው እንዲቀጥሉ ለማድረግ መንግስት ፣ የክልሉ መስተዳድር ፣ የዞንና የወረዳ የሰላምና የደህንነት አካላት ለስራቸው እውቅና መስጠት ፣ መተዳደሪያ የሚሆን ክፍያ መክፈል ፣ በሞራልና በቁሳቁስ ማገዝ የመሳሰሉትን ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል።

ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቱን እና ሌሎች የማህበረሰቡን ባህላዊ እውቀቶች በጥናት ላይ በመመስረት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተት ፤ በተለይ በማህበረሰቡ ቋንቋ ፣ ትምህርት በሚሰጥባቸው ደረጃዎች ፣ በህብረተሰቡ እና

በቋንቋ ትምህርት ዓይነቶች ውስጥ በማካተት ፣ አዲሱ ትውልድ የማህበረሰቡን ባህልና እውቀት ከዘመናዊው ትምህርት ጎን ለጎን እንዲማር ማድረግ፡፡

ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቱ በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ከሚተገበሩ መሰል ጠቃሚ ልማዳዊ ደንቦች ጋር ተቀናጅቶ ከኢትዮጵያ ዘመናዊ የህግ ሰነዶች ጋር ሊሰራ የሚችልበትን ዘዴ መቀየስ፡፡
የህገር ሽማግሌዎች እና የመደበኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በመቀራረብ ፣ በመረዳዳትና በመመካከር የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፡፡

የፍትህ አካላት ፣ የዘርፉ ምሁራን ፣ የክልልና የዞን የብሄር ብሄረሰቦች ምክር ቤቶች ፣ በሰላምና ደህንነት ላይ የሚሰሩ መንግሥታዊ የሆኑና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅት ጭምር የበኩላቸውን ድርሻ ቢወጡ መልካም ነው፡፡

ዋቢ ጽሑፎች

ሃፍታይ ገ/እግዚአብሄር፡፡ ‹‹ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በኩናማ ብሄረሰብ ›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ለታሪክ ተሾመ፡፡ ‹‹ የባሌ ኦሮሞ የግጭት አፈታት ›› አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ሰለሞን ሲሳይ፡፡ ‹‹ የቅማንት ብሄረሰብ የግብቻ ስነ ስርዓት እና የሰርግ ግጥም ትንተና ›› አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ ፣ 1998 ዓ.ም፡፡

ሰለሽ አባተ፡፡ ‹‹ የሸካኞ ብሄረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ›› አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ ፣ 2002 ዓ.ም፡፡

ብርሃኑ ቦጋለ፡፡ ‹‹ መሳል- ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በአንጸኪያ ገምዛ ወረዳ ›› አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

አብነት ሰለሞን፡፡ ‹‹ የቅማንት ማህበረሰብ ማንነት በዝርው የቃል ተረኮቻቸው ውስጥ ›› አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ ፣ 2005 ዓ.ም፡፡

አንዱዓለም አባተ፡፡ ‹‹ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በመኤኒት ብሄረሰብ ›› ፣ አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ 2004 ዓ.ም፡፡

አየለ ፍቅሬ፡፡ ‹‹ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ማህበረሰብ ›› አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ 1998 ዓ.ም፡፡

ዓለሙ ካሣዬ፡፡ ‹‹ ባህላዊ የደም ማድረቅ እርቅ ስርዓት በላሎ- ማማ ምድር ወረዳ ›› አ.አ.ዩ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፣ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ዲማጽ 1999 ዓ.ም፡፡

Assefa Abebe ‹‹ Conflict : Its Caused and Resolution . Theortical Sources Paper'' Pastoralism in South Omo : Towards an Integrated Development . Proceeding of the Work Shop heid in Jinka (South Omo) October 11-12 , 2001 .

Augsburger W. David. *Conflict Mediation Across Cultures.* Louisille London : Westminster John Konz press , 1992 .

Ben-Amos, Dan (1982). *Folklore in Context*. New York. New Hampshire press, 1982.

Bensinger, M. H. (1988). ‹‹Lecture Textual Folkloric.›› *Journal of American Folklore*, 101/401. New York: New Hampshire.

Buman,Richard (1983*) the Field Study of Folklore in Context* in hand book of American folklore (ed) by (Richard. M. Dorson) bloominition; Indian university press.

Coser. Lewis *A Continuities in the Study of Social Conflict* . New York : The Free Press , 1967 .

_____. *The Function of Social Conflict . 1st ed . New York : Free Press , 1964 .*

Deborah , A.Kapchan .‹‹Common Ground ; Key Words for the Study of Expressive Culture ›› *the Journal of American Folklore* . vol . 108 , no 430 , p . 479-508 , 1995.

Dorson , R . (ED) *Folklore and folk life : An Introduction* . the University of Chicago Press , 1972

Dundes , Alan . ‹‹ folkloristics in the twenty- first century : (AFS invited presidential . plenary address , 2004)›› . 2005 *Journal of America Folklore* ,118.

Dundes , Alan . *the Study of Folklore*. N.J; prentice- hallinc , 1965.

Finnegan , Ruth . *Oral Literature in Africa* . Oxford Clarenden Press , 1970 .

_____. *Oral Tradition and the Verbal Arts* . USA and Canada : Routledge is an International Thomses Publishing Company , 1992 .

Fisher, D. Ibrahim et al., *Working with Conflict. Skills and Strategies for Action*. Bath: UK, Zed Books, 2000.

Fisher, J.Ronald. *Social Psychology an Applid Approach*. New York. St.Martins Press, 1982.

Gamst, F.C ‹‹The Qemant Agaw of Ethiopia: A Study in Culture Change of A pagan Hebraic Culture.›› Unpublished Ph.D. Dissertation, 1967.

_____ "The Qemant: A Pagam-Hebraic Peasantry of Ethiopia. Cases studies in cultural Anthropology››. New York: Holt Rinehart and Wilson, 1969.

Goldstein, Kenneth. *A Guide for Filed Workers in Folklores*. Pennsy/vania : Gale Research Company . 1974 (American folklore association inc.)

Habtamu Wondimu. *Hand Book of Peace and Human Right Education in Ethiopia* .Addis Abeba. OSSREA , 2008 .

Habtamu Wondimu, (1998) ‹‹Conflict Resolution in the Families of Nine Ethnic Groups in Ethiopia.›› The Ethiopian Journal of Education. Vol. XVIII.

Jerome , Smith . *Folklore and folk life ; An Introduction* . Chicago and London ; the University of Chicago Press , 1972.

Kreidler , W . *Creative Conflict Resolution* . more than 200 activities for keeping peace in the class room . Glen View , IL : Scott , Foresman and Company .

Medhane Tadesse . ‹‹The Quest for Conflict Settlement in Ethiopia 's Territory›› . Addis Abeba Eventstifing , 2004 .

Nader , L. ‹‹*Conflict Anthropological Aspect* '' International Encyclopedia of the Social Science . vol , 3 . New York : Macmillan Company and the Free Press , 1968 : 230 – 241

Rapport , Roya . *Ritual and Religon in the Making of Humanity* . UK. United kingdom at the University Press . Cambridge , 1999.

Schellenberg . James A. *Conflict Resolution : Theory , Research and Practice*. Albany : State Universtiy of New York Press , 1968 .

Tirsit Girshaw. ‹‹Indigenous Conflict Resolution Mechanism in Ethiopia››. (Paper Presented for First National Conference on Federalism, Conflict and Peace Building, May 5-7).Addis Abeba, Ethiopia,1999.

Webel , Charles and Johan Galtung . Eds . *Hand Book of Peace and Conflict Studies* . Londen : Rutledege , 2007 .

Zelealem Leyew. ‹‹The Kemantney Language: A Sociolinguist and Grammatical Study of Language Replacement››. PhD: Dissertation. RUDIGER Koppe Verlag. Kerlag.Loln, 2003.

አባሪ አንድ

አውራ የመረጃ አቀባዮች አጭር መግለጫ

1. **አቶ አየልኝ ተሰማ ፡-** አቶ አየልኝ ተወልደው ያደጉት በጭልጋ ወረዳ ልዩ ስሙ አንተብ ደዛ ተብሎ በሚታወቅ ቦታ ነው፡፡ አሁን በአይከል ከተማ ነዋሪ ሲሆኑ ዕድሜያቸው 59 ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለአስታራቂነት ከሚመረጡት የአገር ሽማግሌዎች መካከል አንዱ ሲሆኑ የዘር ረጋቸው ከክብር የዘር ሀረግ የሆኑ ናቸው፡፡ መተዳደሪያቸው በእርሻና ከብት በማርባት ነው፡፡ አቶ አየልኝ ስለማህበረሰቡ ካመጣጡ ጀምሮ አጠቃላይ ገጽታውን እንዲሁም የጥናቱ ትኩረት ስለሆነው የማህበረሰቡ የግጭት አፈታት ሥርዓት ሰፊ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

2. **አቶ ፍርዱ ነቃ ፡-** አቶ ፍርዱ ነቃ ዕድሜያቸው 72 ሲሆን በጭልጋ ወረዳ ልዩ ስሙ ኩሽይና ዋጅሞ በተባለ ቦታ ተወልደው ያደጉ ናቸው፡፡ አቶ ፍርዱ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ክብር የሚሰጣቸው ፣ ሃይማኖቱንና (ህገ-ልቦናን) ቋንቋውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ፣ የማህበረሰቡን ታሪክ በማወቅ አንቱ የተባሉ ናቸው፡፡ የዘር ሃረጋቸው ከክብር ሲሆን በማንኛውም ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ወቅት ለፍትህ ተቋማቱ ወሳኝ ሰው ናቸው፡፡ መተዳደሪያቸው እርሻና በብዛት ከብት በማርባት ነው፡፡ እኚህ የዕድሜ ባለ ፀጋ ስለማህበረሰቡም ሆነ ስለባህላዊ የግጭት አፈታቱ ሰፊ ግንዛቤን ያስጨበጡኝ ሰው ናቸው፡፡

3. **መቶ አለቃ ጥጋቡ ዘገየ ፡-** መቶ አለቃ ጥጋቡ በጭልጋ ወረዳ ልዩ ስሙ ተንበራ ከዋ በተባለ ቦታ ተወልደው ያደጉ ሲሆን ዕድሜያቸው 55 ነው፡፡ በጭልጋ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ ጽ/ቤት ውስጥ የበላይ አዛዥ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ከክብር የዘር ሀረግ የተገኙ ናቸው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ከበሬታ የሚሰጣቸው ፣ ባህላዊውና ዘመናዊው የፍትህ ተቋም ተባብሮ እንዲሰራና የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ ቀን ተሌት የሚጥሩ ናቸው፡፡ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ በስራ አስተዳደር ዘርፍ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ የሚተዳደሩት ከመንግስት በሚያገኙት ወርሃዊ ክፍያ (ደመወዝ) ነው፡፡ ስለ ማህበረሰቡ በአጠቃላይ የሚያውቁትን በመንገር ፣ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሰዎችን በመጠቆም ቀና ትብብር አድርገውልኛል፡፡

4.አቶ እዮብ ድንቁ ፡- አቶ እዮብ ከይተንቲ የዘር ሀረግ የተገኙ ፣ በሞልጋ ወረዳ ልዩ ስሙ ቤዛሆ መቀነት በተባለ ቦታ ተወልደው ያደጉ ናቸው፡፡ ዕድሜያቸው 32 ነው፡፡ በሞልጋ ወረዳ ፖሊስ መምሪያ ጽ/ቤት ውስጥ የወንጀል ክትትል ኦፊሰር ሆነው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከቅድስት ማርያም ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በርቀት ትምህርት ክፍል በቋንቋ ዲፕሎማ አግኝተዋል፡፡ የሚተዳደሩት ከመንግስት በሚያገኙት ወርሃዊ ክፍያ (ደመወዝ) ነው፡፡ ወደ አካባቢው ስሄድ መልካም አቀባበል በማደረግ ፣ ማንን ማናገርና ማግኘት እንዳለብኝ በመጠቆም ፣ የሚያውቁትን መረጃ በመስጠት ፣ የተባበሩኝ ሰው ናቸው፡፡

አባሪ ሁለት

የአጋዥ መረጃ አቀባዮች ስም ዝርዝር

ተ.ቁ	መ/ለ ስም	ጸታ	ዕድሜ	አድራሻ	መግለጫ
1	ጥጋብ ወንድይፍራው	ሴት	37	ጎንደር ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ በጎንደር ከተማ በግል የንግድ ስራ የተሰማሩ፡፡
2	ነጋ ጌጤ	ወንድ	57	ጎንደር ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ በጎንደር ከተማ በግል የንግድ ስራ የተሰማሩ፡፡
3	አበቅ የለሽ መርሻ	ሴት	29	አይከል ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ በአይከል ከተማ የ9ኛ ክፍለተማሪ፡፡
4	እንዳለው ጋሻው	ወንድ	43	ጎንደር ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ በጎንደር ከተማ የጎንደር መምህራን ኮሌጅ መምህር፡፡
5	አስቻል አሻግሬ	ሴት	63	ጎንደር ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ የቤት እመቤት፡፡
6	ጥሩዘር ተሾመ	ሴት	48	ጎንደር ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ የቤት እመቤት፡፡
7	እነየ አየልኝ	ሴት	37	አይከል ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ የቤት እመቤት፡፡
8	አውግቸው ተሰማ	ወንድ	31	አይከል ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ፡፡
9	ቢራራ በለጠ	ወንድ	45	አይከል ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ በእርሻ ስራ የሚተዳደሩ፡፡
10	ትሻል ሰጠኝ	ሴት	53	ጎንደር ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ የፋሲለ ደስ ትምህርት ቤት መምህርት፡፡
11	ሲሳይ ነጋ	ወንድ	47	ጎንደር ከተማ	የቅማንት ማህበረሰብ ተወላጅ ፣ በአስጎብኝነት የሚተዳደሩ፡፡

አባሪ ሦስት

የቡድን አንድ መግለጫ

ተ.ቁ	የቡድን አባላት ስም ዝርዝር	የተወያዩበት ቦታ
1	መቶ አለቃ ጥጋቡ ዘገየ	አይከል
2	አቶ ፍርዱ ነቃ	አይከል
3	አቶ አየልኝ ተሰማ	አይከል
4	አቶ ኢዮብ ድንቁ	አይከል

የቡድን ሁለት መግለጫ

ተ.ቁ	የቡድን አባላት ስም ዝርዝር	የተወያዩበት ቦታ
1	ሲሳይ ነጋ	ጎንደር
2	እንዳለው ጋሻው	ጎንደር
3	ጥጋብ ወንድይፍራው	ጎንደር
4	ጥሩዘር ተሾመ	ጎንደር